

# ጌይ ፊቀር
# የሀረሪዎች ሙዚቃ

ኢሊያስ ተስፋዬ

አሳታሚ ፡- የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ

ሐረር/2012

# ጌይ ፊቀር

# የሀረሬዎች ሙዚቃ

ፀሐፊ፡-ኢሊያስ ተስፋዬ

ዲዛይን፡- ዮሴፍ በቀለ

**አሳታሚ፡- የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ**

**ሐረር/2012**

ለ________________________________



ይህ መፅሐፍ መታሰቢያነቱ በጣም ለምወዳቸውና ለፍቅራቸው ምንዳ ለሌለኝ ለሑሉም እናት ለሑሉም መሰብሰቢያ አድባር ለነበሩ ለአያቴ ለኡማ በድሪያ አህመድ አሊ ሻሚ/ኡማ በድሪያ/ቢዮ/አባያ/ ማስታወሻ ይሁንልኝ::

# ማውጫ


ተ ቁ ርዕስ ገፅ

1. መቅደምት ........................................ 1
2. መግቢያ........................................ 3
3.ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ ( አይ ሻሚቱ )........................................ 5
4. ስለ ዘፌን ካብተዘፌኑ እና ካብተባሉት የስንኝ ቋጠሮ........................................17
5. የሀረሪ ሙዚቃ እና የታሪካ ቁርኟት........................................ 21
6. “ሙጋጽ”(ቡጽኙ) ........................................ 33
   6.1–ኩሉብ ሀኖላተ ........................................ 34
   6.2– አመሸና ........................................ 36
7. ሙጋጽ እንዴት ይመሰረታል? :– ........................................ 39
8.ቀደም ብለው የተመሰረቱ ሙጋጾቹ ........................................41
   8.1 ሑላል ሙጋጽ ........................................55
   8.2 ማሕፋዛቹ ሙጋጽ፡– ........................................58
   8.3 ፌዛላቹ ሙጋጽ ........................................58
   8.4 አዲባቹ ሙጋጽ :– ........................................ 59
   8.5 ሐይዋናቹ ሙጋጽ፡– ........................................ 60
   8.6 አፍሪካቹ ሙጋጽ........................................62
   8.7 የሙጋጾቹ አባላት ስም ዝርዝር ........................................ 63
9. የሀረሪ የሙዚቃ ስራዎቹ በሌሎቹ አርቲስቶቹ........................................71
10. ሀረሪ እና ሙዚቃ መሳርያ ........................................ 73
   10.1 ደፍ /Frame drum/ ........................................ 73
   10.2 ካረቡ/kettle drums/........................................ 74
   10.3 ካበል/wooden blocks/ ........................................ 75
   10.4 ኪራር አልያም ኪስሳር (ካራር) ........................................ 75

10.5 ታንበር/ tanbur / (ማሲንቆ) ........................ 76
10.6 ቀርና (ዋሽንት) ፡- ........................ 76
10.7 የሀረሪ ሙጋዶቹ ይጫወቱት ነበነበረው የሙዚቃ ........................ 82
11.ቀፌት መሃለቅ........................ 88
12. ፌቀር (ዘፌን) ........................91
13. ስለ “ጌይ”አጭር መግለጫ ........................92
14. ጌይ ለዳ ፌቀር........................ 93
15. የሀረሪ ዘፌን የቅኚት ጫፉ እና ስር መሰረቱ ........................ 96
16. የሀረሪ የግጥም አፃፃፍ እና የገለፃ ለሳሳል........................ 97
17. የሀረሪ ባህላዊ ዘፌኖቹ የቅኚት አይነቶቹ እና ምንነት ........................98
18. ሳሌይ........................98
19. ሜራስ........................100
19.1 ዱመሲዛላ /መሪ /THROWER/ ........................ 102
9.2 ዱላህዴዛል/ተቀባይ/CHATCHER........................ 102
19.3 በሜራስ ስር የሚገኙ የተወሰኑ የዘፌን ግጥሞቹ........................ 110
20. ጸርሲ........................ 124
20. 1 ነሺዳ ........................ 125
20.2 ዚክሪ ........................ 125
20.3 ጸባል ፌቀር ........................133
21. መስኖይ........................135
22. ጌይ ለዳ ፌቀር ዊቂር ቃ ም ........................
/የሀረሪ ባህል ዘፌን የግጥም ይዘት/........................143
23. የጌይ ለዳ ፌቀር ሙዚቃዊ ቴክኒካቹ........................144
24. የግጥም አፃፃፍ ስነ ፅሁፍ........................146
25. ሀረሪ በአማርኛ ስነ ፅሁፍ ........................159
የአርቲስቶቹ የፎቶ መግለጫ........................ 168

# 1. መቅደምት

ይህ አነስተኛ መፅሀፍ የተዘጋጀው በሀረሪ ሙዚቃ ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ባለመካሔዱና ለአጥኚዎች በቂ መረጃ የሚሰጥ ምንጭ እምብዛም ባለመኖሩ ነው፡፡ እንዲሁም የዚህ ሙዚቃና ባህል ባለቤት የሆኑት የሀረሪ ብሔረሰብ የራሳቸውን የሙዚቃ ስልት፣የታሪክ ሑደቱን፣ግጥሙን፣ወዘተ...ጠንቅቀው እንዲያውቁትና ጉልበት እያጣ ያለውን የሀረሪ ባህላዊ ሙዚቃ እና ልዩ የአዛዜም ስልቱ ዳግም እንዲያንሣብብ እንድሁም እንደቀረው ባህል አንድ የራሳቸው አድርገው ከራሳቸው ጋር እንዲዋሃድ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ይህ የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያቱ ሙዚቃው በሀረሪ ብሔረሰብ በሁሉም የእድሜ ደረጃ የሚዜም ቢሖንም ሳይንሳዊ የሙዚቃ መዋቅሩን ለማወቅ የሚያስችል ግኝት ባለመኖሩና የሙዚቃው ስልት ጥንታዊና በሙዚቃ አይነት ምድቡ እስካሑን ባለ ጥናት በኢትዮጵያ ብቸኛ የሙዚቃ ስልት ያለው በመሆኑ ለቀሪው የሙዚቃ ምሁሮች እንደ ምንጭ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ ነው፡፡

ታድያ ይህ መፀሐፍ ለጠቅላላ እውቀት ብቻ ታስቦ የተዘጋጀ ሳይሆን ለሀረሪ ሙዚቃ ማስተማሪያነት ለሚዘጋጁ መፅሐፍት ገቢር ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ ነው፡፡አንዳንድ የሙዚቃ ቋንቋዎች እና በማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊረዳው የማይችለው የሙዚቃ ቃላቶች አሉ፡፡

እነዚህ የሙዚቃ ቋንቋዎችን በተቻለኝ መጠን ለማብራራት ሞክርያለሁ፡፡ነገር ግን በአማረኛ ምትክ ያጣሁላቸውን ቃላት እንዳሉ አስቀምጫቸዋልሁ፡፡የሀረሪ ሙዚቃ ቴክኒካል የሆኑትን ክፍሎች ለመግለፅ የሞከርኩት በሙዚቃ ጠለቅ ያለ እውቀት እና ባለሞያ ትክክለኛውን የሀረሪ ባሕላዊ ሙዚቃ በዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያና ስልት እንዴት መጫወት ይችላሉ የሚለውን ለማሳየት እንዲሁም ከዘመናዊው የአዘፋፈን ስልት ጋር ለማዋሃድ እንዲረዳ ብዬ ያዘጋጀሁት ነው፡፡ ታዲያ ይህ መፅሐፍ ከባሕር የተጨለፈ እንጂ ባህር አለመሆኑን ማስመር እፈልጋለው፡፡

ፀሐፊው

# 2. መግቢያ

ሀረር በሆነ ወቅት አገር የነበረች አሁን ጥንታዊ ከተማ እና ከአንድ ሺህ በላይ  እድሜ ባለፀጋ ታሪክና ባህል ያላት ከተማ እንደመሆኗ መጠን የራሷ የሆነ የህዝብ፣ንግድ፣ዘርና ብሔር ብሔረሰቦች  መናሃሪያ ነች፡፡ በክልሏም ሀረሪ፣ ኦሮሞ፣ትግሬ፣ስልጤ፣አማራ፣ሶማሌ፣ ወዘተ.... ሲኖሩባት  የእስልምና፣የካቶሊክ፣የኦርቶዶክስ፣ፕሮቴስታንት፣  እምነት ተከታዮች የያዘች በታላላቅ ቤተ- መቅደሶች የተከበበች የአንድነት መዲና ተምሳሌት ነች፡፡ለዚህም ማስረጃ በአለም አቀፍ መሸለሟን መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል፡፡

የብሄር ብሄረሰቦች መገለጫ ባህሉ እንደመሆኑ መጠን የክልሉ ባለቤት የሆኑትየሀረሪ ብሄረሰብ ማንነቱ እና ምንነቱን(ሑጅጃ ዋ ቁራስ) ከሚገልፅ መካከል የሀረሪ ብሄር ዘፈን አንዱ ነው፡፡ሀረሪዎች ለሙዚቃ ካላቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ የማሃበራዊ ህይወታቸውን ክንውን ድርጊትና መስተጋብር ለዘመናት የህይዎት ጉዞአቸውን ባጠቃላይ ማለት ይቻላል በዘፈኖቻቸው አማካኝነት ታሪክን ለባለ ታሪኩ ከትውልደ-ትውልደ ለምእተ-አመታት ሲያወርሱ ኖረዋል፡፡

## “ዋኪ ዘል ኻና ወኪ ዩ ኹኔል”

## ዘፋኝ ያልሆነ ፃድቅ አይሆንም

ለዝክሪ እና ለሙዚቃ ካላቸው ከፍተኛ ቁርኝት የተነሳ አብሮአቸው ለዘመናት ሲዘልቅ ለሀረሪ አርት የራሱን ድርሻ አበረክቶ አልፎዋል፡፡ ሌላው ተፅእኖ ማሳደር የቻለው በ7[ኛው] ክፍለ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት ሀረር ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ለአርቱ በር እንደከፈተ ይነገራል፡፡ በጥልቅ ተገብቶበት የጎላ ጥናት ባይደረግባቸውም የሀረሪ ሙዚቃ የሀረርን የሶስት ሺህ እድሜ(ከሚነገርላት አንድ ሺው ውጪ) ጉዞ እንደሚገልፅ እና ለታሪክ ፀሀፊያን እንደ አንድ ገቢር ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ይሰማኛል፡፡

ምክንያቱም ሙዚቃ ነባራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ያለፈውን፣ያሁኑን፣የውደፊቱን እየተነበየ ታሪክን በግጥም፣በሙዚቃ ውስጥ እይታን በመፍጠር በምናብ መስኮት እውነታውን የሚያሳዩን የጥበብ አውታሮች ናቸው፡፡

የሀረሪ ሙዚቃም ከቋንቋው ተናጋሪ አልፈው የብዙዎችን ቀልብ የሳበ የውጪ አጥኚዎች የጥናት ዘርፋቸውን ወዲሕ ያዞሩበት የብዙዎች የድምፅ አርት ቃናቸው ነው፡፡ስለዚህ ሁሉም የዚህ ሙዚቃ እውነታን ይረዳ ዘንድ ከባህላዊ አዛዜም በመነሳት ዘመናዊ ሙዚቃዎችንም ለመመልከት እና ለማስቃኘት እሞክራለው፡፡

# ३.ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ ( አይ ሻሚቱ )

## የዲሚሾቅ ኀግስት

ከዚህ መጽሐፍ ጎን ለሙዚቃው ለባህላዊ ዘፈን ከሞት አፋፍ አንስታ ለዛሬ ትውልድ ያቀበለችውን የዲቢሽቋን ንግስት ታሪክ ላካፍላችሁ፡፡



የሀረሪ ባህላዊ ሙዚቃ ንግስት ተብላ ከሀያ ሚበልጡ ቅጥያ ስያሜዎች ተሰጥቷታል፡፡ ሻሚቱ፣ዲቢሽቂ፣ሁድሁዳ፣ሻም እና መሰል ስያሜዎች...

ታዋቂውና ብቸኛው ጂዮሎጂስት፣ አርኪዮሎጂስትና የታሪክ፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ ምሁር ፀሐፊና ገጣሚ ከነበሩት አው አህመድ አሊ ሻሚ እና ከታዋቂዋ ቡና ነጋዴና የሰፌድ መምህርት ከነበሩት እናታቸው ዘይነባ ሁሴን ቱርኪ ከአምስቱ በር በአንዱ ቡዳ በር (በድሮ በሪ) አከባቢ በመጀመሪያው ሞይ ጋር(ሰፌድ መስፋት የሚማሩበት ቤት) በ1930 ዓ.ም ለቤተሰባቸው አምስተኛ ልጅ ሆነው እቺን አለም ተቀላቀሉ፡፡

አርኪዮሎጂስቱ አባታቸው አው አህመድ የዋዛ አልነበሩምና ቁጣቸውን ፍርሐት ከቤት ወጥቶ መክረም የማይታሰብ ነበር፡፡ በስርአት አሳደጓቸው፡፡እድሜአቸው አራት ሲሞላ ወደ ቁርአን ጌይ(የሐይማኖት ትምህርት ቤት) ገቡ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ አባታቸው አው አህመድ ሻሚ ሀሙስ ሀምሌ በ1936 ለኢድ ሰላት አው አብዳል መስኪድ ሶስተኛ ልጃቸው የሆኑትን በድሪያ አህመድ አሊ ሻሚ እና ሻሚቱን ይዘው ሲሄዱ በወቅቱ ተከስቶ በነበረው እ.ኤ.አ. july 20,1944 የፀሐይ ግርዶሽ (solar eclipse) ሁለቱም የልጅነት ነገር ሆነና ወደ ሰማይ አንጋጠው ሲመለከቱ በግርዶሹ መሀከል አፈትልኮ በሚወጣው ብርሐን የሁለቱም አይን ለጊዜው የጨለመ ሲሆን ወዲያው ሆስፒታል በሚሄዱበት ወቅት የእህታቸው አይን ሲበራ የሻሚቱ አይን ዳግም ሳይበራ ቀረ፡፡

ይህ ጊዜ ለ6 አመት ህፃን የሚቻል አልነበረም፡፡ ትምህርቷን አቋርጣ ቤት መዋል ሆነ፡፡አዳጋች ግዜአትን ካለፈች በኋላ ቤት ውስጥ በራሷና በአባቷ ጥረት ነገሮችን በመዳሰስና በማዳመጥ የመለየት ባህሪ እንድታዳብር መንገድ ተከፈተላት፡፡በዚህ ጊዜያት አባቷን የመርዳትና እንደማንኛውም ጤነኛ ሴት ቤት ውስጥ መስራት መንጎዳጎድ ጀመረች፡፡ ይህ ሞራሏን የገነባላት ሲሆን ጤናማነት እንዲሰማት አድርጓታል፡፡

በዚህ ጊዜ የአይኗን ቦታ ተክቶ የሚሰራው ጆሮዋ ማንኛውንም ድምጽ ከያለበት እየለቃቀመ ሲያስደምጣት ቃና ያላቸው ዜማዎችን ጆሮ መስጠት ጀመረች፡፡ በዚህ ጊዜ አባቷ እየጠፉ የነበሩ የመስኖይ ግጥሞችን መሰብሰብና ዜማውን ለመረዳት እየሞከሩ የነበሩት ጊዜ ስለነበር ጆሮ ሰጥታ ማዳመጥ መጀመሯ ለሙዚቃው በር ከፈተላት፡፡

ብዙም ሳይቆይ በየስፍራው የሚንጎረጎሩ የባህል ዘፈኖችን ከአባቶች (በእድሜ በጉልምስና ደረጃ ያሉ ተሰብስበው ያንጎራጉራሉ) ከነዚህ ባህላዊ ይዘቱን በመውሰድ የባህል ሙዚቃውን ተረዳችው። ቤት ውስጥ ማንጎራጎርና ለጓደኞቿ መዝፈን ጀመረች፡፡ ሆኖም አባቷ እንድትዘፍን ፍላጎት ስላልነበራቸው ከማንጎራጎር የዘለለ ነፃነት አልነበራትም፡፡ በ1946 የጓደኛዋ ሰርግ ላይ እንድትገኝና እንድትዘፍንላት ጓደኛዋ ጥያቄ አቀረበችላት፡፡ አባቷ የሚቀመሱ ባለመሆናቸው ለማስፈቀድ የሚደፍር አልነበረም፡፡ስለዚህ ያላቸው አማራጭ ይዘዋት በድብቅ መሔድ ነበርና አባቷ ቀኑን ሙሉ ውጪ የማእድን ምርመራ እና ማፈላለግ ላይ ስለሚጠመዱ በተገኘው አጋጣሚ ይዘዋት ሔዱ፡፡



የመጀመሪያ ስራዋ የሆነውን ከአባቷ ያዳመጠችውን ከሰበሰቡት የመስኖይ ዘፈን በመዝፈን የአድማጨን ምላሽ በጀሮዋ መጠበቅ ጀመረች፡፡ሰርጉ ላይ የነበሩ ሁሉ ተደመሙ ባህሉ እና ባህላዊ ሙዚቃው እየሻከረ በመጣበት ጊዜ ዳግም በማድመጣቸው እጅጉን ተደሰቱ፡፡ አበረታቷት እንድትቀጥልበት ገፋፏት፡፡በጊዜው በሁለት ለሚዜሙ ዘፈኖች ተቀባይ ባይኖራትም አድማጭ ተቀባይ ሆኖ አብሯት በማዜም ያጅቧት ነበር፡፡

ያኔ እድሜዋ 16ቱን እየጨረሰች ነበር፡፡ያገኘችውን ሞራል እና የተወሰነ ገንዘብ ይበልጥ ወጥቶ ለመዝፈን ጉጉት አደረባት፡፡ቀን በቀን እንደተለመደው እየተደበቀች በመውጣት መዝፈኑን ተያያዘችው፡፡ ስሟ እየገነነ በመጣ ጊዜ ያባቷ ጆሮ መድረሱ አልቀረም፡፡

በአንድ ወቅት አባቷ "ጉፍተ ኑጉድ" ተብሎ በሚጠራ ገደላማ ተራራ አቅራቢያ የነበራቸውን የጂዮሎጂ እና የአርኪዮሎጂ ጥናት አገባደው ሲመለሱ ሰፈር ከመድረሳቸው አንድ እናት እንዲሕ ሲሉ ሹክ አሏቸው "አባ ሻሚ ቀሐትኾ ጠበዜ ሑድ ሑዳ መንቴ" (ታላቅ ወንድሜ ሻሚ የልጀት ድምፅ ጅንጅላቴ ወፍ ድምፅ አላት) ሲሉ አሞካሽተው ነገሯቸው፡፡(ጅንጅላቴ ወፍ በኢንግሊዘኛው Hoopoe bird) ነች፡፡ ይህን ግዜ አባቷ ተናደው ድንጋይ ሚፈለቅቁበትን የእጅ ብረት መዶሻ እንደያዙ አለችበት ወደተባለው ሰርግ ቤት ገሰገሱ፡፡

ልበ ብርሐኗ ሻሚቱ በአንድ ልብ እየዘፈነች ስታስጨፍር በድንገት ከበር ደረሱ ያኔ ጓደኞቿ ያባቷን ሐያልነት ያውቁ ስለነበር ሮጠው ነገሯት፡፡ ይህን ጊዜ ለሷም የመጀመሪያ ግጥም ሆነውን ለአባቷ እንዲህ ስትል ተቃኘች፡፡

ኤሐ.....ይ

ባዴይ ባዴይ ኩዴይ - አልላ ኸሸሌሽ

ኤሐ......ይ

ወልላ ኢኔንተኽ - ኢኔሌ ኑር ንኽ

ሀረር ታማኞው- መንጊስቲ ታማኞው

የመአድን መርማሪዮው

አሕመድ አሊ ሻሚዮው

ሲተረጎም፡-

አገሬ አገሬ ውዴ - አልላህ አረገልሽ

ወላሒ አይኔነህ - ለአይኔ ብሌን ነህ

የሀረር ታማኙ - ለመንግስት ታማኙ

የመአድን መርማሪው

አህመድ አሊ ሻሚ ነው

ስትል አናቷ ላይ ሊያሳርፉት የነበረውን መዶሻ መልሰውት አጭር ትዛዝ ሰጧት "ስጨርሺ በጊዜ ወደቤት ግቢ" የሚል ነበር፡፡ ይህ ቀን ለሙዚቃዋ ነፃነት ያገኘችበት እለት ሆነችላት፡፡

በየሰርግ ቤቱ መዝፈን ስራዬ ብላ ተያያዘችው፡፡ ዘፈን ከፍላጎቷ በተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሆነላት ሳታቀው ለሽልማት ግንባሯ ላይ

የሚለጠፍ ብር ብዙ ነገሮችን ይሸፍንላት ጀመር፡፡ ሊጠፉ ዳር ደርሶ የነበረው የመስኖይ ዘፈን ዜማ ዳግም አደሰችው፡፡ዜማው ቢከብድም ለሻሚቱ ግን ውሐ ከመጠጣት በላይ ለጎሮሮዋ የተመቸ ነበር፡፡ ለኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ ቅፅል ስሟ ሆኖ ይጠራ የነበረው ቀዳሚው" ሻሚቱ" ሲሆን ስያሜው የተገኘው በቤተሰብ መጠሪያ ከሆነው ከአባቷ አጭር ስም አልያም "አው ሻሚ" ከሚለው ነው፡፡ አባትሽን ትመስያለሽ ስለምትባል የተሰጣት ስያሜ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ የአባቷ አባት የመጡት ከሱሪያ በመሆኑ የሱሪያ ቀደምት ስሟ ሻም በመሆኑ ስያሜውን አገኙ፡፡ከዚህ ሲቀጥል "ሁድሁዳ" የሚለው በተስረቅራቂ ድምፅ በመነሳት ሀረሪዎች ለሙገሳ ከሚጠሯቸው አዋፋት መሀከል የተሰጣት ነው፡፡

ሌላው ስያሜ "ዲሚሽቂ" ሲሆን ዲማሽቅ አልያም ባሁኗ የሱሪያ ከተማ ዳማስቀስ የተሰየመላት ነው፡፡በዚህም ምክንያት "ዲሚሽቂ አሚራ" አልያም የደማስቀስ ንግስት ይሏታል፡፡በመሰረቱ የሻሚቱ የዘር ግንድ የሚመዘዘው ከቱርክ እና ከሱሪያ በመሆኑ የአባቷን መነሻ ከሆነችው ደማስቀስ የተሰጣት ነው፡፡ እነዚህና በርካታ ስያሜዎች ቢኖራትም ለመግለፅ ሌላ ማብራሪያ የሚሻ በመሆኑ ወደ ታሪኩ ልመለስ፡፡

ከ1994 በፊት በሷ ድምፅ ያልታጀበ ሰርግ አልነበረም፡፡ ሻሚቱ የሌለችበት ሰርግ ባህል እንደጎደለው ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ ሻሚቱ ዘሌልቲባ በለቹ ቀረ ጊር ይማጃል (ሻሚቱ የሌለችበት ሰርግ ቢቀር ይሻላል) ይባልላታል፡፡ በዚህም ምክንያት ከሀረር አልፎ አዲስ አበባ ፣አዳማ፣ድሬደዋ፣ጂጂጋ፣ አለፍ ሲል ግብፅ፣ጀርመን፣ኢንግሊዝ፣አሜሪካ፣ለንደን ባጠቃላይ ሀረሪዎች ባሉበት ሁሉ አገራት ተገኝታ ዘፍናለች፡፡

በዚህ ኡደት ሻሚቱ ከአንድ ዘፋኝነት አልፋ ባህል መሆን የቻለች እንስት ነበረች፡፡ ሻሚቱ አይኖቿ ባያዩም ሰርጉ እስኪጀመር አጠገቧ ጓደኞቿን በማስቀመጥ ሙሽራው ምን እንደለበሰ ሙሽሪት ምን አይነት መልክና ቁመና እንዳላት ባጠቃላይ በአከባቢው ያለውን እንዲነግሯት በማድረግ ሁኔታውን ታጤነዋለች፡፡ ዘፈን ሲጀመር እዛው ጋ ከየት መጡ እስኪባል ለሙሽራው እና ለሙሽሪት በስንኝ ናዳ ከብር በበለጠ ታሞግሳለች፡፡ ይሕ ከሷ ባኋላ ለመጡትም የማይሞከር ጥበብ ሆነ፡፡ ምንም ባትማር ቋንቋ የማይገድባት እውነትም የዲሚሽቅ ንግስት የሚያስብላትን ስራ ሰራች፡፡ ጣሊያነኛ፣ሀረሪ፣ኦሮምኛ፣አረበኛ፣ሶማለኛ፣አማረኛ፣ አቀላጥፋ ትናገራለች፡፡ አባቷ በርካታ ቋንቋዎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለተማሩ ለሷ መነሻ ሆኖላታል፡፡ ዛሬ የባህል ዜማዎች ከነቅኝታቸው እንዲቆዩ ምክንያት የሆነው በሷ ግጥሞች በመሸከማቸው ነው፡፡ ከመቶ 92 እጅ የሚሆኑ ግጥሞች የሻሚቱ ግጥሞች ናቸው፡፡

አብዛኛው ጊዜ በፉከራ በሱሙት ፈቀር፣በሚራስ እና በተለያዩ ዘፈኖች ከሚሰሩ ውስጥ ጥቂት ስንኞችን ብንፈልግ

ሐሚስቲ በሪቤ ዚትፋለሳ በሪ

ዋሊነት ዚኸሻ ቶፒያ አለምቤ የዴጅ በድሮ በሪ

ማሕቡባ ዲሚሽቂው ዩትጋበዛል ጌይቤ ዛሉም ዩመስለኘል

ቶፒያ አለምቤዋ

“ከአምስቱ በር የተሞገሰው

መዝፈን የፈለገ ከኢትዮጵያ ከአለም ይምጣ  ቡዳ በር (በድሮ በሪ)

ማህቡባ ዲሚሽቂን የሚጋፈጥ ሀረር ላይ ያለም አይመስለኝ

ስትል ራሷን የሞገሰችበት ስንኝ ዛሬ የተወሰነ ለውጥ ተደርጎበት ይዜማል፡፡

ቆባ ኢፋጭሌ ሙሳፊሪን ሌጥኹ

ሚስራ ዋ ሮማ ለንደኑ ወረድኹ

ኢላ ጀርመን ጠረፍ በርሊን አልቀሬኙም

ሀረርሌ ዩቡርዲ አዱኘቤ ኤሉም

ሳፊእ ጀነቲንቴ ሺርቲዜ ዘራንዘር

ኡፋች ኪልበረሩ ያሾዛል ፈቀር

ወዘናም ጠር ዪልማ ያዳን ወለም ያሻል

ላይ ዩበስሊማ ቢሲም ቀብ ቀብ ይላል

ለፉም ዘው ዘው ይልማ ሐበሪም ዩረግፋል

ጌይ ዚቼኸልቲ አያም ያሲንቤ ቼኸሌ

ዘትቲዳመስ ኩታ ፋታሕቤ አቀሬ

መሰል  በርካታ ዘፈኖቿ አሁንም ይሰራል፡፡ አንዳንዶቹ ከግጥሙን ከመጠቀም  በቀር ውስጣዊ  ታሪኩን ለመረዳት ይ ከብዳል፡፡ ምክንያቱም ይህን የኖረችው እሷ በመሆኗ ነው፡፡ እንደ  ምሳሌ  ከላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ የተወሰኑ ስንኞችንም እንመልከት፡፡

ቆባ ኢፋጭሌ ሙሳፊሪን ሌጥኹ

ሚስራ ዋ ሮማ ለንደኑ ወረድኹ

ኢላ ጀርመን ጠረፍ በርሊን አልቀሬኹም

ሀረርሌ ዩቡርዲ አዱኘቤ ኤሉም

እኩያ ልፈልግ መንገድ ጀመርኩ

ከግብፅ እና ሮማ ለንደንም ሔድኩ

እስከ ጀርመን ጫፍ በርሊን አልቀረኹም

ለሀረር የሚደርስ በአለም ላይ የለም፡፡

ይህ እሷ በዞረኑ አለም የሔደችባቸው እና ትላልቅ ብላ የለየቻቸው ናቸው፡፡ ይህን ቀሪው ከግጥምነቱ ውጪ ለባለቤቱ አይጨነቅም፡፡ ምክንያቱም እሷም ባህል ነች ግጥሙም የህዝብ ነው፡፡

ደድ ዳና የጉብሪ - ደድ ሐረቅ ዩገዛል

ተረኸባ መሪኜ መለሳዮው - ራሕመቲን ዩዘልማል

ራሕመት አኑኽ ዶሪ ዱሪ በድሪ በሪ ወልዲ

ዘልፈርኹቤዋ በድሪ በሪ ውልዲ

ደዴም ሐረት ዳብሊ

አዝሊምለነ,ዌይ

በዚህ ግጥሟ ምትኖርበትን አከባቢና ከትዳር አጓ ሰፍር በመጥራት የዘፈነችው ነው፡፡

በዚች ታዋቂ ግሩም እናት መሐፀን አምስት ልጆች ያፈራች ሲሆን መልካም እናት እንደነበረችም ይነገርላታል፡፡በሙዚቃው አለም ከፍተኛ አድናቆት በማትረፏ የተለያዩ አጥኚዎች ወደ ሀረር በመምጣት ከሷ አንደበት በሰሙት ዜማ ተደንቀው በፅሁፍ፣በድምፅ፣በምስል አስቀርተው ሄደዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1965 በሐንጋሪያን መንግስት በ"Hangarian Acadamy of Science " ማእከል በReasrch center for Humanities institute for Musicology ከ55 አመታት በፊት በሀረሪ ክልል የሀረሪ ባህላዊ አጨፋፈር እና ሙዙቃ ላይ ባደረጉት ጥናት በመሪ ድምፃዊነት ስትጫወት የነበረችው የሀረሪ ባህላዊ ሙዚቃ ንግስቷ አይ ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ አልያም በመድረክ ስሟ ሻሚቱ ስትሆን በአጃቢነት ታናሽ እህቷ ረውዳ አህመድ አሊ ሻሚ ስትሆን በዚህ ጥናት 9 ባህላዊ ዘፈኖችን ተጫውታለች። በዚሁ ጥናት መሰረት ከሁለት አመት በኋላ በ1967 እ.ኤ.አ በጂዮርጂ ማርቲን ጥናት ተሰርቶ journal of the international Folk music council በ 19 volume ተዘጋጅቶ ለንባብ በቅቶዋል።

Gey fäqär, the songs of the City ? Voices of tradition and transition in Harar በሚል ርእስ በሻሚቱ የሙዚቃ ስራዎች ተደምማ ጥናት የሰራችው ጣሊያናዊቷ ኢላሪያ ሳራቶሪ ትገኝበታለች፡፡

ሻሚቱ ይህን ሙዚቃ ለወጣቶች ለማስተላለፍ ብዙ ብጥርም ፍላጎት ያላቸውን ለማግኘት አልታደለችም ነገር ግን ታዜምባቸው በነበሩት አርባ ስምንት አመታት ውስጥ በስተመጨረሻ አከባቢ በቀድሞ ቤቷ አከባቢ የነበረችውን አሚና አደም ታገኛለች የሀረሪ ባህላዊ ዘፈን በተናጥል ከሚዘፈኑት ውጪ በጋራ የሚዜም ማለትም አጃቢ የሚፈልግ ተቀባብለው የሚዜሙ ስላሉ አሚና አደም(ጊኒ) አብሯት በአጃቢነት ያዜሙ ጀመር፡፡

በእድሜ የሰፋ ልዩነት ቢኖራቸውም እንደጓደኛ ተቀራርበው ሻሚቱ በመሪ ድምፃዊነት ጊኒ በአጃቢነት መስራት ተያያዙት፡፡ ከሷ ቀደም እና በኋላም አልፎ አልፎ ከሚገጥሟት ጋር እንደነ ዘቢዳ አብዶሽ ፣አሚና አብዲ በጋራ ታዜም ነበር፡፡

ሻሚቱ ቀድሞ ብቻዋን ታዜም እና አድማጭ ያጅባት የነበረው አሁን በተሟላ መልኩ መስራት ጀመረች፡፡ሻሚቱ በተጠራችበት ቦታ ሁሉ ጊኒን እያስከተለች አብረው መስራት ጀመሩ፡፡ አዳጋች የነበረው የሻሚቱን ድንገቴ ግጥም አልያም ባለችበት ቅፅበት የምትቋጥረውን ስንኞች ተቀብሎ ማዜም ለጊኒ የዋዛ አልነበረም፡፡



ብዙም ሳይቆይ የግጥም አገባቡን ጊኒ ስለተረዳች የመጨረሻ የስንኙን ቃላት በመያዝ በመድገም ማጀብ ጀመረች፡፡ ይህ የሁለቱን ትስስር ያጠየናከረ ነበር፡፡ ሻሚቱ ከነበራት የግጥም ተስጥኦ ምክንያት ለወንዶች ሙጋድ(ቡድን) ሁሉ ሳይቀር እስከቤት እየመጡ ግጥም ታፅፋቸው ነበር፡፡

ልበ ብርሓኗ ሻሚቱ ደፍ እና ከረቡ(ከበሮ) አመታት ሚደርስባት አልነበርም ይባልላታል፡፡ እጇ የገባ ደፍ ራሱ መጫወት ይጀምርራል እየተባለ ትሞካሸች፡፡

ይህ ሁሉ ሰርግ ላይ ከተቀረፀ ድምጽና ምስሎች ብቻ በርካታ ስራዎቿ ስቀሩ፡፡ ጥቂቶቹ በሁለት አልበም ታትሞ መውጣት ችሎዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከአርባ የማይበልጡ ስራዎቿ በአውዲዮ ሲገኝ ጥቂቶቹ በምስል ይገኛሉ፡፡

በ1993 መጨረሻ አከባቢ ሁለተኛ ዙረት ጀርመን ሔዳ ስራዎቿን አቅርባ በተመለሰችበት ወቅት በጠና ታማ ነበር፡፡ በ1994 አመተ ምህረት እቺን አለም ላትመለስበት አሸለበች፡፡ የሷ መሞት የብዙኦቹን ልብ ያቆሰለ ከመሆኑ በተጨማሪ የሀረሪ ባህል ላይ እሷ ጎደለች፡፡ ከዚህም አለፈና የመስኖይ ዜማን ይዛው ቀብር ወረደች፡፡ ምናልባት የተቀዱ ድምጾችን ማፈላለግና ጥናት ማድረጉ ሳይበጅ አይቀርም፡፡

በህይወት በነበረች ግዜም ባህሉን ለማቆየት በ1981 ዓ.ም. የተወሰኑ ወጣቶችን ያስተማሩ ቢሆንም ከእውቀት ያለፈ ስራ ላይ ሳይውል ቀረ፡፡ መሞቷን ተከትሎ ለህዝብ ታዜምለት በነበረችበት አሚር አብዱላሒ አዳራሽ ፎቶዋን ከመስቀል ውጪ ያተረፈችው ነገር አልነበረም፡፡የሷን ዋጋ የተረዱ ጥቂት አርቲስቶች ለሷ አዜመዋል፡፡ እንደነ አርቲስት ከሊፋ ኡመር እና አርቲስት አዲብ አብዶሽ ያሉ ዜማ ተቃኝተውላታል፡፡በአሁኑ ጊዜ የሻሚቱ አጃቢ ድምፃዊ የነበረችው አሚና አደም(ጊኒ) የሻሚቱን ዙፋን ወራሽ ሆና የሀረሪን ባህል ህይወት እየዘራችበት ትገኛለች፡፡

በርካታ ወጣቶችን እያስተማረች ባህሉን እንዳይሞት እየታደገችው ትገኛለች፡፡ ይህቺ የዲሚሽ ንግስት ዛሬም ስራዎቿ ይጣራሉ ተጠንተው የማያልቁ ልብን የሚነኩ ግጥሞቿ እየተዜሙ እሷነቷን ህያው ያደርጉታል፡፡ ሁሌም ልትዘከር የሚገባ የሙዚቃ እናት አይ ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ(ሻሚቱ)

# ፋ. ስስ ዘፎን ክብተዘፎኑ እና ክብተባሉት የስንጂ ቋጠሮ

1. ፈቀር ዩሰበራል - አኻኽ ቲሰበሬኽዋ

   ዘይቲሰበር ጊዲር አያት ቁርአንዋ

2. ፈቀር ቦዝ ቦዝ ያሻል - ቁፉል ጋር የትኪፍታል

   ዚጦኘዞ - ዚኜአው የናሕቃል

3. ፈቀር ዩሰበርበኝቤ - ቆበዬ ዩሲሕቂበኝቤዋ

   ሳሳ ወሲፍ አንገቴቤ የንበርበኝ

4. ፈቀሩ ማንባሕ አሻ - ጋሩ ማንባሕ አቢርና

   መሪኜ መለሳይ ጋር ኦናን ኻና

5. ፈቀር ዘሌላ ኤልዋ

   ፈቀር ዘሌላ አሳሲን ኤላዋ

6. ፈቀሮው መብሉሎው - ዩትኼተሉሜልዋ

   ከዛሹቦ አትታይቤ ዩቀራልዋ

7. ፈቀር ቁርአን ዩነብሪጊር - መስላሕ ሱዋብ ዩነብሪጊር

   ከአን ኢሳሸኹሎመ ከሸዲ ዋ መዲ

8. ፈቀር ጊዲርንታ

   ዩቃዛልሌ ዘይቲሐደግንታ

9. ፈቀር ጊድረዞሌ - አወል ኡሱኽ

ኪታቤን ከተቤው

10. ዚጋል አቱሹና

ፈቀር ዘዩቅ ኡሱኽ ዚጋል ያሻልዋ

11. ፈቀሩ ነኽ ሲማኽ

ካፊር ዊጅ አዛኑው ኢመይሲማኽ

12. አሸኔው ፈቀር - አላሸኔዉም ፈቀር

ኢኝኛ ዛልባች ሴናዞ ኤልበናም

13. ፈቀርሌ ጋር ኤላ - ጋሩም ኤላ

ዲክካ ወገር ኤላ

14. ቲሰሞው ሲመአኝ - ደርመነትቤ

ፈቀሩ አሸኔው ናረዌይ

15. ፈቀር የንቃሕቀኛል

ሩማን ሐበሪኩት የርጋግፈኛል

16. ፈቀርሌ ሚን ሐላዋ

ሞሸዞሌ ሔጅ አሐዱም ኤላዋ

17. ፈቀር ዜገሎሰአ ዩላል ፈረት ፈረት

ዜገሎ ቤሔርሌ የትቢሉሜል ሒራት

# ተዛማች (ግርጽፍ) ትርጉም

- ዘፈን ዪሳሳታል - አንተ አትሳሳትም

  የማይሳሳት ትልቁ ህያው ቁርአን

- ዘፈን ዪወሰውሳል - የተዘጋ ቤት ያስከፍታል

  የበለጠው የተኛን ያነቃል

- ዘፈን ከሚበላሽብኝ - እኩያዩ ከሚስቅብኝ

  ሰላሳ ሰይፍ አንገቴ ላይ ዪኑርብኝ

- ዘፈኑን ከማንጋ ልዝፈነው ቤቱን ከማንጋ ላብራው

  የጓደኛዬ የጀግናው ቤት ባዶ ሆነ

- ዘፈን የሌለው የለም

  ዘፈን የሌለው መሰረት የለውም

- ዘፈን ብልሹ አይከተልም

  የዘፈኑበት ቦታ ቀሪ ነው

- ዘፈን ቁርአን ቢሆን ኖሮ - ጭፈራ ፅድቅ ቢሆን ኖሮ

  እኔ እጫወተው ነበር አሳምሬ አስውቤው

- ዘፈን ክቡር ነው

  ለሚያውቀው የማይተው ነው

- ዘፈን ለክብሩ የድሮ ሰው

በመፀሐፍ ፃፈው

- ጥፋተኛ አታድርጉን

ዘፈን የማያቅ ጥፋተኛ ያደርጋልና

- ዘፈኑን ናና አድምጠው

ሐይማኖት የሌለው ልጅ አዛን ከመስማቱ በፊት

- ዘፈነው ዘፈን - ካልዘፈነውም ዘፈን

እኛማ ፀፀት የለብንም

- ዘፈን ቤት የለውም - ቤትም የለውም

ቤትና ምሶሶ የለውም

- ለዘፈን ዘፋኞች - ጆሮ የበሱ

ሶሪ ዙሪያ ለዴቢስ ጓደኞች

- የምሰማውን አድምጠኝ - በጉርምስናዩ

ዘፈንን ዘፍነው ነበር

- ዘፈን ያነቃቃኛል

እንደ ሮማን አበባ ያራግፈኛል

- ዘፈን ምን አለውና

ለመዝፈን ተመልከት ምንም የለውም

- መዝፈን ሲጀምሩ ይላል ፍርሐት ፍርሐት

ከጀመሩት በኋላ አያስበላም እራት

# ፩. የሀረሪ ሙዚቃ እና የታሪክ ቁርኛት

የሀረሪ ሙዚቃ አመሰራረቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ የታሪክ አሻሮች እንዳይረሱ ቅኔ በተላበሰ መልኩ በሙዚቃዊ ስልት በዘፈን፣በመዝሙር፣በልጆች ጨዋታ ውስጥ ተካተው ለትውልድ ይሸጋገራሉ፡፡ ይህ በጽሁፍና በታሪክ ድርሳናት ያልተካተቱና የተካተቱትን በማይጠፋበት መልኩ ለሁሉም ግልጽ ባልሆነ መልኩ ለብሔሩ ተወላጆች በሚታይ መልኩ በግጥምና ዜማ ተከሽነው ይሰራሉ፡፡ በቀዳሚነት የምናገኘው በግጥምና ዜማ የተሰሩ በልጆች ጨዋታ ውስጥ የተሸሸጉ እውነተኛና አፈ ታሪኮች በርካታ ናቸው፡፡

“አቤው ሒባበሎማ

ሰሪ ቆጥ አሴቀሎማ

<ካፊር> ጋሩ ማገዶማ

ጂን በቀል ሼለሞማ

ነይ ሑቡል ሑቡል ሚጣድ ሱቡር…”

(ዚሀረሪ ዊጃች መትፌቀር ፈይሰል አብዲ ሑሴን 1999)

የዚህ ግርድፍ ትርጉም፡-

“እንትናን አባበሉትና

ተራራ ጫፍ አወጡትና

የእርኩስ ቤትን አቃጠሉት

በተደበቀ(የሰይጣን) በቅሎ አሸበረቁትና

ነይ እያሉ ማባበል ማባበል ምጣድ መስበር ነው”

እያለ ይቀጥላል በዚህ ግጥም ውስጥ እንደ አፈ ታሪኩ አገላለፅ ይህ ታላቅ ወንድሜ ተብሎ የተገለፀው ከ1856-1856 ሀረር ላይ ነግሰው የነበሩት አሚር መሐመድ ቢን ገራድ አሊ ቢን አብዱሽኩር መሆናቸው ይነገራል፡፡ እኚህ የሀረር አሚር ህዝቡን ክፉኛ የበደሉ መሆናቸው ይነገራል፡፡ በዚህም ምክንያት ህዝቡ የግብፅ ድጋፍ አሰባስቦ ወደ ሐረር እንዲገባ በማድረግ የንጉሱን አሟሟትና ቀጣይ በሀረር የተፈጠሩትን ሁኔታዎች እየተረከ እንደሚሔድ ይነገራል፡፡ (ከቢር አብዱልሙየሚን አብዱናሲር 1999 ቃለ መጠይቅ ላይ የተወሰደ)

በሌላ አፈ ታሪክ ቀጥታ ከልጅ እያሱ ጋር ያስተሳስሩታል፡፡ በዚህ አፈ ታሪክም ልጅ እያሱን ስልጣን ከሰጡት በኋላ ከዱት ሲሆን "ጂን በቀል" በ1902 ዓ.ም ሀረር የገባችውን መኪና ለመግለፅ ነው ይላሉ፡፡ሑቡል ሑቡል ሚጣድ ሱቡር" እያባበሉት እንደካዱት ያሳያል ይላል፡፡ (ፌሰል አብዲ 1999 ዚሀረሪ ዊጃች መትፌቀር) ከዚህ ውጪ ሑሉም ማለት በሚቻል መልኩ የልጆች ጨዋታዎች ታሪክን፣ማህበራዊ መስተጋብሮችን እያንዳንዱ ቢፈተሽ ጨዋታዎች ላይ የሚጠሩ ስሞች እውነተኛ ሆነው ድርጊቶቹ አለ፤ያም ተደራሲን የጋሐዱ አለም ነፀብራቅ ሳይሆኑ እውነተኛ ምስሎች(ገፀ ባሕሪ) ናቸው:: በሌላ በኩል ከማህበራዊ ትርጓሜዎች ባሻር የፖለቲካ ቅኔዎችን በተማሪዎች እና በመዝሙሮች ተሸሽገው የሞራል ግንባታ የማንነት ፍቅር ሐይማኖታዊ ኡደት እንዲፈጠር ሲደረጉ ከርመዋል፡፡ይህም መሆኑ የሀረሪ ሙዚቃ ጠለቅ ያለ የታሪክ ፣ባህል፣ወግ፣ልማድ፣ወዘተ....ኡደት ያለው መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡እንደምሳሌ ሆኖ እንዲረዳን አንዳንድ ግጥሞችን ያለፈውን፣ያሁኑን፣የወደፊቱን፣ይሳሉበትን የሙዚቃ ግጥሞችን ስንመለከት ይህን ይመስላሉ፤

በ1879 ዓ.ም በጨለንቆ ጦርነት ለተሰዉ ሰመኣታት የተሰነኘ የስንኝ ቋጠሮ፡-

“ጨለንቆ ሚይ ቢርቅቤዋ

ኢር ሰወርዋር ዚፄረረቤዋ

ኢንደርቢው ሚይን መሰሌውዋ

ቲእዞው አግሪ ዛሻ ጢርራም አላደቄውዋ

ኢሕዞው ዋይ ዱፉን ሜታን አደቅታዋ”

## ግርድፍ ቱርጉም

“የጨለንቆ ውሃ ቢያብረቀርቅ

የፀሐይ ጨረር ከርሮ ቢወብቅ

ተራራና ሸንተረሩን ያቆራረጠበት

እንደራብን ውሃ መስሎት

ደረቱን ጋሻ አድራጊውን ጥም አልጣለውም

የወንድሙ ጩኸት አጠቃላይ ሜታ ነው የጣለው” (የሀረሪ ህዝብ ፀረ ጭቆና ትግል አዩብ አብዱላሒ /2003/)

“ ዲል ሞሻ ቀረቤሻ
ድል ማረግ ቀረብሽ

ጎንደርቤ ዚዲጃ ወረሴሻ”
ከጎንደር የመጣ ወረሰሽ

የጨለንቆ ጦርነት ላይ የሜታዎችን ሽፍጥ ለመዘከር የተሞከረበ ት ነው፡፡

በ1960ዎቹ ላይ ስንደርስ የ”አመሽና” እና የ”ኩሉብ” ትግል ላይ ለተሰዉና ለሚሰዉ የተባለ

(ኩሉብ እና አመሽና ቀዳሚ የሀረሪ ብሔር የታጋዮች ቡድኖች ናቸው)

“ሰውዋር መለሳያች

ሶውረሌ ጪንጬሕቤ ዞደቃች

ቲትረሰኡሜኹ ቲትቄቀላኹ

ሐቅ ኡጋ መኽቱታች

ታሪኽ ተዳሪማ ተፈትሊማ ሱምኻው

ሐቁም ቲከልሃት ሱምዋ ዲላገኻው”

“ታጋይ ሰመአታት

ለትግል ታግላችሁ የወደቃችሁ

አትረሱም ትታወሳላችሁ

የእውነት መንገድ ብርሐኖች

ታሪክ ታድርና ፈትላ ስምህን

እውነትም ትጣራለች ስምና ስራህን”

በተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የፖለቲካ ፣በአገር ንቅናቄ፣ በህዝባዊ አመፅ፣በውስጣዊ እንቅስቃሴ በአንዱ ዘመን እንዲህም ብለው ነበር፣

“ባድ ዘሌላ መሃዱም ኤልዋ

መሓድ ዘሌላ ባድ ዩዋሬልዋ

ጪንጫሕ ቢላይ ባዱም ዩኹኔልዋ

ሑርሪያ ቢላይ ባዱም ዩኒሩሜልዋ

ኺላፍ ቢላይ ሌቆቱም ኤልዋ

ገልጌብ ቢላይ ኪሕሊ ዩትረኸቤልዋ

ዲሞቅራጢ ቢላይ ዊጥኒ ዚቅ ዩሉሜልዋ

ዊጥኒ ቢላይ ሶውራም ዩነጅሔልዋ”

በ1980ዎቹ ለነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄ እና መፈንቀለ መንግስት በመደገፍ የተለያዩ ሐገራዊ እንዲሁም ሕዝባዊ ማነቃቂያ የሚሆኑ ሙዚቃዎችም ተሰርትው ነበር፣

“ሐፍ በሉ ሐፍ በሉ አልለኾሌ በሉ

ሐፍ በሉ ሐፍ በሉ ወልዳችኾሌ በሉ

ዚዳመስቲ ጌዩ አሓድነትቤ ቼኽሉ

ሱምኾ አይቲጠመስ ዋትና ሓልና በሉ

ኢማም አሕመድ ዘማንቤ ዚቼኸልቲ ባድ

ሚኒሊክ ወልዳችቤ አሹቡና ዘልባድ”

ተነሱ ተነሱ ለአልላሕ በሉ

ተነሱ ተነሱ ለልጆቻችሁ በሉ

የፈረሰችዋን አገር ባንድነት ገንቡ

ስማችሑ አይጥፋ አለን በሉ

በኢማም አሕመድ ዘመን የተገነባች አገር

በሚኒሊክ ልጆች አረጉብን የባእድ አገር (ሀረሪዎች ሐረርን ከተማ ከማለት አገር ማለትን አብዝተው ይጠቀማሉ፡፡/ከቀድሞ አገር ስለነበረችና ከ1979 በኋላ የኢትዮጰያ አንድ ክፍል በመሆኗ ነው/)

ለዚህም መልስ የሚሆን አፀፋዊ ተጋብሮት እንዲሆን የወጣ የሀረሪ ዘፈንም ነበር፡፡ይሕ ደሞ ለወጣቱ መነሳሳትን ፈጥሮ ነበር፡፡

“ ሐፍ ባዥ ጠብ ባዥ ዚመድለግሌ ጌያ

አይዚኛ ሀረርሌ ታሪኽ መገስ ጌያ

አኑም ባባቼኩት ኡዥንለሽሌ ሽሒዳ

ሐቅዜው አቲሪሌ አይዚኛ ባዳ

አው አባዲር ጌዩም ቲዋርኩት ዚአበዳ

አይዚኛ ሀረርሌ አን ኡቡአኽ አሕዳ”

ተነሳሑ ተነሳሑ የመማሪያ አገር

ለናታችን ሐረር የታሪክ መናገሻ አገር

እኔም እንደ አባቶቼ ልሖንልሽ መስእዋት

እውነቷን ላሳይ እናት አገር

የአው አባዲር አገር እንድትሆን ሕያው

ለናታችን ሀረር እኔ ቃል እገባለው

በ1983 ዓ.ም ለተገኘው የነፃነት ድል መዘከሪያ ይሆን ዘንድ በ1984 ከወጡ የሀረሪ ዘፈኖች መሐከል አንዱን እንመልከት፣

“ዲሞቅራጢ ሽሓን ተስራጫ ኢትዮጵያቤ

ሐፍ ነል ነሌጥባ ቢሪኝ ዳንዲዞቤ

ወቅቲ ኢመዬሌጥበና ኩሽ ነል ሔረዞቤ

ደርመዋ ወሓቺ የትኺሻል ጪንጫሕሌ

ባባችኻኩት የውጣ ፊዳኽሽሌ”

አማርኛ ትርጉም

“የዲሞክራሲ ብርሐን ተሰራጨ በኢትዮጵያ

ተነስተን እንሒድበት በበራው መንገድ

ጊዜው ሳያልፍ እንንቀሳቀስ በስርአቱ

ወጣት ወንድና ሴት ያስፈልጋል ለትግሉ

እንደ አባቶቻችን መስዋት እንሁን ላንቺ”

ተብሎም ተቀነቀነ ሁሉንም በስነ ግጥምና ሙዚቃ ሲሰራም ከረመ፡፡

ሸዋል መፅሔት 1999

ይሑን እና ይሔን በመሳሰሉ የሙዚቃ ግጥሞች በወቅታዊ ሑኔታዎች ላይ ንቅናቄን እንቅስቃሴ መፍጠር ችለው ነበር፡፡ይህ የሚያሳየን ግጥም የትኛውን መንግስት የአስተዳደር ጊዜ ብሎም ያኔ የነበረውን ነባራዊ ሁኔታ በትዝታ ጎዳና ስለ እውነት እያወራን ለታሪክ ምስክር እንድንሆን አንድ አካል አድርጎናል፡፡

ሌላው እንደ ምሳሌ የምንወስደው ታሪክ አስረጂ ሙዚቃዊ ግጥሞች አፄ ሚኒሊክ፣ቀዳማዊ ኃይለስላሴ(ቀ.ኃ.ስ)፣እስከ መንግስቱ ኃይለማርያም የነበሩትን የጭቆና ዘመናት ሲዘከሩ ሲያወሱ እንመልከት፣

“ዘማነ ሱኩትዋ-ዘማነ ሱኩትዋ

ኢዛ ተከላምና-ኒኹና ኑሙትዋ”

የዝምታ ዘመን - የዝምታ ዘመን

ቃል ቢወጣን - ልንሆን ሙታን

“ጌይ ሲናን ኢንታዋ-ጌይ ሲናን ኢንታዋ

የሀረሪ ቋንቋ ነው - የቅኔ ቋንቋ ነው

አው ሓኪም ሰሪ አፍዞ ጩጉፍ ኢታታዋ”

አው ሀኪም ተራራ አፉ እስር(ጫካ) ነው

ይህም ማለት ከግጥሙ እንደምንረዳው መናገር አንችልም መብታችን ተረግጠዋል፣ለመናግር ጊዜው አይፈቅድም የሚል ጭፍን ቃል ይወርሳል፡፡

ንጉስ ሆነው በስድስት ወራቸው

ሰማይ ለሰማይ ዱሔዳል አቶሞቢላቸው

(በ1965 በኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ ከተዘፈነ የተወሰደ)

ያ - ኃይለስላሴ - ባንዲራንተ ዋሴ ( ኃይለስላሴ - ባንዲራ ነው ዋሴ) / ከአርቲስት አህመድ አቦበክሪ የተወሰደ)

በኃይለስላሴ ጊዜ የታወጀውን የሰአት እላፊ ህግን መሰረት አድረገው ለሰርግ በምሽት ይደረግ የነበረው የሙዚቃ ድግስ ላይ እንደ መዝጊያ የሚጠቀሙበት የነበረው ዘፈን፡-

“ሰአ ኻና አግቡኡና

ወቅቲም ኢመይኹን አሌጪና”

ትርጉም፡ “ሰአት ሆኖዋል ወደቤት እንሒድ

ጊዜው ከመሆኑ በፊት እንሒድ”

የሚል ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የባህል ዘፈን ሆኖ እንደቀረ አርቲስት አህመድ አቦበክሪ ለሀረር ጋዜጣ በ1999 ዓ.ም. በሰጡት ቃለ መጠይቅ ያስረዳሉ፡፡

እነዚህና የመሳሰሉ ታሪክ አስረጂ የግጥም ዘውጎችም ይገኙበታል፡፡ ታድያ እነዚህ ግጥሞች በሙዚቃ ሲዜሙ ቆይተው በአሁኑ ግዜ ለትዝታ ይዜማሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስንኙ እየተወሰደ በሌላ ዘውግ የሚሰራበት ሑኔታም ይኖራል፡፡

ዘፈን ለሀረሪዎች እንደ አንድ መተንፈሻ ክፍል ሲሆን ለሙዚቃ ያላቸው አቋም የሚመሰገን ነው፡፡ሀረሪዎች ሙዚቃን

ለፖለቲካ፣ለፍቅር፣ለሐይማኖት፣ለሀዘን፣ለብሶት፣ለጭንቀት፣ለ ትዝታ፣ ለናፍቆት፣ ወዘተ…ሲጠቀሙበት ኖረዋል፡፡ አሑንም ድረስ እንደ ቀድሞው ጎልቶ ባይታይም ይሄንኑ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተለይም ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ታሪክን፣ባህልን፣እንዱሁም ቋንቋን መሰረት ያደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የማንነት አብዮትን በሙዚቃ የሞራል መገንባትን የተጠቀሙ ህዝቦች ናቸው፡፡እዚህ ላይ በልዩ ሑኔታ ቦታ የሚሰጡትና የሚያበዙት የሙዚቃ ዘውግ የፍቅር ነው፡፡(ሀረሪዎች ለፍቅር ልዩ ቦታ አላቸው) የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት አቶ ውቤ ካሳዬ እ.ኤ.አ *March 2010 "THE SIGNIFICANCE OF HARARI MUSIC: THE CASE OF POP SONGS IN RELATION TO THE OBJECTIVES OF THE EDUCATION AND TRAINING, AND CULTURAL POLICIES OF ETHIOPIA"* በሚል African Study Monographs ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፋቸው በ17 የሀረሪ ፖፕ ዘፈኖች ላይ እ.ኤ.አ. በ2007 ባደረጉት ጥናት ከ135 ዘፈኖች ውስጥ የፍቅር ዘፈኖች 54.8%፣ በኢኮኖሚ በልማትና በባህል ዙሪያ 14% በአላት ላይ 9.6% በሀረሪ ባህል ላይ 8.9% በማለት በደረጃ ጥናታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

እዚህ ጋ ሊሰመርበት የሚገባው የሀረሪ ዘመናዊ ዘፈኖች ምንም ያህል ቢዘምኑ የብሔሩን ባህል፣ወግ እንዲሁም ታሪክና ስርአት ያልዘነጉ ሲሆን በእያንዳንዱ ዘፈኖች ውስጥ የሀረሪ ብሔር ሽታና ቃናው ይታይበታል፡፡

የሀረሪ ሙዚቃ ስንመለከተው ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከእምነት፣ ከፖለቲካ፣ ከአከባቢ ሁኔታ(ወቅታዊ ሁኔታ)፣ጋር እጅጉን ቁርኝት ያለው ሲሆን ከአንዱም ዘፈን ተነጥሎ አያውቅም፡፡ስለ ፍቅር በማዜም ሴትን ለማሞገስ ቢሹም ምሳሌም ሲያጣቅሱ ሐገርን፣እምነትን፣ወዘተ... ምሳሌ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡

| | |
|---|---|
| **ምሳሌ፡-** መካ ጋር አፊሬይ | ነለሺዋ |
| የመካ ቤት አፈር | ልበልሽ |
| አፊርሌም ሙሉሔይ | ነለሺዋ |
| ለአፈርም የተመረጠ | ልበልሽ |
| አይዜ ጪን ሐንቆቴይ | ነለሺዋ |
| የእናቷ ወገብ መቀነት | ልበልሽ |
| አውዜ ጋር አሳሴይ | ነለሺዋ |
| የአባቷ ቤት መሰረት | ልበልሽ |
| አይዜሌ ሰባቴይ | ነለሺዋ |
| ለእናቷ እርካ | ልበልሽ |
| አውዜሌ ሰላቴይ | ነለሺዋ |
| ለአባቷ ሰላት | ልበልሽ |

በንዲህ መልኩ ሴትን ልጅ ያሞግሳሉ፡፡

# ፊ. "ሙጋድ"(ቡድን)

አሁን ለደረስንበት የሀረሪ የሙዚቃ ዘመን ህያው ሆኖ ትውልድ ተሻግሮ ለትውልድ  የተወራረሰበት ትልቅና ዋነኛ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ የኖረው "ሙጋድ" አልያም (ቡድን)ነው፡፡ ይህ ሙጋድ ሊመሰረት የሚችለው በተለያዩ  ምክንያቶች   ሊሆን ይችላል፡፡ ሐረርና  በሀረሪ ብሔር በማንነት ጥያቄና በህዝቡ ሉአላዊነት የማይደራደር ስለነበር በርካታ የትግል ጉዞዎችን ቢያደርግም በታሪክ ሽሚያ እና ታሪክ በማጥፋት እንዲሁም ታሪክ በማጠልሸት በተለከፉ ሀረሪ ታሪክ እንደሌለውና ግንጥል ጌጥ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቶዋል፡፡በዚህም ምክንያት የትግልና የመስዋትነት ዘመኑ ሳይዘከር እንዲቆይ ምክንያት ሆኖዋል፡፡ በዚህም የትግል ጊዜያት ፊርማች፣ጀብሐ፣ኩሉብ፣አመሸና... ሲኖሩእንደምሳሌ  ልንወስዳቸው  የምንችላቸው  ሁለት  ድርጅቶች ይኖራሉ፡፡ ምክንያቱም ተመስርተው እንቅስቃሴ የጀመሩ ግንባር ቀደም አካላት ናቸው፡፡ሙጋድ ባይሆኑም ሙጋዶች በብዛት ለመመስረታቸው ትልቁን ሚና  ተጫውተዋል፡፡

## አነሱም፡-

6.1 - ኩሉብ ሐኖላቶ/ቡድን ለዘላለም ይኑር/1943-1947/

6.2 - አመሸና/አመሸን/1950-1987/

# 6.1–ኩሉብ ሀኖላቶ



የኩሉቦች ሰንደቅ አላማ

“ኩሉብ” ድርጅት ማለት ሲሆን “ሀኖላቶ” በጣልያንኛ ለዘላዓለም የኑር ማልት ነው እንደ ሞቶ ተገልግለውበታል:: ከቀድሞው በሜይ 1943 ከተመሰረተው የሱማሌ ታጋዮች የተገኘ ስለመሆኑ ይነገራል፡፡ የተመሰረተበት አላማ እና ምክንያት ቢኖር ግንቦት 2 ቀን 1879(በጀማዱል አወል 1304 ሂጅሪያ)ከአፄ ሚኒሊክ ጋር የተደረገው የውል ስምምነት ይከበር ብለው በጠየቁት መሰረት አጥጋቢ መልስ ሳይሰጣቸው መብታቸው በመረገጡ ሰበብ ነበር፡፡(አፄ ሚኒሊክ ሀረርን በያዙበት ጥር 8 ቀን 1879 ዓ.ም ከገቡ በኋላ ለሀረሪ ብሔረሰብ ቃል የገቡትን ለማለት ነው፡፡)/የሀረሪ አመፅ በአሕመድ ዘካሪያ 1992/ኩሉብ ሐኖላቶ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጭ አድርጎ ለመብት ሲከራከሩ፣ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ሆኖም በግዜው የነበረው ዘውዳዊ አገዛዝ የኩሉብን ትግል ለመግታት ባይችልም ለማዳከም ችሎ ነበር፡፡ ኩሉብ በኢትዮጵያ

የመጀመሪያውን ህዝባዊ የአደባባይ አመፅ ለመጀመር ግንባር ቀደሙ ሲሆን በርካቶች የተሰዉበት በርካቶች የተሰደዱበት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉበት የመስዋእትነት ጊዜ ነበር፡፡

ኩሉብ በቡድን የመደራጀት የሀረሪዎችን ባህል መሰረት በማድረግ በሕብረት የመስራት መንፈስን ወስደው ከሌሎች የሶማሌ ታጋዮች ጋር የታገሉ ናቸው፡፡



የኩሉብ ሐኖላቶ ታጋዮች በከፊል

## ６.２- አመሸና

አመሸና አላማው ከኩሉብ ጋር ተመሳሳይነት ነበረው፡፡ ነገር ግን ለመመስረቱ ዋነኛው ነጥቡ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ተማሪዎች “በቅርቡ ከሚጠፉ ቋንቋዎች መሃከል የሀረሪ ቋንቋ አንዱ ነው፡፡”መባሉ እየተናፈሰ የሀረሪዎች ጆሮ መድረሱ በ15 ወጣቶች በ1950 አመሸና ለመመስረቱ ምክንያት ሆነ፡፡ አላማው ቋንቋውን፣ ባሕሉን፣ማንነቱን ለማዳን በማሰብ የምሽት ትምህርት የተጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ትግሉ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ መሰረቶች ነበሩት፡፡እጅግ በርካታ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ በመላው ዓለም ተበታትነው የተለያዩ ድርጅቶችን መስርተው ለአንድ ዓላማ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፡፡



የአመሸና አባላት፡-

ታድያ እነዚሕ ድርጅቶች ሲመሰረቱ ለመብታቸው ስከራከሩ ለቋንቋቸው ህይወት ለመዝራት ሲሯሯጡ ሲታገሉ ዓላማቸውን የሚገልፅ የራሳቸው መዝሙር(ነሺዳ)እና ዘፈኖች ነበሯቸው፡፡ አዘውትረው ከሚዘምሩት ዋና መዝሙራቸውን ስንመለከት ይህን ይመስላል፡-

## ሎኽ ሸሐን መሐጤና

ያአላህ በሉ ተስቲንታዋ

ጎይቴ ዛዬው ቃነነዋ

ዬ አያም ኢር በዘዝቲማ ኑር ቤረነዋ

ተኼተሌ ሎኽ ኢንታዋ

ቢርናው ሔጁ አዲጄውዋ

ሊማይ ኡጋው አቤረኔውዋ ኑእ ነቤጃዋ

ስሙኡ ሙሃመድ ኢንታዋ

ኡጋ የቀንኩት ገፈረሌነዋ

ሸጥር ዚታ የሔስቢማ የር ፉኩሕዋ

ነመን ኑኡ ሑሉንታዋ

ኒኸሻ ዋቴ ሙሃመድዋ

ኢሊል በሉ ቢርና ኢር ኢንታዋ

ማልቱ ቢርና ኢሪንታዋ

ኑ ኢጂዞ ዘጋሕ ሙሀመድዋ

ኢሊል ነል ኩሉዚኛም ዋቴ ቃነነዋ

ሳላሙቱ የንበርባዋ

ላሉ ቢላይ አመኔውዋ

ኺንጋ ዚታ ሙሃመዱው ኢኛች ተራኤነዋ

ወደ ታች ሲነበብ “ያ ጎይተ ቢሊስ ኡሸነ ኒኢማኑ ኢሳለኺ”(አምላኬ ሆይ ነፃ አድርገን የሚሳንህ የለም)የሚል ትርጉም አለው፡፡

# 7. ሙጋድ እንዴት ይመሰረታል? ፡-

ሙጋድ ሲመሰረት እንደየ አላማውና አቋሙ የራሱ የሆነ የአደረጃጀት መንገድ አለው፡፡ ይሄም ማለት በእድሜ፣በትምህርት፣ አንዳንድ ቦታ ላይ በፆታ ፣ይመሰረታል፡፡ ሲመሰረቱም እንደ ምስረታው አንድ አይነት አቋም አልያም መሰረት ያላቸው ሰዎች ይመሰርቱታል፡፡ ሙጋድ የሚመሰረተው በሚከተለው መልኩ ይሆናል፡፡

- ዊጃች(ልጆች)
- ጉድጉዳች(ኮረዶች)
- ዋዬል (ጎልማሶች)
- ወደልላች (ጎረምሶች)
- ራጋች (ሽማግሌዎች)
- ኢያች (እናቶች)
- አዋች (አባቶች)
- አዜባች (ወጣት ሴት እና ወንድ)
- መርሪኘኛች (ወንድ ጓደኞች)
- ጌላች (ሴት ጓደኞች)
- አፎቻች (እድሮች)
- አሕሊ (ዘመድ)
- ጀማአ (አንድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች)

በዚህ አደረጃጀት ውስጥ በፍላጎታቸው አደረጃጀቱን ወደ ሙጋድ ሊያሳድጉት አልያም ከነዚሕ አደረጃጀት በተጨማሪነት ተሰባስበው ሙጋድ ሊመሰረት ይችላል፡፡ይህ ሙጋድ ሲመሰረት ለዘፈን ብቻ ሳይሆን ሙሉ የኪነጥበብ ዘርፉን የሚዳስስ ሊሖን ይችላል፡፡ከኪነቱም አልፎ የማህበራዊ መስተጋብሮችን መሰረት በማድረግ በአጠቃላይ ለተለያዩ አላማዎች ሊመሰረቱ እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም፡፡

**የቀድሞው ማለትም በ18ኛው ክፍለ ዘመን የሙጋድ ውስጣዊ አደረጃጀቱ ሶስት(3) ክፍሎች ነበሩት እነሱም፡-**

1 - አድል

2 - ዴቢስ

3 - ዲርሲስ በመባል ይታወቃሉ፡፡

እነዚህ የአደረጃጀት መዋቅሮች ላሉ የስራ ክፍፍሎች ለደረጃ እንዲሁም ቀድሞ የገባ ዘግይቶ የገባውን እንዲሁም የተሸ ብቃት ያለውን አለፍ ሲል ስራዎች የሚሰሩበትና የሚቀርቡበትን ለመከፋፈል ለመመደብም ይጠቅም ነበር፡፡በአሁኑ ወቅት እነዚህ የሙጋድ መዋቅሮች አይሰራባቸውም፡፡ምክንያቱም በብዛት በቀድሞው አደረጃጀት ለጦር አከፋፈልና ለወታደራዊ አደረጃጀት ይጠቀሙት ስለነበር ነው፡፡(ከቢር አብዱልሙሔሚን አብዱናሲር 1999) በአሁኑ ግዜ የሚገኘው የሙጋድ አደረጃጀት መዋቅር እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ልዩነት አላቸው፡፡ይሄም መሆኑ ቀድሞ ለነበረው የሙጋድ አመሰራረት ስርአቱን አሁን ካለው ጋር ለመቀላቀልና ለመበረዙ ምክንያት ሆኖዋል፡፡

# ፬.ቀደም ብለው የተመሰረቱ ሙጋዶቹ

ሙጋድ ሲመሰረት ብዙ ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡ስለሆነም የኪነት ሙጋዶችን ስንመለከት እውነተኛ ፍቅርን፣ሐገርን፣ሙዚቃን ብለው ሙጋድን ይመሰርታሉ፡፡አልያም ሙጋድን ይቀላቀላሉ፡፡ታድያ በ19ተኛው ክፍለ ዘመን እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተመሰረቱ ለአርቱ ትልቅ ውለታ የዋሉና ተፅኖ ማሳደር የቻሉ ሙጋዶችን ስንመለከት እጅጉን በርካታ ሲሆኑ በራስ ተነሳሽነት ባህል ሐገሬን ፍቅሬን ሙዚቃን ብለው ሙጋድን ህይወት ሲዘሩበት ታይቶዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ በጥቂቱ የሚከተሉት ይጠቀ ሳሉ፡-

1. ሒላል (ድሬደዋ)

2. ሒላል (ሀረር)

3. ሒላል (ደደር)

4. ሒላል(አዲስ አበባ)

5. ዴቢስ (ሀረር)

6. ደድ ኩሙል (ድሬደዋ)

7. መሕቡባች (ሀረር)

8 .ሐይዋን (ሀረር)

9. ሸባብ (አዲስ አበባ)

10. መስኮብ (ሀረር)



ደድ ኩሙላች



አዳ ቄረሆት ሙጋድ




አዳ አንግጊስ ሙጋድ



ጨለንቆ ሸሒዳች መትቄጠብቲ ሲነት ሙጋድ




ዳሚዱስ (አሺቃች ሙጋድ)

11 .መምዱሕ (ሀረር)

12. ፈዋዝ (ሀረር)

13. ፈናን (ድሬደዋ)

14. አይፋር

15.  ሊባሕ

16 .ነቢል

17. ሸነን

18. ረኢስ(ሀረር)

19. ፋሪስ(ድሬደዋ)

20. ማሕፉዛች(ሀረር)

21. መርኡስ

22. BATAS

23. የመን

24. YABS/ሳታች(ድሬደዋ)

25. UF13(ሀረር)

26. ኮከባች(ድሬደዋ)

27. ሚስራቅ ኮከባች(ድሬደዋ)

28.አዲባች(ድሬደዋ)

29.ሸኑስሳች

30.አሺቃች/ ዳሚዱስ(ቶሮንቶ ካናዳ)

31.LA BAND(U.S.A)

32.መለሳያች

33.መስኖይ

34. ፈዘላች(ሀረር)

35. ሒጋኝ

36. ሀረሪ ባንድ

37. ሲሳች

38. TOP 10

39. 79




LA BAND






ሐብሉል ሙጋድ




ኦዳ ኦንግጊስ ሙጋድ

40.ሲቆ

41.ናዲር

42.ሰባት

43.ሐያታች(ሀረር)

44.ሙሉካች

45.ዘቢባች

46.ማውርዳች




ሻሚቱ

47. አዜባች

48. ማሊካች

49. ሔናች

50. ሌይማናች(ሐረር)

51. ሺሽታች(ሐረር)

52. ሻሚቱ(ሐረር)

53. ነድሪያች(ሀረር)

54. ሐይዘራች(አዲስ አበባ)

55. ኢቆት ሲነት አዜባች ሙጋድ(አዲስ አበባ)

56. ሀረር ባንዲያች 2

57. ኦር ዳንዲ መዚቃ ሙጋዳች(ሀረር)

58. አዳ ጋር ሙጋዳች(ሀረር)

59. ቡቂሳች

60. ፋሽኮአች

61. ፈጫሳች

62. ሊብናናች

63. አፍሪካች

64. ፈጫስ አቦበክሪያች

65. መስፍናች

66. አደላች

67. ሎንዶናች

68. ሰዴታች

69. አይፌራች

70. አንዋራች

72. ፈናናች

73. ቁንሱላች

74. ኻሊሳች

75. ቱምሱላች

76. ቱፋሐች

በአሁኑ ግዜ ከሚገኙ ሙጋዶች መሐከል ጥቂቶቹን ስንመለከት፡-

1. ሳይ ቤሳይ (ሀረር)

2. ኩማማ (ሀረር)

3. ሳትቲ በቅልላ (ድሬደዋ)

4. ሒጋኝ (ሀረር)

5. አማና ቄረሖት (ሀረር)

6. ሐብሉል ሙጋድ (አዲስ አበባ)

7. ጨለንቆ ሸሒዳች መትቄጠብቲ ሙጋድ(ጨለንቆ ሰመኣታት መታሰቢያ ሙጋድ)(ሀረር)

8. ኣዳ ኣንግጊስ ሙጋድ/በሀ/ባ/ቅ/ቱ/ቢሮ ያደራጃቸው(ሀረር)

9. the adus brothers

በዚሕ መሰረት ከላይ ከተዘረዘሩት ሙዳድ አልያም ቡድኖች(ኪነቶች) ውስጥ 28ቱ የሴቶች ሲሆን 16ቱ በሁለቱም ፆታ የተደራጀ ነው፡፡ ቀሪው 41 በወንዶች የተመሰረተ ነው፡፡አምስት ከኢንግሊዘኛ የተወሰዱ ስያሜዎች፣አንድ ሱማለኛ፣አንድ ከቁጥር የተወሰደ ስያሜ፣አምስት የኦሮመኛ ስያሜዎች፣አራት አማርኛ ስያሜ ያላቸው፣ሁለት የአገርና አንድ የአጉር ስያሜ፣ቀሪው ከአረበኛና ከሀረሪ ቃላት(ስሞች) የተገኙ ናቸው፡፡(አብዛኛዎች በሀረሪ እና በአረበኛ ተመሳሳይ ትርጉምና የጋራ ቃላት አልያም ስያሜዎች ናቸው፡፡)

ከተጠቀሱት በቀር መረጃ ለማግኘት ባለመቻሌ ያልተጠቀሱ ለመቁጠር የሚዳግቱ እጅግ በርካታ ሙጋዶች ሳልጠቅሳቸው አልፌአለሁ፡፡ሙጋዶች ከሙብዛታቸው የተነሳ በአምስቱ በሮች ተከፋፍለው አርጎበበሪ፣አስሱሚይ በሪ፣በድሪ በሪ፣አስመአዲን በሪ፣ሱጉጥአጥ በሪ ሙጋዳች እየተባሉ በአከባቢያቸው ጠቅለል ተደርገው ይጠሩ ነበር፡፡

በነዚህ ሙጋዶች ያልተዳሰሰ ርእስ እና ሙዚቃ የለም፡፡የሁሉም ሙጋድ መሰረቱ ሀረሪ ይሁን እንጂ የሁሉም ብሄር ዘፈኖች እንዲሁም የባሕር ማዶ ዘፈኖች ለምሳሌ፡-ህንድ፣ ቱርኪሽ፣ የመኒ፣እንግሊዘኛ፣ሙሉ አረበኛ፣ወዘተ...ይዜሙ ነበር፡፡ታድያ ልብ ማለት የሚኖርብን በቀድሞው ሙጋዶች ውስጥ 97%የሚሆኑት የተለያዩ የሙዚቃ መሳርያዎችን አቀላጥፈው መጫወት ይችሉ ነበር፡፡(የሙዚቃ መሳሪያ ለመጫወት ካላቸው ጉጉት በተጨማሪ ለሙጋዱ አስፈላጊ በመሆኑም ምክንያት ነው)



To Raria 08/03/05

The Mugads of Harar

• Read Durri Mohammed's on the topic Rembard Har.

• Here are some names I've known since my adolescence both of Men & Women.

I - Men's:- chronological

• Imam
• Likah
3 Aifir
• Mallir
• Afrique
6 - Londan

• Amsal
• Masfin
9. Hilal
• Mahbool
• Anwar
12 Ra'eey

• Star
• Fawwaz
• Yemen /Ahmad
15. Mahfuz
• Hi-waan
• Hi-wan Harag
18 Venus.
• Nabil
• Nadir.

II - Women's:-

• Khalir
• Tunsal
3. Zabib
• Hayat
• Naluk
6 Sokat

• Laiman
• Mawardaah
9 Azeb
• Tuffah Qualawah

N.B.— Lagah
• Sisaeh
• Sigo
3 Fafa
• 72
• Top 10

8/3/5

የከቢር አብዲ (ከቢር አብዱልሙሐይሚን አብዱልናስር) የሙጋዶች ስም ዝርዝር በእጃቸው የተፃፈ ማስታወሻ

# ፩.1 ሐላል ሙጋድ

በሐረር  በአቶ ቡሌ አህመድ ዱራር አማካኝነት በ18 ሀረሪዎች የተመሰረት ኪነት ሙጋድ ነው፡፡ በድሬደዋ፣ ሀረር፣ ደደር፣ አዲስ አበባ፣ቅርንጫፍ ከፍቶ ሲሰራ ቆይተዋል፡፡ ታድያ ይሄን ሙጋድ ምን ልዩ ያደርገዋል ልትሉ ትችላላችሁ፡፡

ለመጀመርያ ግዜ በምስራቅ ኢትዮጵያ በሙዚቃ መሳርያ የተደራጀ የመጀመርያው ኪነት ቡድን ነው፡፡ከዚህም ውጪ ለሀረሪ ሙዚቃ ተፅኖ መፍጠር የቻሉና በግንባር ቀደምትነት ለመጀመርያ ግዜ የሀረሪን ሙዚቃ በ1955 ዓ.ም. ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ከተገመገመ በኋላ በኢትዮጵያ ሬድዮ ለመጀመሪያ ግዜ የሀረሪ ብሔረሰብ ዘፈን ያስዳመጡ ኪነቶች ናቸው፡፡ ዘፈኑን የተጫወተው አርቲስት አሊ መሐመድ ወርፋኸ ሲሆን በአጃቢነት አርቲስት ቡሌ አህመድ ዱራር ነበር፡፡

(ሐላል፣ፈናናች፣ፉርሪሳች አንድ ላይ በመሆን እና በመቀላቀል “ደድ ኩሙል ሙጋድ”ብልው አዲስ ሙጋድ መስርተው ነበር፡፡)

ስለ ሐላል ሙጋድ ይህን ያህል ካልን 18ቶቹ እነማን እንደሆኑ ከዚህ በታች የሐላል እና የጥቂት ሙጋድ አባሎች ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቦዋል፡፡




ሒላል ሙጋድ አባላት ፎቶ

# ሒላል ሙጋድ አባላት ስም ዝርዝር

1. ቡሌ አህመድ ዱራር(ሀረር)
2. አሊ መሃመድ ወርፋ(ድሬደዋ)
3. ኢብራሂም ወርፋ(ጀርመን)
4. ሳሊህ ሱፊያን(አዲስ አበባ)
5. አህመድ ጊዴያ(አዲስ አበባ)
6. አህመድ ከቢር(ባቢሌ)
7. መሀመድ ሳሊህ(ባቢሌ)
8. መሃምድ ኢብራሂም(አዲስ አበባ)
9. ዩሱፍ አብዱልዋሲ(ጂግጂጋ)
10. ሱፊያን ኡመር(ጂግጂጋ)
11. ሐምዛ ሐጂ(በሒይወት የሉም)
12. ዩሱፍ ሸሪፍ(አዲስ አበባ)
13. አብዱልላሂ ኡስማኢል(ሀረር)
14. ካሚል አብደላ(አሜሪካ)
15. መሃመድ ሁሴን(ሀረር)
16. አህመድ ሱርሪያ(አዲስ አበባ)
17. ሱፊያን ኡመር(ሀረር)
18. ጣሒር ሸሪፍ

(ሒላል፣ ፊናናች፣ ፋርሪሳች አንድ ላይ በመሆን እና በመቀላቀል “ደድ ኩሙል ሙጋድ”ብለው አዲስ ሙጋድ መስርተው ነበር፡፡)



ከቀኝ ወደ ግራ አሊ መሐምድ ወርፋኽ፣አህመድ ጊደይ፣ቡሌ አህመድ ዱራር

## 8.2 ማሕፉዛቹ ሙጋጽ፡-

ከ50 አመት በፊት የተቋቋመ የወጣቶች የኪነት ቡድን ሲሆን ልክ እንደሌሎች ሙጋዶች በሙዚቃ የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላለፍ በወቅቱ ለነበረው ጭቆና የራሳቸውን አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡ማሕፉዛች ሙጋድ ሙዚቃ በሚጫወቱበት ጊዜ ፖለቲካዊ መልዕክት ሲያስተላልፉ ይታሰሩ ስለነበር በተለያዩ ዘፈኖችና በግጥሞቻቸው ውስጥ በማካተት በተዘዋዋሪ የጭቆና ትግል ሲያካሔዱ የነበሩ የኪነት ቡድኖች ናቸው፡፡

ይህም ቡድን ልክ እንደሌሎቹ መሰብሰብ ክልክል በነበረበት ወቅት በሙዚቃ የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላፍ አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡

## 8.3 ፈዘላቹ ሙጋጽ

ፈዘላች ሙጋድ በቤተሰብ ስያሜ የተመሰረቱ የሶአስት ወንድማማቾች ሙጋድ ሲሆን ለኪነቱ እጅግ የማይረሳ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱና በጊዜው ዘመናዊ ከሚባሉ የሙዚቃ አይነቶች ተርታ መመደብ የቻሉ ሲሆን ለበርካታ ሙዚቀኞች በር የከፈቱ እንዲሁም መነሻ ሊሆኑ የቻሉ አርቲስቶች ናቸው፡፡ድምጻዊት ሐመልማል አባተ የተጫወተችው የሀረሪ ዘፈን “ሚይ በረድ ሚን ያሻል” የሚለው ዘፈን ባለቤቶች እኚህሁ ናቸው፡፡



# ፬.4 አዲባቹ ሙጋድ ፡–

- በድሬደዋ ከተማ ከ45 አመት በፊት የተቋቋሙ ሙጋዶች ሲሆኑ በዘመኑ ሴቶች ከሀይማኖታዊ ትምህርት ውጪ እንዳይማሩ ተፅእኖ ስለነበር፤ ይህን ተፅእኖ አስወግደው አመሸና በተሰኘው ንቅናቄያቸው ሴቶች ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ የራሳቸውን አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡

# ፬.፭ ሐይዋናቱ ሙጋጽ፡—

- በሐረር ከተማ ውስጥ ከ45 አመት በፊት የተቋቋመ ነው፡፡ሐይዋኖች ሙጋድ የድሮ እና ዘመናዊ ዘፈኖችን ይጫወቱ ነበር፡፡ በተጨማሪም ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን እነዲሁም ለተከታታይ ለ10 ዓመታት ትያትር ለህዝቡ በነፃ ያቀረቡ ናቸው፡፡ ሐይዋኖች ሙጋድ የሀረሪን ሙዚቃ ወደ ዘመናዊነት እንዲቀየር አስተዋፅዖ አድርጓል፤ መሰብሰብ ክልክል በነበረበት ወቅት የተለያዩ መልዕክቶችን በሙዚቃ ያስተላልፉ ነበር፡፡ ሐይዋን ሙጋድ የመጀመሪዎቹ የባንዱን ታሪክና አንድ መቶ የዘፈን ግጥሞቹን ጨምረው "ቲሐይዋን ሙጋድ ዚታሪኀ አለፍ"በሚል በባንዱ አባላት በነበሩት አቶ አዩብ አብዱላሒ እና በአቶ አብዱላሒ አሊ ሸሪፍ(በምስራቅ አፍሪካ ብቸኛው የግል ሙዚየም ባለቤት) በመጋቢት 1999 ዓ.ም. ለንባብ አብቅተዋል፡፡




ሐይዋኖች ሙጋድ አባላት ፎቶ

# ፬.፩ አፍሪካባቱ ውጋድ

በ1940ዎቹ ዘመናዊ ሙዚቃን እና ወጣ ባለ ስያሜ ብቅ ያሉ የመጀመሪያዎቹ ባንዶች ናቸው፡፡እነ አርቲስት ቦኪ ታላን ይዞ ምስራቁን ክፍል አርት ያነቃነቁ ነበሩ፡፡በአላትን መሰረት አድርገው በአከባቢው ያልተለመዱ የሙዚቃ አይነቶችን አንግበው ሱሐሊና የምስራቅ አረቦችን ሙዚቃ ሱዳንና እንግሊዘኛን በሚስረቀረቅ ድምፃቸው ታጅበው ማዜም የጀመሩ መሆናቸው ይነገራል፡፡ በሀረር ከተማ የኢንግሊዝ መንግስት ቆንሲላ ከፍቶ ሲንቀሳቀስ ለመጀመሪያ ጊዜ ድጋፍ የተደረገለትና ከቆንሲላው አድናቆትን ያተረፈ ባንድ ነበር፡፡ ከነዚህ በኋላ በርካታ ባንዶች ከክልሉ ቋንቋ ዎች ማለትም ከሀረሪ፣ከኦሮመኛ፣ከሶማለኛ አልፈው ግሎባል ሙዚቃዎችን ማቀንቀን ለመጀመራቸው ምክንያት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

# ፩.፯ የሙጋዶቹ አባላት ስም ዝርዝር

ልክ እንደ ሒላል ሑሉ በርካታ ሙጋዶች እንደየ አደረጃጀታቸው ላሑኑ የሀረሪ ሙዚቃ ፈር ቀዳጅ የሆኑ አርቲስቶችን ይዘው የቆሙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥቂት ሙጋዶች አባላት ዝርዝር ለታሪክ ማስታወሻት ይሆን ዘንድ እንመልከታቸው፡፡

## ፋርሪሳች

1. መሐመድ ያቁብ
2. አሕመድ አብዶ
3. አሕመድ አብዱላሂ
4 .ዘካርያ ኢድሪስ
5. ኢሊያስ
6. አብዱለዚዝ አቅለን
7. አብዱልመሂድ

## ፈናናች

1. አብዱሰመድ አብዶሽ
2. አድሃም ሽሪፍ
3. አብዶሽ
4. አብዲ ሐጂ
5. ሙኽታር
6. ዩሱፍ ኩርቱ
7. አህመድ ኢዋድ
8. ዘካርያ ዱርሪ

## አዲባች

1. አሜ ዩሱፍ ሲዮ
2. መሃመድ በራሶ
3. ፈኢድ አቅለን
4. ሐሺም ኸዲር ሪድዋን
5. በክሪ አብዶሽ

## ሰታች/YEBS/

1. ዩሱፍ ኡመር
2. መሐመድ ዱሪ
3. ሱፊያን ማህዲ ፌይሰል
4. አብዲ ዘካርያ
5. አብዱረህማን ማህዲ
6. አብዱሰመድ ኢድሪስ

## ሸባባች

1. አብዱላሂ ሳሊህ
2. አብዱልአዚ አብዶሽ
3. አህመድ ሙሳ
4. መሃመድ አብዱላሂ

## ሐይ ዘራች

1. ጃሚ ኻሊድ
2. አብዱረሂም ዱሪ
3. ሑሴን ኸለፍ
4. ዘኮ ኡስማኢል
5. አብዱልዋሲ ዩሱፍ
6. አብዱልሰመድ አብዱልመጂድ
7. አሚና አህመድ መዝሃር

## ኢቆት ሲነት አዜባቾ

1. ፈይሰል ቶውፊቅ ፈኽሪ
2. በክሪ ሽሪፍ
3. ሳፊያ ጃሚ
4. ኑርያ ጃሚ
5. አብዱረሕማን መሐመድ
6. አብዱልሐሚድ
7. አሊያ  ኽለፍ
8. ሙሉካ  ኽለፍ
9. ዘኮ አፈን
10. ሸሐብ መሃመድ
11. ሐጀራ ኽለፍ
12. በድርያ ረመዳን

## አብዲ ጊታር

1. አብዱለባሲጥ መሃመድ
2. አብዱረሕማን

## LA BAND

1. ሙኽታር አሕመድ ጋሪ
2. ኢሊያስ ኽዛሊ
3. አብዱሰመድ ኽዛሊ

## ሳሚ

1. ሳሚ ኡመር
2. አብዱሰመድ ኽዛሊ
3. ሻዎል

## ሻሚቱ

1. ሻሚቱ(ኑርያ አህመድ አሊ ሻሚ)
2. ጊኒ

## ዳሚዱስ(አሺቃቾ)

1. አዲብ አበዶሽ
2. ማሕቡብ አደም
3. አንዋር ሽሪፍ
4. ሙራድ ቡሌ
5. ሐይደሩስ ኢብራሂም
6. ኻሊድ

## መለሳያች

1. በድሪ አሕመድ
2. ያህያ ሙኽታር
3. ሳሊህ ገልሞ
4. መሃመድ ዘካርያ
5. ሙኽታር አህመድ ጋሪ

## ሐብሉል

1. አትሃም ዱስ
2. አብዱልማሊክ ገራዶ
3. ነጂብ አብዱሰታር
4. ሰላሃዲን መሃመድ(ሰሌ)

## THE ADUS BROTHERS

1. አተሃም ዱስ
2. በድሪ አዱስ
3. አብዱልዋሲ አዱስ

## ፈዘላች

1. አሊ ፈዘል
2. መሃመድ ፈዘል
3. አብዱናሲር ፈዘል(አብዶ ፈዘል)

## ኮከባች

1. አሜ ዩሱፍ ስርሪ
2. መሃመድ ዩሱፍ
3. መሃመድ አህመድ

## ሐይዋናች

1. አዩብ አብዱላሂ
2. አብዱላሂ አሊ ሸሪፍ
3. አብዱረህማን መሃመድ
4. አብዱሰቡር አህመድ
5. አብዱላሂ ዮኒስ
6.አደም ሐሰን
7. አሊ ኡመር
8. አሊ ፈዘል

9. ባሻ ቡሌ

10. በድሪ ዩሱፍ

11. ሐምዶኝ ሸሪፍ

12. ሐሰን ሸሪፍ

13. ዱርሪ ሸሪፍ

14. ዱርሪ ሐሰን

15. ሙኽታር ሻሽ

16. አደም ዱራር

17. ጃሚ መሃመድ

18. ከማል አሊ

19. ኢስሐቅ ጋቱር

20. ረመዳን አብዱረሒም



የሒላል ሙጋድ አባላት ፎቶ



ኪነቶች በሰርግ ላይ



አርቲስት አህመድ ጊዳይ



አሊ መሐመድ ፈዘል ከላይ ዶ/ር አሊ ቢራ

# ፯. የሀረሪ የሙዚቃ ስራዎች በሌሎች አርቲስቶች

የሀረሪ የሙዚቃ ስልት ዲያቶኒክ እንደመሆኑ መጠን ለተቀሩት አርቲስቶች ሙዚቃውን ለመስራት ፈታኝ ነው፡፡ ከጥቂቶች በቀር በተሟላ መልኩ በሰባቱ ስደር የሔደና የዘፈነ አርቲስት ማግኘቱ ከበድ ይላል፡፡ያም ሆኖ ከመስራት አንጻር ከታዋቂ እስከ ጀማሪ አርቲስቶች ሁሉም ለመስራት መኩረዋል፡፡ጥቂቶች ሙዚቃውን ከማበላሸት መተዉን መርጠዋል፡፡በሌላ ቋንቋ ዘፋኝ አርቲስቶች የተሰሩ ገሚሱ ህዝባዊ ዜማዎች ሲሆን ጥቂቱ በግለሰቦች የተደረሱ እንዲሁም በቀድሞ ባንዶች ይዜሙ የነበሩ ናቸው፡፡ዜማው ፈታኝ እንደመሆኑ መጠን የረጅም ጊዜ ጥናት የሚሻ በመሆኑ በጥቂት ዘፋኞች አንደበት እንጂ ሰፍቶ ሊሰራ ሳይችል ቀርቶዋል፡፡የሀረሪ ዘፋኞች ከራሳቸው አልፈው ለተለያዩ ዘፋኞች ግጥምና ዜማ በመስጠት ቋንቋውንና አርቱን ያጋሩ ነበር፡፡ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በ1960 በአርቲስት በክሪ ዱላሎ ተፅፎ ዜማ የተደረሰለት “ዱደንቃል” በሚል ርእስ የሚታወቀውን የአርቲስት ዶክተር አሊ ቢራ የሀረሪ ዘፈን ደራሲም መጥራት ይቻላል፡፡ከዚህ በመቀጠልም ሑለት ተጨማሪ ዘፈኖች የተጫወተ ሲሆን ሌሎችም እንደ አርቲስት አፈንዲ ሲዮ፣አርቲስት ሐመልማል አባተ፣ታደለ ሮባ፣ቢተው ወርቁ፣ቃቂ ተስፋዬ፣ዳንኤል ከበደ፣ዳንኤል፣ገብሩ ፋኖ ያሉትም በጊዜ ልዩነት ሰርተዋል፡፡



ሐኪም፡ዘምቼዉ፡መሳዬ፡

ሐኑሪዩ፡ዘሞቼዉ፡ሀወካዬ፡ኬሊ፡ኢሽቂሌ፡ሚዓሣዬ፡
ነጉምዘዉ፡ዘሞቼዉ፡መካዬ፡ኢሽቂን፡መሪሌኝ፡ኣሓዬ፡
የፉንቃል፡...የፉንቃል፡

አዝማች

1ኛ፡ ኢሽቂ፡ወሖራም፡ያሕዶል፡ኩሉሌ፡
ዚናኬዉሣች፡ያፊሹር፡ያዋርኬ፡

አዝማች

2ኛ፡ ዓሺም፡ሌይሊ፡ወለኩን፡ያቃሕል፡
ኢሽቆሣቶቤ፡ያዘርፌን፡ያማዓሕል፡

አዝማች

3ኛ፡ ነጃብዘም፡ጫሜዉ፡ፊለኝዘቤ፡ኪብሪዉ፡
ማንፉሜሟቼዉ፡ሙኑር፡ዚፉ፡ኔብሬዉ፡

አዝማች

4ኛ፡ ማኝ፡ያፉ፡ማሊ፡ኢሽቂሌ፡ፊመዘዐ፡
ዘይ፡ኪመዐዕነቻ፡ሁዙን፡ዚኛመርዘዐ፡

አዝማች

5ኛ፡ ኢንቤሮሜል፡ያሹኡ፡ኢሽቂቤ፡
ኢፊ፡ያከባል፡ፊጉ፡ወርሐሳሌቶቤ፡

በዶ/ር አሊ ቢራ የተዜመው ፉደንቃል የሚለው ዘፈን በአርቲስት በክሪ ዱላሎ የተደረሰው የእጅ ፅሑፍ
ከግል ሙዚየም ባለቤት ከአቶ አብዱላሒ አሊ ሽሪፍ የተገኘ

# 10. ሀረሪ እና ሙዚቃ መሳርያ

የሀረሪ ብሄር ካለው መረጃ ጋር አሰባጥረን ስንመለከት አሁንም ድረስ የሚጠቀምባቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች ምት ላይ ያተኮሩ ሪትማቲክ ናቸው፡፡ እነዚህም በሳይንሳዊ አጠራር idiophones እና membranophones ናቸው፡፡ በድምጽ አደረጃጀት(sound produre) monodic,heterophonic , polyphoonic ሲሆኑ አንዳንዴ Anti phonal form ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ይህም የራሱ የሆነ ምክንያት ሲኖረው ከእምነት ጋር በማያያዝ ዜማ የሚያወጡ መሳሪያዎች ግብፅ ሐረርን በተቆጣጠረችበት ዘመን /ከ1875 -1885/ በራኡፍ ባሻ ትእዛዝ እንዲቆም እና በሪቲማቲክ መሳሪያዎች ብቻ እንዲሰራ ማድረግ መጀመራቸው ይነገራል፡፡(አብዱላሒ አሊ ሸሪፍ/የግል ሙዚየም ባለቤት/)

## የሀረሪ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች

### 10.1 ጸፍ /Frame drum/



በተቀረው የአረብ አገራት ሪቅ (Riqq) እና ቡቤን(Buben) በመባል ይታወቃል:: የእጅ ከበሮ ሲሆን በምት እና በመወዝወዝ ቀጠን ያለ የታንቡር ድምፅና ፅላንፅል ድምፀት (percussive sound) አቀናብሮ በአንድነት የሚያወጣ ነው፡፡ በአይነቱም idiophones የሚመደብ ሲሆን ከይዘቱም ክብ እንጨት(wooden ring)ሲሆን ከለስላሰ ቆዳ(parchment or skin)፣ከእንጨት፣በክብ ሳንቲም በሚመስሉ ብረቶች(thin metal) የሚሰራ ነው፡፡ ከ25- 35 ዲያሜትር ሲሆን ከ5-8 ሴ.ሜ. እርዝመት አለው:

## 10.2 ከበሮ/kettle drums/

ይህ ከበሮ membranophones የሚመደብ ሲሆን በእጅ የሚያዝና የማይያዝ ተቀምጦ የሚደለቅ አልያም በእንጨት የሚመታ ነው:: በይዘትና በአይነታቸው የተለያዩ ሲሆኑ እንደየ አገልግሎታቸው



የሙዚቃውን አይነትና የምት ድምፅ የሚለዩ ናቸው፡፡ አሰራራቸው እንደሌሎች አይነት ሲሆን ከዋንዛ አልያም በቀላሉ ሊሰነጠቅ ወይም ሊጎዳ በማይችል እንጨት የሚሰራ ነው:: በቅርፁም ክብ ነው፡፡ነገር ግን እንደ ከፊል ሐይማኖታዊ የከበሮ አሰራር ሁለት አፍ (አፈጋን እና ያማሪት) ቢኖረውም ሰፊው አፍ (አፈጋንኑ) ብቻ ለጥቅም ይውላል ያማሪቱ(ጠባቡ) አገልግሎት አይሰጥም፡፡ ከረቡ ለአገልግሎት ከመዋሉ በፊት እንደተሰራበት የቆዳ አይነት ከ30 ደቂቃ እስከ አንድ ሰአት ፀሐይ ላይ ይቀመጥና እንዲሞቅ ይደረጋል፡፡ይህ የሚሆንበት ምጥን ድምጽ እንዲኖረውና ታንቡሩ አልያም የተወጠረው ቆዳ ለአገልግሎት ብቁና ምቹ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡

## 10.3 ክበል/wooden blocks/

ከእንጨት የሚሰራ ሲሆንከidiophones የሚመደብ በእጅ ተይዞ የሚጨበጨብበት ቀጠን ያለ ድምፅ የሚያወጣ ነው:: ቁመቱ ከ15-17 ሴ.ሜ.ሲሆን 7 ሴ.ሜ.ስፋትና 3 ሴ.ሜ. ውፍረት አለው፡፡



እነዚህ በየትኛውም ማለትም በእምነት እና በአለማዊው ውስጥም የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በግብፆች አገዛዝ ስር ሀረር ለዘጠኙ አመታት በነበረችበት ጊዜ የተፈጠሩ አንዳንድ ሁኔጣዎች ይህን የሙዚቃ መሳርያ ውስንነት እና ሪትማቲክ ብቻ መሆኑን ይነቅፋል፡፡በራኡፍ ባሻ ጊዜ የነበሩትን የሙዚቃ መሳርያዎች ሲያሳይ::

## 10.4 ኪራር አልያም ኪሳሳር (ክራር)

ባለ ሰባት ክር ሆኖ በይዘትና በአይነቱ ብዙም ልዩነት የሌለው ሲሆን ከሱዳን፣ከኑቢያና ግብጽ ጋር ተቀራራቢ አልያም ተዛማጅ ነው፡፡



## 10.5 ታንቡር/ tanbur / (ማሲንቆ)

ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በአይነቱ ከኢራኑ ዱታር ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ኢራኖች አሁንም ይጠቀሙበታል። በ16ኛው ክፍለዘመን ይህ ኢራኖች ከሀረር ጋር ከነበራቸው የንግድና የፖለቲካ እንዲሁም የማህበራዊ ትስስር አንጻር ከኢራን የተወረሰ ሊሆን ይችላል፡፡ምክንያቱም ኢራኖች ይህን መጠቀም ከጀመሩ 1500 እድሜ እንዳለፈው መረጃዎች ያሣያሉ፡፡ሆኖም በዚሁ ዘመን ከኢራን ወደ ሱሪያ እንደሔደና አሁንም እንደሚጠቀሙት የታሪክ ድረሳናት ያስረዳሉ፡፡



## 10.6 ቀርና (ዋሽንት) ፡–

ኢራኖች ካርና ብለው ይጠሩታል፡፡ባለ ሰባት ቀዳዳ3 ሴ.ሜ ዲያሜትር የአፍ ስፋት ሲኖረው ከእንጨት የሚሰራ ነው፡፡ይህንንም ኢራን እና ሱሪያዎች ይጠቀሙበታል፡ ፡ እነዚህን የክር እና የትንፋሽ ሙዚቃ መሳርያዎችን ራሡፍ ባሻ ከእምነት ጋር በማያያዝ እንዲወገዱ እንዳደረገ እና እንዳይጫወቱ እንደከለከለ በአንድ ምንባብ ላይ እንደሚገኝ መረጃ ከሰጡኝ መሐከል አንዱ የሆኑት የግል ሙዝየም ባለቤት የሆኑት አቶ አብደላ ሸሪፍ እውነታውን ያስረዳሉ፡፡ለዚህም ማስረጃ አድርገው ከሚያቀርቡት መሐከል ኢዋልድ ዋግነር በፃፈው መፅሐፍ ላይ "EWALD WAGNER




126 Text B

219. *Ḥalet wälet näbi-le kärära, näbi-le z-älkärära bi-isatin ḥarära.*

219. Seßhafte und Nomaden sagten laut: „Für den Propheten!" Wenn jemand nicht laut: „Für den Propheten!" sagt, wird er im (Höllen)feuer brennen.

ሐሌተ ዋሌተ ነቢሌ ከረራ ሀሌት እና ዋሌት ለነቢ ከረረ

ነቢሌ ዘልከረራ ቢኢሳቲን ሐረራ ለነቢ ያልከረረ በእሳት አረረ

የሚሉ በርካታ የዝክሪ ግጥሞችን ያጣቅሱና በሀረሪ አባባል "ኪራር ኵት አትኪረርበኝ"እንደ ክራር አትክረርብኝ የሚለውንም ጨምረው ያሳያሉ፡፡ክራር በዛን ግዜ የሀረሪ ብሔረሰብ ካልተጠቀመበት ቃሉን እንዴት መጠቀም ቻሉ አልያም ለምን ለመጠቀም እና በምሳሌ ለማንሳት አስፈለገ?

ይህም የራሱ ጠለቅ ያለ ጥናት የሚሻው ነው ፡፡በውጭ ዜጎች የተፃፉ በርካታ መፀሐፍት መኖራቸው ለማሳረጃነት ለዛሬ ታሪክ ፀሐፊያን ገቢር ይሆናል፡፡ለዚህም በአንድ ቆየት ያለ መፀሀፍ ላይ የተገኘውን የሀረሪ ብሔረሰብ ለጦር መሳርያነት ከሚጠቀምባቸው ማቴሪያሎች መሐከል የሙዚቃ መሳርያዎችን ያሳያል፡፡




ኢዋልድ ዋግነር በፃፈው መፅሐፍ ላይ "EWALD WAGNER HARARI-TEXTE IN ARBISCHER SCHERIF 1983" የተገኘ



በ1549 ኢማም አሕመድ በጦር ሜዳ ተሰውተው በባቲ ዲል ወምበራ ጊዜያዊ አስተዳደር ዘመነ መንግስት ከሀረር በባርነት ተገዝቶ ወደ ህንድ በመሔድ የአውራግባድ ለ29 አመታት ንጉስ መሆን ችሎ የነበረው የህንዱ ንጉስ ማሊክ አምባር ባለ ሰባት(7) ክር ክራር ሲጫወት

( ሀረር ውስጥ የነበረውን ሙዚቃ አልያም ክራር ቀደም ብለው በ15ኛው ክፍለዘመን ይጫወቱ ነበር፡፡ምክንያቱም ህንዶች በ15ኛው ክፍለዘመን ወደ ሀረር ገብተው የንግድና የባሪያ ንግድ ትስስር ከነበራቸው ይህን ክራር አያጫወቱም አልያም አያውቁትም ማለት ይከብዳል፡፡)

በተጨማሪም እስካሁን ባለው ጥናት መሰረት በኢትዮጵያ ያሉ ሙዚቃ አይነቶች ፐንታቶኒክ(pentatonic) የድምፅ ስደራ(ሐዲድ) አልያም ባለ 5 ቁልፍ ናቸው፡፡ህንዶች የሙዚቃ ስልታቸው ክሮሞቶኒክ(chromotonic or hybird) ነው ባለ 12 ቁልፍ፡፡ ሀረሪዎች ብቸኛ የሚያስብላቸው የዲያቶኒክ(Diatonic) አልያም Homophonic texture(አፅቅ) የድምፅ ስደራ(ሐዲድ)( ባለ7 ቁልፍ የሙዚቃ ስልት የሚከተሉ መሆናቸው ነው፡፡ለዚህም የሀረሪን ዘፈን በክራር ለመጫወት ባለ ሰባት ክር ክራር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ይህን ምስል ስንመለከት በጥቂቱም ቢሆን ሐሳብ ይሰጠናል፡፡(ስለ ስልትና ሙዚቃ ዘውጎች በተከታይ የምናይ ይሆናል፡፡)

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከ1950ዎቹ እስከ 1960ዎቹ የተለያዩ የሙዚቃ መሳርያዎች የገቡበትና መጠቀም የጀመሩበት ግዜ ነበር፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ አድርገን መውሰድ የምንችለው በምስራቅ ኢትዮጵያ የመጀመርያው በሙዚቃ መሳርያ የተደራጀውን እንዲሁም ግንባር ቀደሙን ሒላል ሙጋድን ነው፡፡ ግዜውም 1951 ዓ.ም. ነበር፡፡

## 10.7 የሀሪሪ ሙገዶቱ ይጫወቱት ነከበረው የሙዚቃ

መሳርያዎች መሐከል፡-

1. ደፍ (KITLLE DRUM)



2.ፒያኖ (PIANO)



3.ከበል (WOODEN BLOCK)



4. ሲንዛይሰር(SYNTHESIZER)




5. ጃስ (VINTAGE DRUM SET)



6. ኪይ ቦርድ(keyboard)(ORGAN)



7. ዋሽንት (FLUTE) (BANSURI)



8. ሐርሞኒካ(HREMONICA)



9. ዶርቡጃ(GOBLET DRUM)

INDIAN TUMBAKNAER





TURKISH DARABUKA

10. አኮርድዮ (AKORDION)




PIANO AKORDIO



11.ከረቡ(ከበሮ) (CONICAL-HAND DRUM)

LITUGICAL-DRUM



12.ጊታር(GUITAR)

MARTIN GUITAR



# 11.ቀፈት መሃለቅ

የሀረሪ ሙዚቃ ለንግድ፣ዘፈን ለመሸጥ ተብሎ የሚዘፈን አልነበረም፡፡ ሑሉም አርቲስት ስሜቱን ከመግለጫነት ለሙዚቃ ካለው ፍቅር በዘለለ ለንግድ ከቶ የማያስበው ነው፡፡ ይህ ለየት ያደርገዋል!!ይህም ማለት የሀረሪ ዘፈን ባሁኑ ግዜ ቆመን ስንመለከት ከሀረሪ ክልል የዘለለ ተሰሚነት አልያም ተሰራጭቶ አይታይም እንዲሁም በሌላ ክልሎች ሳይታወቁ ቀርተዋል፡፡ለምን ይሄ ሆነ ልትሉ ትችላላችሁ፡-

የሀረሪ ዘፈኖች ከድሮም ጀምሮ ካላቸው እና ከሚሰማቸው ስሜት በመነሳት እንዲሁም ሰርግ፣በአላት፣ዝግጅቶችን ለማድመቅ ለማሳመር ሲሉ ይጫወታሉ ከዛም ባለፈ ከባህል ከወግ ከሐይማኖት ጋር ባለው ቁርኘት ይዘፍናሉ፡፡ብዙ የሀረሪ የቀድሞ ዘፈኖች በግለሰብ እጅ እንዲሁም በቃል በሙዝየም ብቻ ይቀራሉ፡፡

ይህ የሚሆንበት ምክንያት አንድ የሀረሪ ግለሰብ አንዷትን ሴት ሲያፈቅር ላፈቀራት ልጅት ከነጠላ ዘፈን እስከ ሙሉ አልበም አልፎም በዛ ያሉ አልበሞችን ሰርቶ በስጦታ አልፎም ባገኘው አጋጣሚ መድረክ ላይ በመዝፈን ስሜቱን ይገልፅበታል፡፡ለአገር፣ለባሕል፣አልያም ለሙዚቃ ፍቅር መግለጫነት የዘለለ ወደ ንግድ የማምጣት አላማ አሁንም ድረስ አይታይም፡፡ይህን መንገድ እንደ ባህል ተይዞ አሁንም ድረስ ሲጠቀሙበት እናያለን፡፡ይህ ደግሞ የዘፈኖቹን መጨረሻ እጣ ፋንታውን መገመት ይቻላል፡፡

ታድያ እነዛ ዘፈኖች በሌሎች ሲደመጡ በሰርግ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ መዝፈን ይጀምራሉ፡፡ያኔ በተለያዩ ዘፋኞች ሲዘፈን መጀመርያ ያወጣው ግለሰብ ዘፈን ባለቤትነቱ ሕዝባዊ ሆኖ የሚቀርበትም ግዜ አለ፡፡በሚዘፍኑበትም ግዜ የሚዘፍኑት ለገንዘብ ሳይሆን የራሳቸውን ውሰጣው ስሜት ለመግለፅ እንዲሁም የሌላውን ስሜት ለመጋራት በማሰብ ነው፡፡

አድማጭ እና ተመልካቹም ወደ ዘፋኙ በመጠጋት ገንዘብ ግንባሩ ላይ አልያም አንገቱ ስር (ይሸጉጥለታል)ያስገባለታል፡፡እናም ይህ የብር አሸላለሙ በሀረሪው ማህበረሰብ "ቀፈት መሃለቅ" ቃል በቃል የአማረኛው ቀጥተኛ ትርጉሙ (የግንባር ገንዘብ)በመባል ይታወቃል፡፡ስለዚህ የሀረሪ ዘፋኞች ስሜትን ከመግለፅ ባሻገር ለገንዘብ ተብሎ ሚሰራ ነገር አልነበረም ባይሆን ጥቂት ገንዘብ የሚያገኙት በቀፈት መሃለቅ ብቻ ነበር፡፡ይህን ገንዘብም ለሙዚቃ መሳሪያ መግዣ ይጠቀሙበታል፡፡

እንደምሳሌ አንድ ታዋቂ የሀረሪ ሙዚቀኛ ታሪክ እንመልከት አርቲስት አትሐም ሽሪፍ ይባላል በ1970ዎቹ የሙዚቃን አለም ተቀላቀለ፡፡ አርቲስት አትሐም እጅጉን አይናፋር በመሆኑ ሙዚቃዎቹን በቴፕ ካሴት በመቅዳት ማንነቱን ሳይናገር አልበሙን በተነ፡፡ ከአድማጩ ብዙ ተወዳጅነት ሲያገኝና የአርቲስቱን ማንነት ለማወቅ ጉጉት እንዳደረበት ሲመለከት እያከታተለ ሙዚቃ መስራቱን ተያያዘው፡፡አጋጣሚ ሆነና በርካታ አልበሞች እየሰራ ሲበትን ቆይቶ ወደ ውጭ ለስራ ጉዳይ አመራ እዛም ሆኖ አልበም እየሰራ ከ30 አመት በላይ አስቆጠረ ሐያ ሑለት አልበሞች ሰራ ይህ ማለት ከሑለት መቶ ሐያ ዘፈን በላይ!! ይህ ሁሉ ሲሆን አርቲስቱን በመልክ የሚያውቀው አልነበረም፡፡ በ2004 ዓ.ም. ሀረር ሲገባ እኔ ነኝ እስኪል የሚያውቀው ጠፋ፡፡

በሙዚቃው ስራ ለፍቅር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡2005 ኣ.ም.ራሱን ገሐድ አወጣ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በድሮው ETV በአሁኑ EBC ላይ ቀርቦ ራሱን ጋሐድ አወጣ፡፡ አሑንም ድረስ በመልክ የማይታወቁ ነገር ግን ዘፈኖቻቸው ዝናን ያተረፉ አርቲስቶች በርካታ ናቸው፡፡

ይሕ የሚያሳየን ለገንዘብም ለዝናም አርትን የማያውሉ አርቲስቶች ለአርቱ ክብር አላቸው ናቸው፡፡

በሙጋድ ደረጃ ስንመለከት አንድ ሙጋድ ስራውን ሲያሳይ መድረኩ ጫፍ ጠርዙ ላይ ሰፌድ ይቀመጥና ዘፈኑን ዝግጅቱን የወደደ ለሞራልበዛሰፌድላይያለውንያኖራል፡፡ይህደሞመድረኩእንዳይረበሽና ስርኣት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ይህ የተሰበሰበውን የተገኘውን ቀፈት መሃለቅ በስተመጨረሻ ለባንዱ(ለሙጋዱ)ማጠናከርያ እና የሙዚቃ መሳርያ እና የተለያዩ የሙጋዱን ጉልበት ማጠናከርያነት ይውላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ሁሉም ማለት ባያስደፍርም በርካቶች ከሙዚቃው አለም ቶሎ ሚገለሉት ወደ ትዳር ሲገቡ ከአለማዊ ህይወት ተላቀው ወደ ሐይማኖታዊ ህይወት ስለሚገቡ በጅምር የሚቀርበት ሁኔታም ሰፊ ነው፡ ፡ ለዚህም ነው የሀረሪ ሙዚቃ ሳያድግ ባለበት እየተራመድ ለዘመናት የኖረው፡፡ነገር ግን ያሉ ዘፈኖችን እንቁጠር ብንል ስፍር ቁጥር የሌላቸው ለመቁጠር ሚዳግቱ ድንቅ የሙዚቃ ስልት በድሮው ግዜ እንዲህም አይነት የሙዚቃ ቅንብር አለ ወይ ብለን ተአምር እስኪመስለን የዘመኑን ቅንብር ከ 50 እና ከ60 አመታት በፊት እናገኛቸዋለን፡፡

# 12. ፈቀር (ዘፌን)

የሀረሪ ብሄረሰብ ዘፈን "ፈቀር"በመባል ይታወቃል፡፡የሀረሪ ዘፈን እጅጉን የረጅም እድሜ ባለፀጋ ነው፡፡እየተወራረሰ ለዚህ ትውልድ የበቃ ነው፡፡በሐገራችን ቆየት ያሉ አልያም በ1992 የሁለተኛ ክፍል የሙዚቃ ማስተማሪያ መፀሐፎች ላይ ቅኝቶችን ሲያስቀምጥ በአምስት ይከፍሎዋቸው ነበር፡፡

1- አንቺ ሆዬ

2- ትዝታ

3- ባቲ

4- አምባሰል

5- የ"አደሬ" ሙዚቃ በማለት ያስቀምጣቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ባሑኑ ጊዜ ከአራቱ ቅኝቶች ውጭ የሀረሪ የሙዚቃ ስልት ሲካተት አልገጠመኝም፡፡እንደ እኔ ግምት እና ካለኝ መረጃ በመነሳት በቂ ጥናት እና ትኩረት ባለመሰጠቱ እንደሆነ ነው፡፡ ወደ ሀረሪ ሙዚቃው ስንመለስ የሀረሪን ዘፈን ለሁለት ይከፈላል፡-

1 - ጌይ አዳ ፈቀር(ባህላዊ ዘፈን)እና

2 - ጌይ ፈቀር(ዘመናዊ ዘፈን) በመባል ይታወቃሉ፡፡

# 13. ስለ "ጌይ" አጭር መግለጫ

ከዚህ በኋላ ባሉት ጽሑፎች ጌይ የምትል ቃል ልትደጋገም ትችላለች፡፡ ምናልባት ለዚህ ቃል በእውቀታችን መጠን በሰማነው ትርጓሜ ልንሰጠው እንችላለን፡፡በሀረሪ ግን ትርጓሜው ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በሀረሪ ቋንቋ ጌይ ማለት ከተማ ማለት ሲሆን ሀረሪዎች በሚጠቀሟቸው ነገሮች ላይ ጌይ ትታከላለች፡፡ እንደምሳሌ

-ጌይ ኡኻት - የከተማ እንጀራ

-ጌይ ሊጂ - የከተማ ልጅ

-ጌይ ኢራዝ - የከተማ ልብስ

- ጌይ ፈቀር - የከተማ ዘፈን እና መሰል ቃላት በዚሁ ይገለፃሉ፡፡ ይህ የሆነበት በሁለት ምክንያቶች እንደሆነ ይነገራል፡፡ አንደኛው እንደማንኛውም ቋንቋ የከተማውን ከገጠሩ ለመለየት ሲሆን ሁለተኛው በፍልሰት እና በተለያዩ አጋጣሚዎች በሀረር ዙሪያና አቅራቢያ ይገኙ ከነበሩት ህዝቦች በስልጣኔው እና በቀድሞ አሰፋፈር አገር አልያም ስቴት ክራፍት(የአገር ቅርፅ) የነበራት በመሆኗ ከተማነትን አገርነትን ለመግለጽ እንደተጠቀሙበት ይነገራል፡፡ ለዚህም እንደበቂ ማስረጃነት እ.ኤ.አ. 1855 ሀረር የገባው የመጀመሪያው እንግሊዛዊ አሳሽ ሰር ሪቻርድ በርተን ይህንኑ እውነታ the first foot step in east Africa or the exploration of Harar በሚለው መፅሐፉ ያትተዋል፡፡

# ፲፬. ጌይ አዳ ፌቀር

ጌይ አዳ ፈቀር ከሀረሪዎች ጋር አብሮ የተወለደ ነው ብል ድፍረት አይሆንብኝም፡፡ምክንያቱም ሁሉ ነገር ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት አብሮዋቸው የተሳሰረ ነው፡፡ይህ ባህላዊ ዘፈኖች የሚዘፈኑት በሰርግ ፣በኣላት፣በስራ(በደቦ)፣በጨዋታ፣በወግ፣በንዴት፣በፍቅር፣ለሐገር፣ለ ሙገሳ፣ለስድብ(ቆሰ)ወዘተ...ላይ ይዘፈናሉ፡፡ታድያ አዳ ፈቀር ሲዜም በእድሜ፣በፆታ፣በደረጃ፣ይለያያል፡፡ለግጥሙ እና ለዜማ ተስማሚ የሆነ ሰው ሊያዜመው ይችላል፡፡ይህ ማለት ለሚዘፍነው ዘፈን አዛዜም እድሜ፣ፆታ፣ደረጃ እና ድምፅን ይለያያል፡፡

አዳ ፈቀር ሲዜም

- በነጠላ
- ለሁለት
- በህብረት

የሚዜሙ ናቸው፡፡



ነገር ግን አብዛኛውን(አብላጫውን)የሚይዘው ለሁለት የሚዜሙ አዳ ፈቀር ናቸው፡፡እናም ለሁለት የሚያዘሙ ሰዎች ሁለቱም የራሳቸው ስራና ስም አላቸው፡፡ስማቸውን እና ተግባራቸውን በሚራስ የቅኝት አይነት ስር የምናገኘው ይሆናል፡፡

የሀረሪ ዘፈን ጌይ ፈቀር እና ጌይ አዳ ፈቀር ባጠቃላይ የሚያውጠነጥንባቸው ዘውጎች ስንመለከታቸው የራሱ የሆነ የአመዳደብ እና የዘውግ ክፍሎች ኖሮአቸው የሚዘፈኑ ዘፈኖች የትኛው በየትኛው ዘውግ እንደሚገኝ ለመረዳት ያስችሉናል፡፡

እነዚህን ዘውጎች ከፋፍለን ለመመልከት ስንሞክር 17 የተለያዩ ክፍሎች እና ዘውጎችን በመሰረታዊነት ተከፍሎ እናገኛቸዋለን፡፡ (ከቢር አብዱልሙሚን አብዱናሲር ቃለ መጠይቅ 2003 ዓ.ም እና ከመፀሀፋቸው የተወሠደ)

1 - አለሌ(ለአላሕ)

2 - ነቢሌ(ለነቢይ)

3 - ባድሌ(ለአገር)

4 - ደድ ሺራ(በፍቅር ጉዳይ)

5 - ፈቀር(ዘፈን)

6 - ሙራድ(የሰርግ)

7 - ዘማን ፈቀር(የዘመኑ ዘፈን)

8 - ሞይ ፈቀር(ሲነት ፈቀር)(የእደ ጥበብ ዘፈን)

9 - ፈንኒ ፈቀር(የመዝናኛ ዘፈን)

10 - ቀጠብቲ ሙዳይ ፈቀር(የትዝታ ዘፈን)

11 - ታሪኽ ኤድ ፈቀር(ታሪክ ተራኪ ዘፈን)

12 - መለሳይ ፈቀር(የጀብዱ ዘፈን)

13 - ሱዱብ(ቆሰ)ፈቀር(የአሽሙር ዘፈን/የሽሙጥ/)

14 - መፋለስ ፈቀር(የሙገሳ ዘፈን)

15-ሺርቲ ሃል ፈቀር(አከባቢዊ ዘፈን)

16 - ሚኻት ዘማን ፈቀር(የብሶት ዘፈን)

17 - ሒትፋን ፈቀር(የምክር ዘፈን)

እነዚህ የሀረሪ ዘፈን እና የግጥሙ ሰውነት ስንመለከት የተገነባው በነዚህ የሙዚቃ ዘውጎች ነው፡፡ነገር ግን እነዚህ 17 የግጥም ዘውጎቹ የግጥሙ ፍሬ ሐሳቦች ብቻ ሳይሆን እንደ ግዜው እና በሑኔታዎች አስገዳጅነት የተለያዩ ዘውጎች ሊወለዱ ይችላሉ፡፡

ነገር ግን እስካሁን ባለኝ መረጃ እነዚህ የግጥም ዘውጎች እናክፍሎች ብቻ እንዳሉ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ስለዚህ እነዚህ ዘውጎች በሁለቱም ውስጥ ማለትም በሀረሪ ባህላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ እንደሚገኙና እንደሚሰሩ ልብ ማለት ይገባናል፡፡

# ፲፭. የሀረሪ ዘፈን የቅኝት ጫፉ እና ስር መሰረቱ

## ፨ የሀረሪ ዜማ አኳኳል እና የዜማው አወጣጥ

የሀረሪ ዘፈን ስር መሰረቱ የቅኝቱ ጫፉ ብንመለከት ሁሉም የራሱ የሆነ የሙዚቃ ስልት ለመፍጠሩ ምክንያት ሆኖዋል፡፡ለምሳሌ፡- በሜጀር እና በሬጌ የሚጫወቱት ዘፈኖች እንዲሁም በተለያዩ የሙዚቃ ስልት የሚያዜሙት  የሙዚቃ መርገጫዎች ሊፈጠሩ የቻሉት የሀረሪ ሀረሪዎች ተሰማርተውበት በነበሩበት የሞያ ዘርፎች ነው፡፡

የሀረሪ  ዘፈን አሁንም ድረስ ከጥንቱ የሀረሪ ግጥም አፃፃፍ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ይህም መሆኑ የያኔውን የህይወት መስተጋብር ለመመስከር ምክንያት ሆኖዋል፡፡

ለዚህም ምሳሌ ይሆን ዘንድ ከ400 በላይ እድሜ ያላቸው የ"መስኖይ" መፅሐፍ እንዲሁም "ኪታቡል አል ፈቀር" ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህም መፅሐፎች ለጌይ ፈቀር እስካሁን በሒይወት ለመኖሩ ምክንያት አድርገን ልንወስደው እንችላለን ፡፡



# ፲፩. የሀረሪ የግጥም አፃፃፍ እና የገለፃ አሳሳል

እንደ ሙዚቃ ዜማው ሁሉ ወደ ግጥም አፃፃፉ ስንሄድ የሀረሪ የግጥም አፃፃፋቸው ይሰሩት ከነበሩት የሞያ አይነት ጋር እጅግ በጣም ቁርኝት አለው፡፡ይህም ማለት አንድ አራሽ አርሶ አደር የሚወዳትን ሴት ሊያወድስ ቢፈልግ ሐገሩን ሀረር ለሙገሳ ቢሻ ውስጡ ያለውን ለመግለፅ ቢነሳ ምሳሌ ለማጣቀስ የሰብሉን ውበት፣የማሳው ወደር ፣የአየሩን፣በጋ፣ገና፣ነፍሳትን፣አፈሩን፣ትርፉን፣ወዘተ...ምሳሌ እየሰጠ ውበቷን፣ፀባዮን፣አካሏን ለማሞገስ ለመግለፅ የስራውን ክፍል ውስጥ እሷን መሳሉ ይቀለዋል፡፡

እንደ አርሶ አደሩ ሁሉ አናፂውም፣ግንበኛውም፣አርብቶ ደሩም፣ነጋዴውም፣ወዘተ...ሁሉም በየራሳቸው አገላለፅ እና የሞያ ዘርፉን እያመሳከረ መግለፅ የፈለገውን ነገር ይገልፅበታል፡፡ስለዚህ ይህን አገላለፅ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሞያቸው ጋር በማያያዝ የሚፈልጉትን ሐሳብ ጋር በጣምራ ለግጥሞቹ ማማር ለበቂ ገለፃ ምክንያት ያደርጉታል ማለት ነው፡፡

እነዚህ ግጥሞች መነሻ እና መዳረሻቸው ይህው ይሁንናም አሑንም ድረስ ከጥቂቶቹ በቀር የትኛውም ግጥም ሲፅፉ ከዚህ የአፃፃፍ ስልት አይወጡም፡፡

## 17. የሀረሪ ባህላዊ ዘፈኖች የቅኚት አይነቶች እና መኀኒት

የሀረሪ ዘፈኖችን ሰብስበን ለጥናት እንዲመቸን እና ቀድሞም እንደተቀመጠው የሀረሪ ባህላዊ ዘፈኖችን ለመመልከት ስንሞክር እንደ አማረኛው ቅኝቶች ሁሉ የሀረሪውም አራት ክፍሎች አሉት፡፡እነሱም፡-

1 - ሳሌይ

2- ሚራስ

3 - ደርሲ እና

4 - መስኖይ ናቸው

## 18. ሳሌይ

ሳሌይ በአንድ ሰው ብቻ የሚዜም Solo Music ሲሆን እንዲሁም ማንኛውም በአንድ ሰው ብቻ የሚዜሙ የሀረሪ ዘፈኖች ሳሌይ ይባላሉ፡፡ የትኛውንም የሀረሪ ዘፈን ስንጀምር የሚጀመረው በሳሌይ ነው፡፡ የዜማው አይነት እና አጣጣል ስናይ በማይነር የሚዜም ሲሆን ዜማው በጣም የሚሳብ የሚመዘዝ ነው፡፡ሳሌይ ሊዜም ሲል በቅድሚያ መስመር ማስለቀቅያ እና መያዣ “ኤሔይ”የምትለዋን ቃል በዜማ ስትሳብ ከ2 እስከ 12 ግራፍ (እጥፋቶችን)ሊሰራ ይችላል እንደዘፋኙ ብቃት ከ12 አልፎ በአንድ ትንፋሽ እስከ 24/26 ሊደርስ ይችላል፡፡ባሁኑ ግዜ በብዛት የሚጠቀሙት እጥፋቶች በአንድ ትንፋሽ እስከ 8/12 ድረስ ብቻ ነው፡፡

ይሄም ማለት "ኤሖ2.4.6.8.19.12.ይ"ሲሆን "ኤሖይ"የምትለዋን ቃል በ4 እጥፋት ከጨረሰ የግጥም ቤቱን (ዊቂር ጋር ሐዋጅ)በ4 መጨረስ ይኖርበታል፡፡ይሕም በጨረሰበት እጥፋት የቀረውንም እጥፋት በጀመረው መጨረስ ይኖርበታል፡፡

ሳሌይ የሚዜመው ከሚዘፍኑ ሰዎች አንዱ እየዘፈነ ከሆነ መግባት የፈለገ ሰው ሳሌይ ማዜም ከጀመረ ሲዘፍን የነበረው ዘፈኑን ባጭር በመቋጨት ሳሌይ ላዜመው ቦታውን ይለቅና ሳሌይ ያዜመው ሰወ በተራው መዝፈን ይጀምራል፡፡ሌላውም በዚሁ መልክ በተራ ያዜማሉ፡፡ ይህም የአዘፋፈኑ ስርአት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሳሌይ ከዚህ ውጪ በእርሻ ግዜ፣በስራ ላይ፣ብቻቸውን ሲሆኑ የሚያዜሙት የዘፈን ቅኝት አይነት ነው፡፡

ሳሌይ በሴት አልያም በወንድ በነጠላ ብቻ የሚዜም ሲሆን ሲዜምም ከሁሉም የዘፈን አይነቶች ከፍ ባለ ድምፀት በመሳብ የሚዜም ነው፡፡ እዚህ ጋ ልብ ማለት የሚገባን ሳሌይ ሰዎች ባሉበትቦታ ሲዜም ሳሌይ ማዜም የሚችለው ወንዱ ብቻ ሲሆን በስራ በቤት ውስጥ ወዘተ...ላይ ግን ሁለቱም ፆታዎች ማዜም ይችላሉ፡፡

ሳሌይ በሌላ መጠርያው "ዋሊ ሙጥጢ ፈቀር" በአማረኛው (ዘፋኝ ብቻው ዘፈን) እንዲሁም "ቀር ፈቀር" (የነጠላ ዘፈን)በመባል ይታወቃል፡፡ሳሌይ የዘፈን መጀመርያ ብቻ ሳይሆን ራሱን የቻለ የዘፈን ቅኝትም ነው፡፡

የሳሌይ ቅኝት ውስጥ የተለያዩ የዘፈን አይነቶች እና ክፍፍሎች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በጥቂቱ ለመግለፅ ያህል እና ለማሳያ፡-

- ያዳ ፈቀር - የትዝታ ዘፈን
- ሴና ፈቀር - የቁጭት ዘፈን
- አፍዲጃ ፈቀር - የማድ ቤት ዘፈን
- ሚህራ ፈቀር - የግድታ(የስራ)ዘፈን
- ሚኻት ፈቀር - የችግር ዘፈን
- ደድ ፈቀር - የፍቅር ዘፈን

እንዲሁም ባሁኑ ግዜ ለሁለት የሚጫወቱትና በሚራስ ስር የተጠቃለለው "አዲያዬይ" እና ጌሌ ጌሌ በመባል የሚታወቀው መነሻ ምንጩና ቀድሞ በአንድ ሰው ብቻ ይዜም የነበረና መገኛው ሳሌይ ነው፡፡

# ፲፱. ሚራስ

ሚራስ(Canonical Song) የሚባለው የቅኘት አይነት በስሩ እጅጉን በርካታ የዘፈኖቹ አይነትን ጠቅልሎ የያዘና በሑለት ድምፃዊያን(ሑለትዮሽ)(ኮኦታን ኮኦት)/Phrase or Stanza/ የሚዜም የቅኝት አይነት ነው፡፡

ሚራስ ከቃሉ ስንነሳ ውርስ ማለት ሲሆን ይህ የቅኝት ዐአይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ የመጣና የቅኝት አይነት ነው፡፡ ዜማና ግጥም የቀድሞው ትውልድ ዜማና ግጥም ሳይደፈርስ ሳይዳቀል ዘመን ሳይሽረው ዘመን ተሽግሮ ለዛሬ የበቃ የቅኝት አይነት ነው፡፡ ኮኦታን ኮኦት አልያም ሁለትዮሽ የአዘፋፈን አይነቱ ለሁለት ድምፃውያን አልያም በመሪ ድምጻዊና በተቀባይ የሚዜም ሲሆን በአያያዝና በድምፅ አደራደር የመሪ እና የተቀባይ የድምፅ ቆይታ(Duretion ) እንዲሁም

እርዝመት(length) እጅጉን ተቀራራቢና የአንድእና የአንድ ከግማሽ ልዩነት ሲኖራቸው የሁለቱ የድምፅ አደራደር እንዲሁም ፍጥነትና ዝግታ (Tempo ) አንድ ሲሆን በሙዚቃ ኖታ አሰላለፍ ሌጋቶ (Legato) ይሔ ማለት ድምፃቸው በለሰለሰ ሁኔታ ከአንድ ወደ አንዱ ክፍተት ሳይፈጥር ይተላለፋል፡፡



የሌጋቶ አሰላለፍ

እንዲሁም በቅደም ተከተላቸው መሐከል እና መጨረሻ በግጥም ቤት ላይ የሚፈጠሩ መካከለኛ ክፍተት ስታካቶ (Staccato) እጅጉን የሚያስደምም የድምፅ ቃና (Tone Color) ይፈጥራሉ፡፡



የስታካቶ (Staccato) አደራደር

ለሁለት በሚያዜሙበት ቅፅበት መዝጊያው አልያም በመጨረሻ ቃል ማብቂያ ፊዲደል ጉተታ ላይ ከመሪው ድምፃዊ የአጃቢው ድምፀ ተ ቃና የለሰለሰ እና የሟሟ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ለሁለት የሚዜሙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ቅኝቱን የሚቀኙ ሁለት ዘፋኞችም የራሳቸው ስራና ስም አላቸው፡፡ በዚህ መሰረት ያለ ምንም የሙዚቃ ትምህርትና እውቀት በዶሜስቲክ ኖሌጅ በልምድ ባካበቱት እውቀት ያለምንም ስህተት መሰረታዊ የሆኑትን የዘፈኑ ቅኝት (Music Articuletion ) የሆኑትን ስታካቶ Staccato፣ Accent(ድምፀት)፣tenuto(ለሙሉ ቆታ ድምጽ መያዝ)፣Fermata(ከእርዝሙቱ በላይ ድምጽ መያዝ)፣ Staccato፣አሚልተው ይዘዋል፡፡

ስማቸውም፡-

፨ ዱመሲዛላ /መሪ/THROWER/

፨ ዱላህዲዛል /ተቀባይ/ CHATCHER/ ይባላሉ፡፡

## 19.1 ዱመሲዛላ /መሪ /THROWER/

ይህ የሙዚቃው መሪ ድምፃዊ /LEAD VOCALIST/ሲሆን የዘፈኑን(ላህኒ ዋ ዊቂር)ዜማና ግጥም በማዋሃድ ሜጀሩን(ድምፀቱን) ከፍ በማድረግ ርእሱን በመጥራት ዐጠር ያለ አንጓ ያዜማል(Phrase) ይዘፍናል፡፡ዱመሲዛላ/መሪ/THROWER/የግጥምና ዜማ (ላህኒ ዋ ዊቂር )ባለቤት አልያም የተሰራ ዘፈን ደግሞ ሊሰራ ይችላል፡፡ዱላህዲዛል/ ተቀባይ/CHATCHER/ ግጥምና ዜማውን በተቀበለው ዱመሲዛላ/መሪ/ THROWER/ ፈጠን ብሎ የመምራት(የመዝፈን)ባህሪ ይኖረዋል፡፡

## 9.2 ዱላህዲዛል/ተቀባይ/CHATCHER

የዚህ ሰው ስራ ዱመሲዛላ/መሪ/THROWER/ ግጥም እየተከተለ ግጥምና ዜማ (ላህኒ ዋ ዊቂር ) በማዳመጥ በስሱ እየተከተለ (Melodic and Metro-rhythmic)የግጥሙን የመጨረሻ ቤት (ዊቂር ጋር አኺር

ጩቅቲ)በመያዝ አብሮ ከደገመ በኋላ አዝማቹን(መሸረብ)ከመሪ ድምፅ ጋር በማጠላለፍ third and fourth አልያም ኳየር/Choir/ በመሆን ያጅባል፡፡ታድያ አንዳንዴ የመሪውን ሙሉ ግጥም አብሮ እና በነጠላ ለብቻው የሚያዜምበት ግዜም ይኖራል፡፡

## የሚያዜምበት የደረጃ

ዱላህዲዛል/ተቀባይ/CHATCHER/ ከዱመሲዛላ/መሪ/ THROWER/ ላይ ከአፉ ላይ የመጨረሻውን ግጥም ቤት (ዊቂር ጋር አኪር ጩቅቲ) በመመንተፍ አልያም ፈጠን ብሎ ቃሏን በመቀበል የሚያረገው የግጥም አወሳሰድ “መትቃፈጥ” በመባል ይታወቃል፡፡

በሚራስ ስር የሚገኙ የዘፈን አይነቶችም፡-

- ጃሊዩይ
- ዊረጅላ
- መዋ ጃል ጃሊዩይ
- ጃሌ ጃሌ
- አሚረል ሙዕሚኖው
- ኢሰይ ለሌ መዲዋ
- ነለሺ/ዱሉሻል/
- ሉማ ለይሙኔይ
- አሚና ሙሐመዴይ
- አላ ዋሊዩይ
- ጌሌ ጌሌ
- ከሎሌይ

- ቀመር ሻሼይ

- ጉምጉምቲ

- ቆሰ ፈቀር እና መሰል ሲገኙ በመደብና በክፍል ተከፋፍለው ስንመለከት በጥቂትና ከፊሉን ብቻ እንደሚከተለው እናገኛቸዋለን፡-

## ኮአታን ኮአት(ሑለትዮሽ)

1. ኩዴ ከፈር ያሌይ
2. ሐፎት
3. ሰፍፎይ
4. አሚሬይ
5. አብባ
6. ተስ የለሽ ሀረሬይ
7. ራሐ
8. ዋሊዮይ

## ጃሊዬይ (የልብ ወዳጅ)

1. ሙጥጢቤ ያሽዛል ጃሊዮይ
2. ጉዶር ጃሊዮይ
3. ዊረጅላ
4. ነለሺ
5. መስኖይ

# በለቹ ፈቀራች(የሰርግ ዘፈኖች)

## ዘገን ከረቡ

1.አዋይ መካ ሐሮው

2. ዋትቲ አሩዝዋ ቤልቲ አሩዝዋ

3. ቢቀይማ ሼሽኚ

4. ቢስሚላ ዶኝ

5. ጌይሌ

6. አው አባዲር ወልዳች

7. አውወል ፈለኬይ

8. ባዴ ሀረር ዱፍዜ ደዌይ

9. ሉሙ ሌይሙኔይ

10 .አኪዮ ሚላኪይ

11. ሀረር አማተሺዋ

12. ነይ መዲዋሎው

13. ያወዱድ ኢማን አልቢሰና

## አያች ከረቡ

1. ያነቢይ/ሜገልዞ/

2. ደልሲ

3. አኑዝ ሀረር

4. ዳዋ ነቢ

5. ሼለሜው አልላ

6. ነቢ ደዎው

7. አፌ ሰለላ አሌይካ

8. ነቦ ዲጁዌይ

9. አሰላቱወሰላሙ አላ

10. ኢናችሌም አልላሁ ዩሸለና

11. ጌሌሌም አሸሌ

12. ሀረኑ ሼለሜማ ሼመቄ

13. አሰላቱ ወሰላሙ አላእ ረሱሉላህ /መቆፋይ/

## አንቀር ማህጠብ

1.ነቢኾ ሲናኑ /ሜገልዞ/

2. ያሸዛል አልላ

3. ኑሮ ነቢ

4. ኑሮ ነቢ /መቆፋይ/

## አልላ አላእ

1. ቢስሚላእ ራህማን ረሂም አማ ኢሳል የቶር አሩዜይ

2. ሐደስ ጫያ አዮባን ሚገር ዛሌ

3. ያሲን ሑጡርቤ

4. ሺፍቱ ጋሎ

5. አይነናር ዛላ አውኻሽ ጌዮይ

## አሩዝ መግባእ /አሩዝ ዚዲጀሳ/

1.ሐይ ሲቺም ዱስ ለሐሺም በሌ

2. ዲጃ በሎ

## አሩዚት ዘመሐዋችዜ ዞጠአሳ

1.ዚሰፍታ ዚከመልታ ማን የጦርሌ

## አሩዚት ዞጠቲሳ

1. አው ቀሐቴይ

### ጉፍታ ሞገድ

1.ቢስሚላ ራህማን ረሒም/ሜገልዞ/

2. ሉላ ወከሌ

3. ሚዱው ቲርጊር

4. ጉፍታ የዲድ

5. ዲጀሌሻ ዚአበድ

6. ዘር ወረድና ዘራንዘር ወረድነዌይ

አሩዝ መውጣእ

ኢያች ፋታህ

1. አው አባዲር ኑቡቶው

2. ሳዳቴይ

3. አብቤይ ኹጥበ ላይቤ ይትጌቤ

4. አባዮ ቲመስኪን ዚትቴ

5. አቤ ሐርቢሌም ሸዲዶው

6. አባዮ አገማሙ ዚቄሔይ

7. አብቤ ኢልሚሌም ባሀሮው

8. አብባዮ ለፉእ ላይ ጉኑዜ  ወ.ዘ.ተ... በስሩ ይመደባሉ፡፡

እነዚህ ሲዜሙ አብዛኛውን ጊዜ ሴት እና ሴት አልያም ወንድ እና ወንድ  ማለትም በተመሳሳይ ፆታዎች ሲሆን አንዳንድ የዘፈኑ አይነት በሚፈቅድበት ቦታ በተቃራኒ ፆታ ሊዜም ይችላል፡፡




ሩኔይ ሩኔይ አይ ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ(ሻሚቱ) የተዜመ ከ"Ethnomusicological Research among the Harari People of Southeast Ethiopia" Marianne Bröcker የተወሰደ

# 19.3 በጫሬስ ስር የሚገኙ የተወሰኑ የዘፌን ግጥሞቹ

## ኮአታን ኮአት ፈቀር/የሁለትዮሽ ዘፈኖች/

1. ኩዱይ ከፈርያሌይ

ቆባ ኢፋጭሌ ሙሳፊሪን ሌጥኹ

ሚስራ ዋ ሮማ ለንደኑ ወረድኹ

ኢላ ጀርመን ጠረፍ በርሊን አልቀሬኙም

ሀረርሌ ዩቡርዲ አዱኘቤ ኤሉም

ሳፊእ ጀነቲንቴ ሺርቲዜ ዘራንዘር

ኡፋች ኪልበረሩ ያሾዛል ፈቀር

ወዘናም ጠር ይልማ ያዳን ወለም

ላይዞው ይበስሊማ ቢሲም ቀብ ቀብ ይላል

ለፉም ዘው ዘው ይልማ ሀበሪም ይረግፋል

ጌይ ዚቻኸልቲ አያም ያሲንቤ ቼኸሌ

ዘትቲዳመስ ኩታ ፋታህቤ አቀሬ።

## 2.ናፍቆት/ሒፎት

ሌይሊ ዚትቆጨቤ ኡሱእ ዚኜአቤ

ቢርዛዝ ቡርዚዝቲ ኩት ዲሺቢኝ ፊቴቤ

ጋሩ ከፈትኹማ ቃነንኹ አባትቤ

ሀረር ይልዛል ጠባው ሰመኹ ኡዙንቤ

ኢሰክዛኽ ሌ ጥኹ ሌይሊ ዋ ላኡቤ

አላን አሰለጤኝ ዚናብ ዋ መስሪቤ

ተማጀኹማ ዲጅኹጉዶ ዲልዲለቤ

ሚን ሙጥጢ ዪነብሪ ኢሽቂ ሲንሲለትኸሽ

ቃሜ አማኒስታ ቀልቤው መሮጀኸሽ

አኑ የዲንቀኛል ፊዝቤ መትባለልኸሽ

ኡደሻኽ ኪላሺኝ አንቤ መትፌቀርኸሽ።

3. ሐሎይ

ሌይሊ ዚትቆጨቤ ኡሱእ ዚኜአቤ

ቢርዛዝ ቡርዚዝቲ ኩት ዲሺቢኝ ፊቴቤ

ጋሩ ከፈትኹማ ቃነንኹ አባትቤ

ሀረር ይልዛል ጠባው ሰመኹ ኡዙንቤ

ኢሰከዛኽ ሌጥኹ ሌይሊ ዋ ላኡቤ

አላን አሰለጤኝ ዚናብ ዋ መስሪቤ

ተማጀኹማ ዲጅኩጉዶ ዲልዲለቤ

ሚን ሙጥጢ ዱነብሪ ኢሽቂ ሲንሲለትኸሽ

ቃሜ አማኒስታ ቀልቤው መሮጀኸሽ

አኑ የዲንቀኛል ፊዝቤ መትባለልኸሽ

ኡደሻኽ ኪላሺኝ አንቤ መትፌቀርኸሽ።

4.ሰፎይ

ቀጠቡኽ ታሺነሽ አሺዳይ ኢሰተና

ሉህ ዋ ዲቤትዚኛው ኡገቤ ኪልጌኝኔው

ሸህሼራ አፈርቤ መስሳ ተፌቀርና

አሐድ ቶያ አፈርቤ ደዱም ደበልና

አን ደድኸሹ ሪእኾ ሑልሉእ ዛላ መላ

አህዲዚኛ ቢላይ አሩም ዘልበለጣ።

5. አሚሬይ

ወር መሬትቤ ደድኸሽ አሸቤኛ አሰራ

ሚን ሙጥጢ ቲነብሪ አላንተሸም ቀራ

አንቤ ሐጂስ አሊታ ደድኸሽ ማንቤ ፈራ

ቀልቤው ጠለፌውማ ጢልሊኩት በረራ

ማልቱ ሒራት ደድኸሽ ኻነቤኝ ሼህዳራ

ሑሉእቤ ደድ ባይቲው ጌይ ኡሱእ የራ

አንሌ ደድኸሺንታ ኢባደ ዋ ሚህራ

ዘነጣውሪ ታጊር ነሌጥ ሚሻ ደውራ

ፈደም ባይቲን ይማጅ በጂሁም ዚጦራ

አኻእ ደዱኽ ሚን ሐል ደድ አወልቤን ቀራ

ዛላእ ሙትቤ ቢላይ መትላያ መልናራ።

6. አብባ

ኤጂኝ ሚን ይነብሪ ተትቢክሊኝዛሽ ሐጃ

ሼኽ ከራት ወሰኑ አሞሴኝ መትማጃ

ደድ ኸሽ በስሐቤኝ ላኪን አልላ የፍጃ

ማንታ ዪ ዘማንቤ ዚታው የሲሚዛል

ወንደል ገርገብ ቢላይ ማንታ ሐቅ ይምዲዛል

መትዋደድ ኪልሒቤ አህዲ ይመልዛል

አኻእ ዛል ኡሱእ ባሕ ሐቅ ሜዳ የትቃብጣል።

7, ተስ የለሽ ሀረሬይ

ቃጪ ኑሐሪማ ዋ ኑ ኹኒቤ ኑግዳ

ሀረርቤ ነሳመት ኢኺይ ጉማኩታ

ኩዱኽ አጥ ኻነማ ራህመቲን ቀበጣ

ማወርዲ ኤለድ ቆርኸሽ ቀልቤቤን በቀላ

ዳጉው ኪልወረድኹ ኢቢእ ዪትኮበኛል

ማኑእ ማኑእ ኢላእ ማኑኡኽ አሲማ

ራህማኒን ፈረዴው ሀረሬይ ኡሺ ሰብሪ።

8.ራሐ

ማንሌ ኢምዲማ ማኑኽ የሰመአና

ማንሌ ኒበክማ ማን የትረሐምለና

ሐፍ በይ አሌጪና አባዲር ዚያራ

ባሳ ዘኑጭኩታ አወልቤ ዚናራ

ኤለሽ ሰብሪ ኡሺ አልላ ይልቄሲዞ

የሸ ቀልቤ መፍቻህዞ ኢላዞቄስሲ

ሐንቲኸሽ ዩኹንኩት አጭለሻኽ ሑጃዞው

ኡፍሌ ዚሶቻዊን ዱስቦሖል ኪለፍዞ

ኡፌሌ ሶችሺኝማን ኤሰብኹሽ ኪለፌዞ።

9. ዋሊዮይ

ቃሜቤ ዚቆጬ ማልታኩት

ዘልታው ባኹጊሩም ያህዘዥ ሚራቂ

አኻሺንተሸ አልሌ ኦርኩታረፈቂ

ሩሑቅቤ ኡደሽሌ ራዲመልታ ቀልቤ

ኪልሰቹ ቲጢሜይ አባዲር ዘሪኔይ

ሐርሻችዜ መስኖይ ኡሩስ ጌይ ጀነቴይ

አወባዲ ጌዩይ ወሊ መዳበዩይ

ዚትወለድነማ ዚሌቅነቤው ባዴይ

ባዴ ሀረርቤ ተላይ ባዩኝጊር

ነሐስ ሚን ኢሰኻና ዚቄህ ዩኹኒጊር።

10. መዲ ዋሎይ

ዛል ዪቀብጢማ ዘሌላን የገኛል

ሰላት ቤሔሪንታ ፈረጀት ዩኹዛል

ቱጃር ቀበጠጊር ጂናሚን ዩኹናል

ሚስኪን አገኘጊር ተስቲቤን ይሙታል

ዛላ ዘሌላሌ ሚንሌ ራህመት አዩሸ

ይሙትቦ አዱኚትሌ ሲሲት ምሻ ሚን ዩሸ

አዱኚት አታላይ ዋትኹ ሐልኹ ቲልዛት

ሖጂ ቲቢርኒማ ጊሸታኝዞ ቲጪልማት።

11. ሀረር አማንተሺ

ሰብሪ ሲሪንታ ባዩ ኡማችዚኛ

ፈረቃ ኤቀብና ጢልላ ቀዳህና

ሀረር ዘጋሒንቴ ታብሉሜትዋን ወቪላ

ሙሉህ አፈር ሐሌ ታብሉሜት ዋ ፈፍሪካ

ጌይ ወልዳች ሲሙኡኝ ኡዙንኾዉ አሌህቁኝ

ባድ ኻድቤ መትላያ አዱኛ ከፍቲንታ

ሲሙ ሀረረያች አልቲኤናም አዞእ አያም ጪንቂንታ

ባድ ሀልጊሪን ሳሎይ ባድ ሐልጊሪን ቪላ

ቃጪ አየቆምሰና ሲሙኡ ሀረሪያች ባድ ኻዲን ይማጃልማ

አሐደ አየፍራረሸ አልላንታ

ሚይ ሰችነጊሩም ኩዴይ ደድ ሶሪንታ

## ከባህላዊ ጌይ አዳ ፈቀር ዘፋኝ ከአሚና(ኢኽስታ ጊኒ) የተገኘ

## ዊረጅላ

ዊረይላ መዲዋ - መዲ ደርሜይ ዊረጅላዋ

ዊረጅላ አልላ ዛዬው  - ቢላይ መዪኹኔል

ሲናን አጀል ኢንተ - አጀል መኽቱብ ኢንታዋ

ጃሊዬይ አልላ ዚፈረዴው ዘይቂር ኢንታ

አልተበኙም ዪሎቤ - ዪሺማመቆቤ

ዞደዶሌ አን ኢንተኝ ባይቲን ዪማጅ

ከዪሺማመቆቤ ዋ ጃሊዬይ

ተስ ታሸዛት ተጋሪ ሐራሻች ገደሌዋ

ዘላቄቤ ገደብቤን ቀበሬ

ከተስታሸዛት ተጋሪ ዋ ጃሊዬይ

አሬይሌ ወር ኢሳሌ - ወሩም ኤለኝ ቲላትዋ

ነቢ ሙቱው ወሩም ኤለኝ ቲላትዋ

ከቲትፈቃቀራትዋ ጃሊዬይ

ነቢው ኒሊዛና ኒትፌቀሪዛና

ነቢሌ ጌይዚዩ ኑሑሪዛና

ከኒትፊቃቀሪዛና ዋ ጃሊዬይ

ጨለንቆ ጨል ያሻል

ወራበ የትቢላል

ጨለንቆ ጨል ያሻልዋ ጃሊዬይ

ነቢው ባይቲዚኛ ሐል- ነቢው በይሊኝ አርራቴ

ወልላሒ ከይሲ አይዴጅበሽ - ተውባ ሙት ሚራቴ

ሙት ሚርራት ሰኸራት ዋ ጃሊዬይ

## ጃሊዬይ

ቢስሚላ ዶኻዚኛ - ያሲን ሑጡርዚኛና

ነቢው ባይቲ ኢኝኘሌ ሐልዚኛ ሐላ አመልዚኛናዋ

አልለዮው ኹንለኝ - ረቢዮው ኹንለኝ አንሌ

ኢንሻ አልላሕ ከአዩም ወልዲዜሌ ቱኹንዛትኩትዋ

አልላም አይላየና - ደዱ የድበለና

ዚዳበሌና ቁድረዞቤ መስሳ የንቢረና

ዘይቲቆጭ ቀላዶው - ዘይቲሰበር ኢንጪዮው

ከተጥለጠልነቤኽ ዋ - አተምራስጠና

ሙቱም ሐልበና - ሙራዱም ሐልበና

ዘይቂር ሙቱ - ኸይሪ አያም ኡሸለና

ሙራድዱ አቅዲምለና

ነቢ ሐርዳው ነኼጅ

የሊጣል ዘማንዋ ዱርገብጌል ዘማንዋ

ኪልሐደሮ - ጠባን ዱዲእፋልዋ

ዋዬልነት የዲጃል

ሲፍ ነጦርመ ሚን ጀሐድ ነሞት

ሑሉፊት ዱላል - አይሔጅበና

ሑሉፍ ዘየሊው አየዴጅበና

ማወርዲ ነቢ ቦራ

ነቢው ኒልማ ሱት ጀነት ኑቡአ

ነቢው በይ አርራቴ  ኢሰይዴጅበሽ ሙት ሚርራት

ሙት ሚርራት ሰኸራት

# ነለሺ

ነለሺ ነለሺ ነለሺዋ

ነለሺ አንዳብሊበሺ

ማገት አፍ ረሐኔይ ነለሺ

ኤለዳቾሌም ሙሉሔይ ነለሺ

አውዜሌ ሰላቴይ ነለሺ

አይዜሌ ሰባቴይ ነለሺ

ነለሺ ነለሺ ነለሺዋ

ነለሺ አንዳብሊበሺ

መካ ጋር አፈሬይ ነለሺ

አፈርሌ ሙሉሔይ ነለሺ

አይዜ ጪን ሐንቆቴይ ነለሺ

አውዜ ጋር አሳሴይ ነለሺ

ነለሺ ነለሺ ነለሺዋ

ነለሺ አላይዞም አየለሺ

## ደድሌ ደድሌ (ደርሲ)

ዱመሲዛል፡- ደድሌ ደድሌ --------- ዱላሕዲዛል፡- ዋሳኒን ሐላዋ ጃል

ከኢሕ ደድሌ -------------------- ዋሳኒን ሐላዋ ጃል

ከኢሐት ደድሌ -------------------- ዋሳኒን ሐላዋ ጃል

ከአሩዝ ደድሌ -------------------- ዋሳኒን ሐላዋ ጃል

ከመሪኝ ደድሌ --------------------- ዋሳኒን ሐላዋ ጃል

ከባድ ደድሌ --------------------- ዋሳኒን ሔላዋ ጃል

ከአይ ደድሌ ---------------------- ዋሳኒን ሔላዋ ጃል

አሩዞው አሩዞው --------------ጃሊዬይ አሩዞው አሩዞው ዱርራ ኡፎው

ቲመልካኝዞም ጃሊዬይ -------------------- ሳምዞ ጋርቤም አሩዞዋ አሓ

አሩዜይ አሩዜይ ---------------- ጃሊዬይ አሩዜይ አሩዜይ ዱርራ ኡፌይ

ቲመልካይዜም ጃሊዬይ --------------------ሳምዞ ጋርቤም አሩዝዋ አሓ

ሼልመና ሼምቀናዋ ---------- ጃሊዬይ ባዱ አቦርደናዋ አረብ ኢኹይኩት

ጀካሊዬይ -------------------- ባዱው አቦርደና ሹሉማት ባሕ አሓ

ዘማን ዱሊጣል---------------- ጃሊዬይ ዘማን ዱርገብጌልዋ

## ኪልሐደሮ ጠባን ዪዲእፋልዋ

## ዋዬልነት ዪዲጃልዋ አሓ

አልላም አይላየናዋ ----------------------- ጃሊዬይ ደዱ የድበለናዋ

ዪ ጎይቴ ቀድረዞቤዋ አሓ

አማኔይ አማናዋ -------------------- ጃሊዬይ አማናው አማኑው

አን አኻኹ አማንዋ

አሰሎ ከራትዋ ---------------- ጃሊዬይ ወረዳ ከራትዋ ነቢ ያጩኛል

ኢሳት መስሪ ወለገትዞቤዋ አሓ

ሐርቢ ጁገልዋ ----------------------------ኹጥበቤ ዪገድሪዋ

አሩዝ ደድሌዋ ----------------------------ተማጅኹማ ዲጅኩዋ

አሩዚት ደድሌ --------------------------- ተማጅኹማ ዲጅኩዋ

ኢጃብ ሚስቲጃባ --------------------------- ጃሊዬይ ኢጃባ ሚስቲጃባ

ጃሌይ-------------------------------- ሳተልሐጃብ ሔጅ ዘሌልባዋ አሓ

ኢስታኽፉሩላህ ነልዋ ----------------------- ነቢው ነልማ ነፋይዋ አሓ

ነቢው በይሊኝ አርራቴ---------------- ኢመይዴጅበሽ ሙት ሚርራት

ሚርራትዋ ሰኸራት አሓ

ጃሌይ--------------------------------------------ጃሊዬይ

# ሒና ሞገድ (ሂና መቀባት)

ሚስሚላሒ ረሕማን ረሒም

አሊ ዊሳቶው ኖ አሩዞው

ሐዲስ ሚያ አዮባን ጉጃጅ ዛላ

አዌ አውኸሽ ጌዩ

ያሲን ሑጡርቤ ተባረክ ሚጋር ዛላ

አዌ አውኸሽ ጌዩው

ያሲን ሑጡርቤ ተባረክ ሚጋር ዛላ

ጉፍታ ሞገድ

ሚዱ ዲርጊም

ሚዱ ቲልጊር አርበ ሚዱ ነዲጄይ

ሚዱ ቲልጊር አርበ ሚዱ ነሺኔ

ሲሮይ ከላም ሐዩይ

ሉላ ወሰላ ሉላዜም ሐዩይ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔሽዋ ዚቄሕ ሊጂ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔኸዋ ጉፍታ ሙዳይ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔኸዋ ሳሒል ወንጠፍ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔኸዋ ሰሊጥ ማሐሻ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔኸዋ ደሐብ ወንጠፍ

ጉፍታ የዲጅ መጋለዮው  ዛላ ኸይራትዞው ሰጥኔኸዋ ሳትቲ በቅላ

...............

# 20. ደርሲ

ደርሲ በሌላ ስያሜዎችም ይጠራል ከነዚህም ውስጥ

“ሱሙት ፈቀር”(የህብረት ዘፈን)

“ሙጋድ ፈቀር”(የቡድን ዘፈን)

“ዱሙቲ ኪህሊ ፈቀር”(የስምምነት ዘፈን)

“ዳይ ፈቀር”(የጋራ ዘፈን)

“ሳይ ፈቀር”(ተድላ ዘፈን)

“ለከኩ ሐጃ ፈቀር”(የጋራ ጉዳይ ዘፈን)

እየተባለ በተለያየ ስያሜዎች ይጠራል፡፡ ይህ የሚዜመው አንድ ነጠላ አልያም በውስን መሪ ድምፃዊ ተዜሞ ብዛት ባላቸው ተቀባዮች(Chores Group) የሚዜም ሲሆን ይሕን ለማዜም በተመሳሳይ ፆታ አልያም በተቃራኒ ሁለት ፆታዎች ሊዜም ይችላልእንደ ሚራስ በስሩ በርካታ የሙዚቃ ስልቶችን የሚይዝ ሲሆን ከሚራስ የሚለይበት በሁለት ሰው የተወሰነ አለመሆኑ አንዱ ነው፡፡ደርሲ በአንድ ሰው አልያም በህብረት የሚዜም ነው፡፡ከዚህ ባሻገር ደርሲ በስሩ የሚገኙ የዘፈን አይነቶች ለ “ደባል” (ለዳንኪራ) የሚጋብዝ ነው፡፡በዚህ ስር ጠቅለል አርገን ልናየው የምንችለው ሐይማኖታዊ ይዘት ያለው ዚክሪ(መዘከር) /devotional chant /ነው፡፡ ዚክሪ ራሱን ችሎ ቢዙ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ ቢሆንም እንደነጣላኒያዊው ዶር ሲሞን ታርሲታኒ በዚክሪ ላይ ጥናት ያደረጉ ሲሆን በይዘቱና በአይነቱ የጋራነት እንዳለው Zikri rituals in Harar, Ethiopia በሚለው በጥናታቸው ያስረዳሉ፡፡ ይህ ማለት የዘፈኖቹ ምት ለውዝዋዜ የሚጋብዙ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት ደርሲ በሑለት ይከፈላል፡፡

1- ነሺዳ

2- ዚክሪ

3- ደባል ፈቀር ናቸው፡፡

## 20.1 ነሺዳ

በቃሉ ትርጓሜ ስንመጣ መዝሙር ማለት ሲሆን መዝሙር ያለ መሪ ድምፃዊ እና ያለተቀባይ ሁሉም በጋራ የሚያዜሙት ዜማ አልያም ዘፈን ስለሆነ ከዚሁ ትርጓሜ ጋር በማያያዝ ነሺዳ እንለዋለን፡፡ይህን ነሺዳ በብዛት የምናገኘው ሰርግ ቤቶች ላይ ሲሆን ሁሉም በጋራ ሙሽራና ሙሽሪትን በህብረት የሚያወዱሱበት የቅኝት ንኡስ ክፍሉ ነው፡፡

## 20.2 ዚክሪ

ዚክሪ ከቃላዊ ፍቺው መዘከር ማለት ሲሆን በዚህ ስርም መንዙማ እና ተጨማሪ ዘውጎች ያላቸው ሐይማኖታዊ ሙዚቃዎችን ጠቅልሎ የያዘ ነው፡፡ያሉት ሲሆን በዚህ ላይም ጣሊያናዊው ሲሞን ታሪስታኒን(ዶ/ር) የመሳሰሉ በዚሁ ላይ ጥናት ያደረጉ ሲሆን ሲሞን በጥናቱ በዚክሪ ውስጥ ያሉትን የከበሮ አመታት ባጠናበት ወቅት ቻላ አልያም ምት ወይም Beat ምንነቱን እንዲሁም ክፍሎቹን ቢት ባር ጠንቅቀው እንደሚያውቁ በጥናቱ ጊዜ ገልፆዋል፡፡ሲሞን 478 ገጽ I rituali musicali dello zikri a Harar, Etiopia በሚል ርእስ ያቀረበው ጥናት ላይ ገና ብዙ መዳሰስ ያለባቸው ርእሰ ጉዳዮች በዚህ የሀረሪ ዚክሪዎች ውስጥ እንዳለ ይዳስሳል፡፡ Depeche Mode አልያም በአማርኛ ተመጣጣኝ ምሳሌው እንደማህሌተ ገንቦ ዘውግ የሚሰራ

አለፍ ሲል በድምፀት ብቻ የሚንጎራጎር ሆኖ ሊሰራ ይችላል፡፡ ነገር ግን ምቱ እጅጉን የተለየ ነው፡፡በሙዚቃም ሆነ በተቀረው የማይታይበት ተደራራበኒና ተለዋዋጭ እንዲሁም ቻላ(ምት) በተለዋወጠ ጊዜ ወደ ጡዘት ሲጠጋ ውስብስብ የድምፅ አቀራረብ /Colotomic ዘውግ/ ይይዛል፡፡ ዚክሪ እጅጉን የሰፋና ከፍተኛ ጥናትን የጠሚሻ ሲሆን በከበሮ ምቱም ሆነ በዜማ አጣጣሉ ላይ እጅጉን ለየት ያለና ስፋት ያለው በመሆኑ ጠለቅ ብዬ ለማስቀመጥ አልደፍርም፡፡ዚክሪ በሱሙድ ፈቀር ስር መካተቱ ለማዜም የጋራነት እና የተናጥል የህብረ ድምፅ / ፎር ፓርት ካኖን / የቡድን ቅብብል ስላለው በመሆኑ ነው፡፡



## ያ ሐቢበላሕ

ረካ ናሸባ ዚናራ ወቅቲቤ  ዞጦአቺ ንዩ፡፡”
ኢሳዩኝ ቤሔር ዚክሪ ሞሽ ኤገሉ፡፡
ሶቼኝ ነቢ ቦር ሚስኪዋ አንበር
ሐበቅ ሐበቅ አሼኝ አላሁ ወክበር
ነቦው ነቦው ባይቲ  አን ኻነቤኝ አዳ
ኢንሽአላህ ኡሑራኽ ዛሉቦ ባዳ

ሽለላ ሼሕኽ አባዲር
አው በሀር ሼኽ አባዲር
አው በሐር ሼኽ አባዲር
ቢስሚላሒው ነቀድማና
አልረህማኔው ኒደብላና
አልረሒም ነልማ ኒግላና
አው በሐር ሼኽ አባደር
አልሚዱና ኪታቡ
አኽፊፍቡና ተአቡ
አጥፉቡና ኢሳቱ
ጉታዚኛቤ አዋ ዋቱ
አው በሐር ሼኽ አባዲር
አልሎው በለና ሐምዶኛ
ገርገብ ሼኽ ሐለና ጦኛ
አልላሑ አዚዝዛ
ሙመድ ነቢ አዚዛ
ሙዕሚኑም አዚዛ
አው በሐር ሼኽ አባዲር

አሚን ያ አላህ  ተቄበለና
ነቱዋ ነዙቤ አልሎው አስሊጠና
ወረምዋ ረሐብቤ ነ'ጃ'ት አጬና
ሳሚዕ ኢላሒዮው ሲመአና
ዘዩቀ'ኹ አትጊፈርበና
አውፊ ረህማው አውፊ ኡሽለና
ዲልሒዚኛውም ፈደም በለና
አሚና ያ አላሕ ተቄበለና
አ'ኻ'ኸ ጪልመቤ ዛጭ'ኸና
ዩይ ዚ'ኻና ኡምመትዞዛሽክና
ኩሉ ገሱስቤ አልሎው ኤውለና
ደድ'ኻ ዛልበያችባሕ አልሎው ዳብለና
አሚን ያ አላሕ ተቄበለና







ዲጂታላይዝድ የተደረገ አጀሚ ዚክሪ ማኑስክሪፕቶች

## 20.3 ጾባል ፌቀር

በአንድ መሪ ድምፃዊ እየተመራ ቀሪ ዘፋኞች አልያም ሰዎች በተቀባይ ድምፃዊነት ከስር እያጀቡ ይከተሉታል፡፡ ነገር ግን እንደ ሚራስ ከአፍ ላይ ስንኝ መንጠቅ አልያም መትቃፈጥ የለውም፡፡ይህ ክፍል በሙዚቃ ስልቱና በግጥም አደራደሩ ለደባል ማልትም ለውዝዋዜ የሚጋብዝ ነው፡፡

አሩዞው አሩዞው ቲለኽ ናርቲ አይኻ

ዚቄሕ ተኮአቤ ኢላ ኢጊር ጢፊርኻ

ቶያኻ ጩራንጩር መኽቱት ኤላ ጪልማ

አበድ ኢቀርበኼኽ አልላው ኢላሕዲማ

አሩዝ ባይቲ ተስቲ ሲዲስቲ ደረጃ

ከዛቄው ኡሱሌ ሱት አልፊ ደረጃ

አሸሌኽ አልላሁ አሸሌኽ

ዪ ቂጤ አሕላችኻባሕ አልላሁ ዳበሌኽ

አሺት አሩዜይ

አሩዜይ አሺት አሩዜይ

አሩዜይ አሺት አሩዜይ

ሐልዜ ሐላዋ አመልዜ ዱሴይ

አሺት አሩዜይ

ኡኩም አልመስሌኝ ጠሊላ ዱሴይ

ዪመሽ ሚሼት ዪዛኝ አልመሰሌኝ

ሐልዜ ሐላዋ አመልዜ ዱሴይ

አሺት አሩዜይ

ኢሳዩ ቤሔር አትኼተልኹማ

አሩዙም ዋቲ አሩዚት ቤልቲ

አሩዙም ዋቴ አሩዚት ቤልቲ

ነትፌቀርለዩ ሳቲ ለሳቲ

በደርሲ ስር የሚካተቱት የዘፈን አይነቶች መሐከልም

-አንቀር ማሕጠብ

-ጉፍታ ሞገድ

-ነቦው ሐይነቦው ይገኙበታል፡፡

# 21. መስኖይ

መስኖይ የመፀሐፍ ስም ሲሆን ይህ መፀሀፍ ማኖስክሪፕት አጀሚ ነው ፡፡ ይህም በእጅ  በአረበኛ ፊደላት በሀረሪ ቋንቋ የተፃፈ ነው፡፡ ከ200 እስከ 400 የሚደርስ እድሜ አለው፡፡ፀሐፍው አንድ ሳይሆን በበርካታ ፀሐፊያን የተፃፈ ነው፡፡



መስኖይ እና ኪታብ አል ፈቀር መፅሐፎች ላይ የተወሰደ

የሚወሳውም አንዲጥ ሴት ለትዳር ከታጨችበት ጊዜ እስከ ወንዱ ቤት እስክትገባ ያለውን ሒደት የሚያሳይ የዘፈን ግጥም መድብል ነው፡፡ እ.ኢ.አ.በ1949 ዋልፍ ሌስ ልዎ የተባለ ስለ ሀረር ታሪክ ሲፅፍ የአው አህመድ አሊ ሻሚ ስብስብ የሆኑትን እነዚህን የመስኖይ ግጥሞች እና ሌሎችንም ጨምሮ "CHANSONS HARAR"በሚል ርእስ አንድ መፀሀፍ ለንባብ አብቅቶ ነበር፡፡

ፀሐፊው ዋልፍ ሌስ ልዎ የመስኖይን ግጥም ይዘት ሲገልፀው፡ -"የሀረሪ መስኖይ ፍቅር፣እና ውበትን የሚያወድስ ሐይማኖታዊ ስሜት የተላበሰ መግለጫ መሆኑ ስለ ማሕበራዊ ሕይወት ትኩረት የሰጠ ስነ-ግጥም ነው፡፡"ስል ገልፆታል፡፡(የሀረሪ እና የሀረር ከተማ ታሪክ በአብዱላሒ ሼኽ አህመድ ቡህ 1998ዓ.ም ገፅ112)በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ በከቢር ኡመር አብዶሽ የተፃፈው ኪታብ አል ፈቀር የመስኖይ የግጥም ድርሰት ሌላው ምሳሌ ነው፡፡

ብዙ የታሪክ አዋቂዎች መስኖይን እንደቅኝት አይመለከቱትም፡፡ ምክንያቱም መስኖይ መጻሐፍ ስለሆነ ባዮች ናቸው፡፡ አው መስኖይ የሚባለው የመጽሐፍ ስም ነው፡፡ ታዲያ ይህ መጻሐፍ ምንድን ነው?

መስኖይ ከሁለት መቶ አመታት በላይ ያስቆጠረ ማኖስክሪፕት (በእጅ የተጻፉ) ሆኖ አጀሚ(ፊደሉ የሌላ ቋንቋ ቋንቋው ደግሞ ሌላ ሲሆን) ነው፡፡ ይህም ጠቅልሎ የሰፈረው በርካታ የግጥም መድብል ነው፡፡ ፀሐፊውም አንድ ሰው ሳይሆን እጅግ በርካታ ፀሐፊዎች የተሳተፉበት ነው፡፡ ‹‹መስኖይ›› የሚለው ቃል ከሱማለኛ ቃል የተወሰደ ነው የሚሉ ቢኖሩም እውነታው እና የሚያስማማን በሀረሪ ቋንቋ

‹‹መስኖይ›› ማለት በሚይ መላቅ (ውሃ ቀያሽ) ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተቀይሶ ወደ እርሻ እንዲወርድ የሚከፈተው ውሀ መስኖይ ይባላል፡፡ (ምናልባትም ከተለያዩ ገጣሚያን ግጥም ስብስብ የተፃፈው መጽሐፍ እንደውሀው መስኖይ አልያም መድብል በመሆኑ ይሆናል፡፡) ሌላው እውነታ መፅሐፉ የሀረሪን ባህል የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ቃሉ በሀረሪ መሆኑ እንደማያሻማ ያሳየናል፡፡

የመስኖይ ግጥም አንድ መጽሐፍ ሳይሆን በርካታ መጽሐፎች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ባሁኑ ጊዜ መስኖይን ግጥም ባጠቃላይ ለመሰብሰብ ያልተቻለው፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ፀሐፊያን የታሪክ ሙሁራን ስለመስኖይ የግጥም አፃፃፍ ተደምመው ብዙ ብለዋል ጥቂት ፅፈዋል፡፡

እንደነ ሌዊጅ ሮቢክ ባለካቲ፣ ዋፍ ሌስሊ፣ ሮቢች ቢሪቸር ሊዊንጊ፣ ካሜላ ጊብ፣ ኤነሪኮ ቸሩሊ መስሎቹ ስለ መስኖይ ግጥሞች ለመናገር በቅተዋል፡፡ ታዲያ ለዚህ ያበቃቸው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ‹‹ኪታብ አል ፈቀር›› በሚል ርዕስ የመስኖይ ይዘት ያለው የከቢር ኡመር አብዶሽ ድርሰት፣ እንዲሁም የአው አህመድ አሊ ሻሚ የመስኖይ ግጥም ስብስብ የሆነው መጽሐፍ በኋላም የሳቸው ተማሪ የነበሩት አብዱልሙሔይሚን፣ በ1988ዓ.ም ‹‹የሀረሪ ጌይ ፈቀር›› በምትል ርዕስ የመስኖይን ግጥም ከአው አህመድ አሊ ሻሚ ስብስብ ወስደው ለማሳተም በቅተዋል፡፡

ንዲሁም አው አህመድ አሊ ሻሚ ልጅ የሆነችው አይ ኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ በሞያ ስሟ (ሻሚቱ) የመስኖይ ዘፈን እናት እስከመባል የደረሰችና ጣሊያናዊቷ ኢላሪያ ሳላቶሪ ዶክትሬቷን በመስኖይ እና በተስረቅራቂ የመስኖይ ዜማ እናት በሻሚቱ ለመስራት በቅታለች፡፡

ታዲያ መስኖይ ከቀሩት ቅኝቶች ልዩ የሚያደርገው በግጥም አፃፃፍና በዜማው ከቀሩት እጅጉን የተለያየና የራሱ የሆነ ስልት ያለው መሆኑ ነው፡፡ የመስኖይ ዘፈን የውዳሴ አልያም የሙገሳ የሰርግ ዘፈን እስካሁንም ድረስ እየተጠቀሙበት ይገኛል ‹‹ቆሰ ፈቀር›› ‹‹ሽሙጥ ዘፈን››የሚባል ነበር፡፡

ይህ በሽሙጥ የሚዜም የዘፈን ዓይነት ሲሆን ባሁኑ ጊዜ ሲጠቀሙበት አይስተዋልም፡፡ ይሔ ዘፈን ሀረሪዎች ቅኔ የላቸውም ለሚለው ጥሩ አድርጎ መልስ የሚሰጥ የዘፈን ዓይነት ነው፡፡

ሀረሪዎች ባሁኑ ጊዜ ቅኔው ቅኔ ሆኖ ቢቀርም በመስኖይ ዘፈን ውስጥ የቅኔ አሰራርና አገነባቡን ጠብቆ እጅጉን በወዛ መልኩ የሚገኝበት ‹‹በቆሳ ፋቀር›› ውስጥ ነው፡፡ ይህን የተረዱ የታሪክ ሙሁራን ጥናት እያደረጉ ቱሪስቶችን መሳብ ይችላሉና አሁንም እንስራበት እላለሁ፡፡

## መስኖይ

አልላው ፊሩ - ዱላል ዌይ

አልላው ለሐድ መሪኞው

አልላ ጎይተሬ - ማህሪዋ

ሱም ዘልነሰአ - ሰዱም ዱነሴልዋ

ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባዋ

ጠይ ሰሪቤ ወራባ የግበባዋ

ኢንዜማኩሑሌይ - ኢለሻኽዋ

ጪንማ ቀጪኔይ - ኢለሻኽዋ

ፈንከዜ ዱላሎዬይ - ኢለሻኽዋ

ማወርዲ መለሴይ - ኢለሻኽዋ

ኢመይጊፈሮ ዩሩጥዛል - ቀድራ ሲፈቤዋ

ሰላመት ኡጨነዌይ

ቁብዜማ ቀጪኔይ - ኢለሻኽዋ

አጥራፍዜ ጉዶሬይ - ኢለሻኽዋ

ቲንፋሽዜ ሚስኪዬይ ኢለሻኽዋ

ሲንዜማ ሱኩዬይ - ኢለሻኽዋ

ከከቡር ኡመር አብዶሽ መስኖይ መጽሐፍ የተገኘ


شاش جذبي أحد حشاش زلبلبا
شاش وسيفني أحب بلغي زليلبا
شاش دبابي أحن رحس زليلبا
شاش علمي أحن خدام زلبلبا
بجرا نجر سيفني أفنل محدوبي دنججع
ورج جمعين إسحرن جمعن زالبا
طإفروجمعين إسحرن حبر زالبا
نجد برخ يانا برخ نو نخوا
الله بلاي إيلن وس ككيبلا
الله فري وأيلخ دعاء أونلي
حبوا طر بنز زال حل جاف
عرفانك ا نجوجنوا منابروا ٢
بنفنا نفينا نبوت نلوا
محمد رسول الله أستغفر الله
قطن أوت بقلب يا إلرحي
والله والده إبلا ولد به إيلا
طادونز وفرضينا جاف بلسلبي
أنجنا ألنا زمانا عرفن الرحمن

የመስኖይ ግጥሞች

(ከአቶ አብደላ ሸሪፍ ሙዝየም የተገኙ)

قَمَرَ آوزَى شَاشْ وسِيفْ زَلَدوَ

قمَرَ آوْزِى شَاشْ دِ بَايِ زَلَاوَا

عِلْمِى زَلَاوَا

الظلم طِرَقَا جُدُ بَرْسَا وَرَاذِبِى

أَحَبِّ آمِنْبِى أُسِرَا كُعُتْ وَرْجِبِى

أَحَبِّ لُعَبِى أُسِرَا كُعُتْ طِبَا فبيوا

آ نحوا نجدانا كيسما ننا

أُنحوا صَبَبْنَا صابِرِينَا

يِسِنْ زُنبلاَ صَبَّبِي دُعَاءَ إِبلاوَا

سَأَنْ بَقَلْ فَحِبَّتِى نُوْدُزُوْ يُوظِعوَا

جُوجْ جُوجْ نحِدَ ابَاء إِنحِتُّوا

لِي ورأمِنفناى وحَسَنَنَا تنشوّ

لا اله إلا الله دنح إبليوا

نف يد يجروا

الله أُحَدِينَا وَاجِدينا

أَحَدْ نَنْزُوْ وَاء قُوتُو إِلا الله

أَنْبِيَاءُ لِي دُو رَئِيسُو وَرَزُوْ دُوسُوَا
نَبِيَ عِزْ بِسَاطِي فَانَنُوهُ مُحَمَّدًا

〃

نَبِي عَبدِ المَكُولُو مُحَمَّدُوَا
نَبِي صَاحِبُ العَرْشْ زَوجُ عَائِشَا
نَبِي بُقَلْ سُرُورِي فَنْكَرِ بُجِي نِبُوَا
نَبِي مُرس خَيْرِ وَنُوحِمز وبيوا
حَمد وا أحمدوا أحمدبنا اللهى لي حمدينا

〃 〃 〃 〃

〃 〃 〃 〃

〃 〃 〃 〃

〃 〃 〃 〃

〃 〃 〃 〃

..مى وروا بدرٍ إنجليغوا

أَنْ أُخَاخُوْ إِجِيسَا نُجِيسَا
تَاالله أُتَفَاطُوزِ إِنَّا حَاجَاوَا
رَتِمْشِكِيْن حَاجَ
أَنْطَفُلُو فِرَاشَا زِنُوزْ فِرَاشَا
بِلِيل حَاشَا 〃 〃
أَلْفُ لَامْ كُتُبُ زَالنَّبِي اللهُ سَطِيبِنَا
زِنُوزْ أُفْرَاس زَالَتَ مِنَّا بِقُومِسِ
نَبِي خَانُوا إِمَامْ اللهُ فِلِي حَمْدِي
دِينُهْ خَانْ تَمَامْ 〃 〃 〃
كَافِرُمْ خَانْ إِسْلَامْ 〃 〃 〃
نَبِ أُمَنْ خُنُوتُلِي اللهُ وِلِي حَمْدِي
زِجَا بَجَلِي هُمرِ رَحِينَا 〃 〃
زِجَا حِشلا مسِيوُ نُورحِشَاما
دَذْ نِي أُنُورْ دِينُوا اللهُ نِي حَمْدِي

# 22. ጌይ ሰዳ ፌቀር ዊቂር ቃ ም /የሀሬሪ ባህል ዘፌን የግጥም ይዘት/

የሀረሪ ባህላዊ ዘፈን በቅኝቱ ብቻ ሳይሆን በግጥም አፃፃፉም ልዩነት መፍጠር ችሎዋል፡፡የራሱ የሆነ የአፃፃፍ ስልትና አካሔድ ያለው ሲሆን በግጥም አደራደሩም የራሱን የስርአት ፈሰስ ተከትሎ የሚወርድ ነው፡፡ከባህላዊ የዘፈን ግጥም አደራደር ስንነሳ የተለያዩ አራት ክፍሎችን ይይዛል፡፡እነሱም

| |
|---|
| አላህን የሚያወድስ ስንኞች |

| |
|---|
| ነቢን(ሰ.ዐ.ወ.)የሚያወሱ<br>እና የሚያወድሱ ስንኞች |

| |
|---|
| ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት<br>የሚገልፅ ግጥም |

| |
|---|
| አላህን የሚያወሱ ስንኞች |

ከዚህ እንደምንረዳው አብዛኛው የሀረሪ ባህላዊ ዘፈኖች ጅምራቸው አላህንበሚያወድሱስንኞች(ሚጊር)ይጀምሩናበመቀጠልም ነቢ ሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ.)የሚያወሱ አልያም የሚያወድሱ ስንኞች (ሚጊር)ይሉና በሶስተኛ ደረጃ ማስተላለፍ የተፈለገውን ሐሳብ ለምሳሌ ፍቅር፣ጥላቻ፣ትዝታ፣ናፍቆት፣ሐገር፣ወ.ዘ.ተ...የፈለጉትን ሐሳብ

በማንሳት ካዜሙ ብሐላ መዝግያው አልያም መቋጫው አላሕን አልያም ነቢን (ሰ.ዐ.ወ.)በሚያወሱ ስንኞች አልያም በንሰሐ ስንኝ ይዘጋል ይጠናቀቃል፡፡ከዚህ በኋላ የሚዜሙ ዘፈኖች ከማሐል(ከመልአከቱ) ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡

## 23. የጌይ አዳ ፌቀር ሙዚቃዊ ቴክኒኮቹ

በዚህ ምእራፍ የሚጠቀሱ አልያም የሚሰጡ ትንታኔዎች ባጠቃላይ ለሙዚቃ ባለሞያ ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑ ሙዚቃዊ ቴክኒኮች አልያም ቃላት የሚጠቀሱት በሳይንሳዊው አገላለፅ ይሆናል፡፡

የሀረሪ ሙዚቃ ዲያቶኒክ (Diatonic Scale or Heptatonic Scale) በመባል ይታወቃል ይህ ስኬል በሙዚቃው ህግ ሰባት ቁልፎች ያሉት ሲሆን የሀረሪው ሙዚቃ በተጨማሪነት ግማሽ ቁልፍ አልያም ሰሚ ቶን(7 tone(key) and 1/2 smi tone key) አለው ማለት ነው፡፡

በርካታ የሙዚቃ ባለሞያዎች አልያም አድማጮች ክሮማቲክ ስኬል(Chromatic Scale) አድርገው ይወስዱታል፡፡ምክንታቸው የሀረሪ ሙዚቃው ከህንድ ጋር በጣም በመመሳሰሉ ነው፡፡ ቅሉ ግን የሀረሪ ሙዚቃ ምንጩ ዲያቶኒክ ነው፡፡ሆኖም ግን በሙዚቃው አልያም በዘፈኑ መቀየጥ ፔንታቶኒክ(Pentatonic) ባለ አምስት ቁልፍ(ቶን) እና የራሱን ዲያቶኒክ ባለ ሰባት ቁልፍ በማዋሐድ የቁልፎቹን ቁጥር ወደ አስራ ሁለት ከፍ በማድረግ CC # dd # eff # gg# a a # b ይሆንና ከክሮማቲክ ስኬል (Chromatic Scale) ይወለዳል፡፡ እዚህ ጋ ሙዚቀኞችና አድማጮች ከክሮማቲክ መመደባቸው ፍትሐዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለሙዚቃው ቅኝት ውህድ አልያም የተለያየ መጠቀሙ ቀድሞ በነበራቸው ከአለም አገራት ጋር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ

ትስስሮች ለዚህ ውህደት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

የሀረሪ ባሕላዊ ሙዚቃውን ከፋፍለን ስንመለከተው እንደሚከተለው እናገኘዋለን

1 - ሳሌይ ማይነር

2 - ደርሲ ሜጀር

3 - ደርሲ ማይነር

4 - ደርሲ ሰከንድ

5 - ሚራስ ማይነር

6 - ሚራስ ሜጀር

7 - ሚራስ ፈርስት

8 - ሚራስ ሰከንድ

9 - መስኖይ ሜጀር

10 - መስኖይ ማይነር

11 - መስኖይ ፈርስት

12 - መስኖይ ሰከንድ

# ፭፬. የግጥም አፃፃፍ ስነ ፅሁፍ

ሀረር ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን ወደ ኋላ አንድ ሺህ አመታት መለስ ብለን የሀረሪን የስነ-ፁሁፍ ጅማሮዎች እና ስራዎችን እንቃኝ ካልን ለማመን እስኪታክተን ድረስ ከኢትዮጵያ ቀዳማዊ የስነ-ፁሁፍ ጅማሬ ሆኖ እናገኛታለን፡፡

በስልጣኔ አክሱማዊ ኪንግደም በነበረው ስልጣን ስልጣኔን በኢትዮጵያ አምጥቷል፡፡ ሆኖም ሀረርም በተመሳሳይ ሁኔታ የስልጣኔ ጮራ ሆና እናገኛታለን፡፡

ሀረር በስነ-ፁሁፍ ለቀዳሚነቷ ምስክር የሚሆን በርካታ የታሪክ አሻራዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌም በሀርላ መንደር የተገኙ የድንጋይ ፅሁፎች የሀረሪ የንጉሳዊ ሳንቲሞች ላይ የሚገኙ ፅሁፎች በእጅ የተፃፉ እድሜ ጠገብ መፅሀፍቶች፣ መሰሎችን ልንጠቅስ እንችላልን፡፡

እስልምና ወደ ሀረር ከገባበት ጊዜ አንስቶ ለሀረሪ የስነ-ፅሁፍ እድገት እና መበራከት ትልቁን ሚና ተጫውቶዋል፡፡ አብዛኛው ጥንታዊ ፅሁፎቻቸው ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸው መሆናቸው ደግሞ ለዚህ እውነታ ማረጋገጫ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በቀድሞው የስነ-ፅሁፍ ጥቂት ጥንታዊ ፅሁፎች የተፃፉት ከተለምዶው ለየት ባሉ የአፃፃፍ ስልት ነው፡፡ ያም ሀረሪዎች የራሳቸው አድርገው ይጠቀሙበት የነበረ ፉደሎች ናቸው፡፡ በአጠራሩም ሲሪክ አልያም ሻም አልፉቤት ይባላል፡፡ ይህ ፊደል ሱሪያ እና ቱርኮች በመጠኑ ይጠቀሙበት ከነበረ አልፋቤት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ይነገራል፡፡ ሀረሪዎችን ይህን ፊደል እየተጠቀሙበት ለዘመናት ከቆዩ በኋላ በአረበኛ ፊደል ተተክቶ ዛሬ በፅሁፎች ብቻ ቀርተዋል፡፡

ሀረር ላይ የምናገኛቸው ጥንታዊ ፅሁፎች ባጠቃላይ አጀሚ ናቸው፡፡ አልያም በሌላ ፊደል ተፅፈው ቋንቋው ደግሞ ሌላ ነው፡፡ ሀረሪዎች በአረበኛ ፊደል የመጻፍን ያዳበሩት ከእስልምና ሀረር መግባት እንዲሁም እነሼኽ አባድር ሀረር መዝለቃቸው ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በጊዜውም ዝክሪና መንዙማ በኋላ ነሺዳ ሀይምኖታዊ ይዘት ያላቸው በአረበኛ ፊደል እየተቀረፀ (እየተፃፈ) ሲሰራባቸው ቆይተዋል፡፡

ይህ አይነቱ አፃፃፍ (አጀሚ) ዛሬም በእምነቱ አባቶችና ወሊዎች (ብፁአን) ዘንድ በአረበኛ ፊደል የተፃፉ የሀረሪ ዝክሪዎችን ይጠቀሙባቸዋል፡፡

ሌላኛው እጅግ ብዙ አመታትን ያስቆጠረው እና በአሁኑም ጊዜ በሀረሪዎች እየተሰራበት የሚገኘው የመስኖይ ዘፈን ነው፡፡ መስኖይ በተለያዩ ፀሐፊያን የተደረሰ የሰርግ የዘፈን ግጥሞች ያዘለ እድሜ ጠገብ የግጥም እንደመሆኑ መጠን ይህ ግጥም ዛሬም በሰርግ ቤትና በተለያዩ ጊዜያት የሚዜሙ ናቸው፡፡

ይህ የመስኖይ ግጥም በአፃፃፍ፣ በቃል አጣጣሉ፣ በቀለሙና በአዛዜሙ ከተለመዱት የስነ-ፅሁፍ አሰራር እጅጉን የተለየና የራሱ የሆነ ይዘት ያለው ነው፡፡

ነገር ግን የሀረሪ ስነ ፅሁፍ ግጥማዊ ይዘት ያላቸው ቢሆኑም ስድ ንባብ አልፃፉም አልያም አልተጠቀሙም ማለት አይደለም በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተፃፈው «ኪታቡል አል ፋራኢድ» ታሪካዊ እና ሀይማኖታዊ ይዘት ያለው ሲሆን በተለያዩ በስነ ጽሁፋውያን የተደረሰ ነው፡፡

ይዘቱን ስንመለከት በማህበራዊና ሀይማኖታት ይዘቶች እንዲሁም በሀረሪዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ የስእልምና ሀይማኖቶች ስነ-ምግባሮች ከሀይማኖቱ ጋር የተያያዙ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን የያዘ እንደሆነ ያትታል (የሀረሪና የሀረር ከተማ ታሪክ) አብዱላሂ ሼኽ አህመድ ቡህ በ1998 ኸሊፍ ማተሚያ ቤት)

የሀረሪ ስነ-ፅሁፍ አሁንም ድረስ በቂ ጥናት ስላልተደረገበት እንጂ እጅግ በርካታ የታሪክ ደራሲዎችን የያዘ ነው፡፡ በሀረሪ፣ በኦረመኛ፣ በሶማሌኛ፣ በአረበኛ የተፃፉ በርካታ የቀዳሚነት አስረጂ መጽሐፎችን እናገኛለን፡፡

ታሪክ ቅርስን ትቶ ይሔዳል ቅርስ ደግሞ ለታሪክ ምስክር ሆኖ ለዝንተ አለም ይቆማል ያ ቅርስን ደግሞ ስለታሪክ እውነታ ለማረጋገጥ ሁሉም ቱሪስቶች ይጎርፋሉ፡፡ አይተው ተረድተው ለታሪክ ምስክር ሆነው ይሔዳሉ እናም እውነታው እንዲወጣ ሙዚየም ጠርዞ ያሥቀምጣቸዋል፡፡ መፅሐፍትን ለንባብ እናብቃቸው ፁሁፎቹ በዝምታ ውስጥ አንብቡኝ ብለው ይጣራሉና፡፡

የግጥም አፃፃፋቸውን ስንመለከት ወጥ የሆነ አፃፃፍ ባይከተሉም ብዙ አይነት የአፃፃፍ ስልቶችን ይተገብራሉ፡፡

አለቤኽ ደድ የገኛሉ - ረቢዮውቤ የገኛሉ

አልላ ጋፊዮው አኑም - አትፊቅሪለኻኽ

ሙሉእ ጌይ ጀምሚእ - ቀኚት ጃሊዩይ

*******

ውርስ ትርጉም

ከአላህ ፍቅር ያገኛሉ-ከአምላክ ያገኛሉ

የአላህ ባሪያ እኔም-እጫውትልሐለሁ

ሙሉ ከተማ ሁሉ-ቀኝ ጓዴ

ይህ አፃፃፍ በአማረኛው “ህገ-ወጥ ቤት”የሚባለው ሲሆን ግጥም ቤቱ ባይመታም በዜማ እተሸፈነ አልያም ግጥም ቤቱን በመድገም እርስ በእርሱ ቤት እንዲመታ አልያም ራሱን እንዲሞላ ያደርጉታል፡፡

ሌላይኛው የግጥም አፃፃፍ አጌጭ አልያም አቆላማጭ ፊደሎችን በመጨረሻው በማስገባት የሚፃፍ ነው፡፡

ደድኸሸ ዜለሜኝ ኺያር ኢፋጭበሻኽዋ

ሰባቴ ገደሌኝጊር መኚት ዘማኔይዋ

ከመትፌቀር በጂሔይዋ

*******

ውርስ ትርጉም

ፍቅርሽ ጎዳኝ ጉዳይ እፈልግብሻለሁና

ትግስቴ ቢገለኝ በተኛሁበት ዘመኔና

ጨዋታ ብዙዬና

“ዋ” የምትለው ፊደል በሀረሪ ቋንቋ አያያዥ “እና” ማለት ሲሆን በሌላ ጎኑ “ማ” የሚል ሲሆን ማጌጫ ፊደል ነው፡፡ ለምሳሌ እፈልግሽና፣እመጣና፣በይኝና፣አንቺማ፣ወ.ዘ.ተ...በሌላ አረዳድ በዚህ ግጥም አፃፃፍ የአራተኛውን የፊደል ረድፍ ይይዛል፡ -ሃ፣ላ፣ማ፣ሳ፣ራ፣ሻ፣ቃ፣ባ፣.......ማለት ነው፡፡

መካ ጋር አፈሬይ ነለሺዋ

አፈርሌም ሙሉሔይ ነለሺዋ

አይዜ ጪን ሐንቆቴይ ነለሺዋ

አውዜ ጋር አሳሴይ ነለሺዋ

አይዜሌ ሰባቴይ ነለሺዋ

አውዜሌ ሰላቴይ ነለሺዋ

# አሹራ

‹‹ዊርሺ ያኞው

ዊርሺ የሰበር

ዊርሺ ያኞው

ገል የሰበር

ኤሔር አመት አሹረኾም

ቢሻረኾም የቦርደኹ

አሎው አመት አመትዞም

ሙባረክ ዩሸለኹ

ኢሒትዚኛም ተሌቅለኹ

ኢህዚኛም የሌቅለኹ

አብባያ ሐሰንዚታ ሁሴንዚታ

ሊጂ የሰጠሸ

ኡሞው ዚኢማን ራጋ ኡሞው

ኩዶው ዚኢማን ራጋ

በርቲዚኛው ደለጌውዋ

ዴራ ደፍደፍ ዊዚዕ ጪፍጪፍ

ኺይሪ ባይ የንሰር

ሽሪ ባይ የሰበር፣አንገትዞም የትገመም

ትርጉሙ

መጥፎ ልማድ - መጥፎ ዱሰበር

መጥፎ ልማድ - ሸክላ የሰበር

መጪው የአሹራ አመት ቸር ወሬ ሚሰማበት ዱሑን

አልላህ አመት ከአመት የተባረከ ያድርጋችሁ

እህታችሁም ትደግላችሁ

ወንድማችንም ይደግላችሁ

ታላቅ እህቴ እንደ ሀሰንና ሁሴን የተባረከ ልጅ ይስጥሽ፣

አያቴ ሆይ እምነታችሁ በረከት ይኑረው

ውዱ አያቴ የተባረከ እድሜ

በትራችንን ደክሞታልና

ጓዳ ቅል ፍለጋ ላብ ይንጠፍጠፍ

በጎ አድራጊ ያሸንፍ

ከፉ አሳቢ ዱሰበር አንገቱም ይቆልመም

ይህ የሚዜመው በወጣቶች ሲሆን አሹራ በአል ነው፡፡ አሹራ በአመተል ሒጂራ አቆጣጠር ‹‹ሙሐረም›› ወር (አዲስ አመት መግቢያ የመጀመሪያው ወር) በ10^ኛው^ ቀን የሚከበር የሀረሪዎች ክብረ በዓል ነው፡፡

ከላይ የተቀመጠው የግጥም አፃፃፋቸው ከ”ሰንጎ መገን ቤት” የግጥም አፃፃፍ የሚመደብ ሲሆን ስንኞቹም አጫጭር ናቸው፡፡ እነዚህን እንደምሳሌ እንይ እንጂ በብዛት የሚጠቀሙት “የወል ግጥም” አፃፃፍ ሲሆን በተጨማሪነት ወዳጄ ዘመዴ ምነው ቤት፣ሌሎችንም ይጠቀማል፡፡እንደተቀረ የግጥም አላባዊያን ሁሉ ክረት፣ፍላት እና ቁጥብነት ይታይባቸዋል፡፡

‹‹አሩዝ ባይቲ ተስቲ - ሲዲስቲ ደረጃ

ከዛቄው ኡሱዕሌ ሱት አልፊ ደረጃ፡፡

(ጋብቻ ማለት ደስታ - ባለስድስት ደረጃ

ላወቀበት ሰው - ስምንት ሺህ ደረጃ)

አማረኛው የግጥም አይነቶች ላይ ክርክሮች ቢኖሩም በተለምዶ በሚገለፁት የእሳቤ የግጥም አይነቶች ለማየት የሞከርኩ ሲሆን የሀረሪውም በዘውግ እንጂ በአይነት ተለይተው ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ አመዳደቤ እምብዛም አያከራክረንም፡፡ሌላው የባህል ዘፍን ግጥም አፃፃፍ ላይ በ1960ዎቹ በኑሪያ አህመድ አሊ ሻሚ (ሻሚቱ) እንደተጀመረ የሚነገርለት ሱም ጋር “ስም ቤት” የግጥም አፃፃፍ ሌላይኛው ነው፡፡ ይህ አይነት የግጥም አፃፃፍ የሚሰራው ሊሞገስ የተፈለገው የግለሰቡ ስም ይወሰዳል

ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀደም በሻቱ የተሰሩ ዘፈኖችን እንመልከት የተሞጋሷ ስም "ሁስኒያ ሙሐመድ"

ቲንፋሸኸሸ ሱችነዞ ዘባድ ዘባድ

አኻሸ ነትገረፍ ነተገድ

ሁደፍ ሁዳ ኡድ ሁስኒያ ሙሐመድ

የሰሞጋሹ ስም፡- አሊ ባሻ

አዞው ቂሰዞ ሞቀሌ ዚኸሻ

ኢና ቢዝሐዞቤ ሩሕዞው ታአብ አሻ

ኸጣኧ ዛሻ ቂጤው ሒትፋንቤ ተስ አሻ

ሩሔንታ ቀልቤንታ ሱኡድ አሊ ባሻ

ከስያሜ አለፍ ሲል የመጡበትን አከባቢ አልያም ልዩ መለያ በመጠቀም ይሰራል፡፡

ጠበኸሸ ተስ ያሻል ከበንጂዋ ጠረብ

ሙብለኸሸ ደም አኛ - አጥሪያዋ ከባብ

ወቅቲዞ ቢሲንተሸ ዚፈካሕሺ አዜብ

አለምቤ ዋሊንተሸ አን አኻሸሌ ነኬብ

ቄሕ ኢስተሸ ዚቄሕ ዚፈካሕሺ አይነብ

ነፍሴቤ መላሕኼ ዲሚሸቂ ሻም አረብ

ዘማን ፡- 1958-1961

ዜመ ፡- ዘከሪያእ አብዱላሂ

ዋሊ ፡- አብዳላ ኦመር

ዊቅር ፡- ዘከሪያች አብዱላሂ

ሙጋድ ፡- አዲብ

## ሒርቃኦት፡-ደድኻሹው ጦርኾመ

ደድኸሹው ጦርኾማም ዛልሬዘኜኘቤ
ዋሕራች ኑግዳነትቤም ናርኹ ኡውሱእ ባድቤ
ሩሔው ኢሕባብሌዛኽ ሳቤሪ ሞሸቤ
ኢናብሪት ናርኹ አን በጂሕ ታአብቤ

1. ደድቤን ተአቃርኹ ኢሔር ሚንተ መለ
   አኻሸቤን ኢትቤቀኽ ኤኔም አልዋለለ
   ደኢም ኢናዲዛኽ ኩዴሚን ሐመለ።

2. ዚቦራደቤውመ ደዱው ዛጋረደ
   ንሒትፋንዞው ያስጠኻመ አን ኩውዴው ያብሪደ

3. በጂሕ ጌበትኹመ አሞሴኘ ማትማጀ
   ደድኻሸ ቀልቤ ኡውስጡቤ አይሰ አሳስ አሸ
   ኢማንሞት ኢሳልኹ ነይ ደዴው ዊረሸ ።

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]



[illegible]

[illegible]
[illegible]
[illegible]

1 [illegible]
[illegible]
[illegible]

2 [illegible]
[illegible]

3 [illegible]
[illegible]

ሽም፡ ~~[illegible]~~ ሃብቶም
ዘመን ዘበን ———

ዓ/ም፡ ሰኔ፡ ክክሰ፡
ዓ/ተ/ም፡ እስሀሮ—(4)—ክመልሮ—

19

# የግጥሚ፡ የሃገሩ

የግጥሚ፡ የሃገሩ፡ ዜኒሃቡ፡ ወሰኒ፡ የሸኔ፡ ቀሊን ኬብቶ
እግሮ፡ እንባዘው፡ ተሊሞን፡ እነው፡ እጣልው፡ ዜኒሃቡ

1 ወሃቡ፡ ለእኔ፡ ተሃዋ፡ ዓሰሃቂ፡ አዜጎም፡ ዩንክ።
አኑም፡ ዜሰሃቡ፡ ዜሌሰቢሃቡ፡ ዓዘርሂሉ፡
ሹንቲክን፡ ቀዩንክንባር፡ ተወጥ፡ ይግክ።

2 እንቋእጣሊ፡ ቀጠሉ፡ ንጋከን፡ ሀፀና፡
ኣሃ፡ መሳሉ፡ ዓንበር፡ ሉንደሲሉ፡ እንሰፀና፡
ቀዓብጋር፡ ንቀወሰሉ፡ መሰ፡ ሀፀና።

3 ንን፡ እርቅብሃቡ፡ ዩትክ፡ እዝዲ፡ በሹ፡ ሃቲ፡
ክደ፡ ሹዘናው፡ ሹሉሉ፡ ዲሌና፡ ዘሰቲ፡
የሰ ዲጎሞ፡ ሌዳናቆው፡ ተሰጊ።

4 ዲጣሊው፡ ዲሀሉ፡ ሹሉውን፡ ደንክው፡
ሀጀትሉ፡ ኤንሰሹ፡ ሹሮቲጎም፡ ዘዝቲ፡
ቆዐ፡ በሺሀ፡ እመክጎም፡ ዘሃናሉ።

ግጥም፡ ስለ፡ መምህራን፡
2ኛ፡ እንደወጣ፡ ዘንድ፡
ለተማሪዎች፡ ሀሁ፡ ሲሉ፡
እኔ፡ ብዙ፡ ሰው፡ መተዉዘነ።

1 ስለ፡ መንግሥት፡ ሰዉ፡ ሰማያ፡ ዘሀገርንት፡
እሱን፡ መምህር፡ ግን፡ ያሸከነዘወት።

2 ግን፡ እኝ፡ የሌለው፡ እንዴ፡ ዘወንት፡
ቀለዉ፡ የንኮሌ፡ ሰማያ፡ ስሰሌሰንት።

3 ገሌብኝ፡ ብዙ፡ ፍርዕ፡ ተመሳዮች።
ቢንደት፡ ቀለቀንጭ፡ ዘኝ፡ ዘለእሱዎች።

4 ያሌዘወ፡ ዘየምግሌወ፡ ምቃ፡ እንደዎች፡
ቤሪተሰ፡ ፈርየይሄለወ፡ እሌበወ፡ እዋሌምሳኝ።

# 25. ሀረሪ በአማርኛ ስነ ፅሁፍ

ስለ ሀረር ስነ-ጽሑፍ አጀማመርና አፃፃፍ ብዙ አንብበናል ብዙም ብንል ስለአስገራሚ የቃል አጣጣልና አስገራሚውን አፃፃፍ በስነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸው ለመታዘብ ችለናል፡፡ በተለይ በግጥም ፅሁፍቻቸው የሚያስገርሙ ገጣሚያን የተፈጠሩባት ሐረር እንደነ አብዱላፊዝ ኸሊፋ፣ ከቢር ኡመር አብዶሽ፣ ሼክ አብዱል ማሊክ፣ አው ሻሚ፣ከሊፋ ኡመር፣አብዱልአዚዝ አደም፣ በሽሙጥ ግጥም ፅሑፍ የሚታወቀው ኢድ አፈንዲ፣ ሰላህዲን፣ አብዱልፈታህ እያልን ለዛሬ ገጣሚያን እንደርሳለን፡፡

“ኑጉስ የሆኑት በስድስት ወራቸው

ሰማይ ለሰማይ ይሔዳል አቶ ሞቢላቸው” (አይ ሻሚቱ እ.ኤ.አ.1965 በተቀዳው አልበሚ ላይ የተወሰደ)

የሀረሪ ስነ-ጽሑፍ ሲፃፍ የኖረው በሀረሪ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በአረበኛ፣ በሶማለኛ፣ በኦረመኛም ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም ከ1890 በኋላ የአማርኛ የስነ-ፅሑፍ ስራዎች በሀረሪዎች በዝተው የታዩበት ጊዜም ነበር፡፡በተለይ በፅሑፍ የማናገኛቸው ነገር ግን በስነ- ቃል የሚገኙ የስንኝ ቋጠሮኦች በቁጥር የሚገለፁ አይደሉም፡፡ ህዝባዊ ስነ- ቃል አልያም ኪነ-ቃሎች አሁንም ድረስ የሚጠቀሙበት ሲሆን በያንዳንዱ ስነ-ቃል የስንኝ ቋጠሮ በተለያየ መንገድ በልጆች ጨዋታ፣በመዝሙሮች፣በዘፈኖች ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን፡፡ በሐይማኖታዊ ይዘት ያላቸው፣ ስለፍቅር፣ ስለአገር ወዘተ... በምስል ዙሪያ የግጥም መድብሎች በስንኝ እየተለቀቁ የተበራከቱበት ጊዜ ነበር፡፡

ምክንያቱም ሀረሪዎች ቶሎ እንግዳን የመላመድ እና ከራሳቸው መሐከል ማድረግ ስለሚችሉ እንዲሁም ስሜትና ፍላጎታቸውን የቋንቋው ተናጋሪ ያልሆነው ክፍል እንዲረዳቸውም በማሰብ ይመስለኛል፡፡

‹‹ከዋርካ ላይ ዋርካ ከዛፍ ላይ ቀዘፋ

እንኳን ባልእንጀራ- የሚታመን ጠፋ

እወዛወዛለሁ እንደ ባህር ዛፍ

ያለቅኔም አልሞት ከቅኔም አላልፍ

ድሬደዋ ወርዶ ይበላል እንጀራ

አሁን የት ይገኛል የሆድ ባልእንጀራ

የለበሰው ኩታ ንጉሴ መንነዋ

አንለይ አንለይ አንለያይዋ››

ዋልፍ ሌስሎው ‹‹ቼንሰንስ ኦፍ ሀረሪ›› በሚለው መጽሐፍ ካካተታቸው የመስኖይ ግጥሞች መካከል የተወሰደ ሲሆን ከዚህም ባለፈ በሀረሪ ሰርግ ላይ ይዘፈኑ የነበሩ የአማርኛ ስንኞችም እንገኛለን፡፡ አንቀር ማህጠብ ተብሎ በሚጠራው የሰርጉ አንድ ክፍል በሆነው ቀን

‹‹ማማ ማማ ዲሌ ሆ - አንበሳ አለው ጋማ

ማማ ማማ ዲሌ - አምበሳ አለው ጋማ

አምበሳ ገድዬ ሆ - ገደል ሆነብኝ

ሰው እያየኝ መሸሽ - ነውር ሆነብኝ››

እያለ የሀረሪ ግጥሞችን ያካትትና ሁሉን ያማከለ ስነ-ግጥም ጥበብን እናገኛለን ከዚህ ወጣ ስንል በረመዳን ፃም ወር ላይ ወጣቶችና ህፃናት ተደራጅተው ልክ እንደ ሆያ ሆዬ በየቤቱ እየዞሩ የሚጫወቱት ጨዋታም አለ ያ ላይም ይህንኑ የግጥም ስንኞች እናገኛለን፡፡

‹‹መቃብር ገብቼ - ጎኔን ብዳብሰው

ከወንጀሌ በቀር - አጣሁኝ እንድም ሰው››

የመቃብር ድንጋይ - ሲመታኝ አናቴን

ያንጊዜ አወኩኝ - ከሰው መለየቴን

ቀብር ቀብር ይላል ቀብር ምን አለበት

መልካም ስራ ሰርቶ ገብተው ቢተኙበት

የሰማይ ላይ ኮከብ ማሕሉ ጨረቃ

ያረሱለላሒ ሑኑልኝ ጠበቃ

ሐቄን ስጡኝና በትልቁ ቁና

የሰዉ ስጦታ አይጠቅመኝምና

አባቴን ብመራ እናቴን ብመራ

እኔን አረከኝ የመሐመድ ባሪያ

‹‹ቡናው ፈልቶ - ሲኒው ሲደረደር

ከተፍ ከተፍ ይላሉ- የነብይ ወታደር›

ጫትና ቁና የለውም አሮጌ

አሰላሙአሌይኩም አባዲር ሀረርጌይ

መሰል ስንኞች ባማሩ የዜማ ቅላፄ ታግዘው ጆሮን ሳይሆን ልብን ያደማሉ፡፡ እያንዳንዱ ስንኞችም በቃል እየተባሉ ገጣሚው፣ ደራሲው ባለቤቱ ሳይታወቅ የህዝቡ ሆኖም የቀሩ በርካታ ናቸው፡፡

‹‹ውሃ እንጠጣ ነበር በአንድ ኮዳ

አያሳዝንም ወይ - የወደዱት ሲከዳ

የአባይ ውሃ ሞልቶ ዳርዳሩ ያፈሳል

እንኳን ያንቺ ፍቅር - የናትም ሞት ይረሳል

የአባይ ውሃ ሞልቶ ግንድ ያገላብጣል

ፍቅር የጋራ ነው ምን ያለማምጣል

ስጡኝ ጥቁር ልብሴን ሐዘን ይመርብኛ

ተዋዶ መለያየት - ተደጋገሙብኝ

አገር ከማጋራ ቁና ከማጋራ

የወደዱት ሳሂብ ሲሆን ባላጋራ

ምናልባት ስሜትን ከመግለጽ አንጻር ብዙ ቢቀርም ከዚህ በላይ የሚገለጽባቸው ቃላት አሉ ብዬ አላስብም ምክንያቱም እነዚህ ብዙ ይናገራሉና፡፡

ሌላው አንድ ምሳሌ ለመስጠት ያክል በሮመዳን ፆም ጊዜ ታዳጊዎች እንደ ሆያ ሆዬ ቤት ለቤት እየሔዱ የሚጨፍሩት አልያም አንዳንዴ ዚክሪዎችም በዚሁ ሚገለፁበት ጊዜአት አሉ ታዲያ ይህን እስልምና በሀረሪዎች ባቻ የተገደበ ባለመሆኑ ሁሉንም ተደራሽ ለማድረግ በአመ፣ረኛም ይዜማሉ፡፡

አልፊይ ሰላት ወሰላም አላ

አልፊይ ሰላት ወሰላመላ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

እስቲ ልጀምረው ቢስሚላሒ ብዬ

ሼኹን አብደላ ህዝቡን መስዬ

ያ ሰዩዲ ያ ረሱለላህ

ነቢ ሲወለዱ ሲወጣ ራሳቸው

ላኢላ ሐኢለላህ አለ ምላሳቸው

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

ነቢ ሲወለዱ ሰኞ ወደማታ

ጂብሪል ይዞ መቶ የቁርአኑ ባታ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

መካና መዲና አንድ ነው መሬቱ

መዲና ይበልጣል ረሱል ያሉበቱ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

ነቢ መካ ወርደው መዲና ሲያርፉ

ደክሞ የነበረው ለመ፤ለመ ዛፉ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

ልሙት እንጂ ወልላሒ አልቀርም

እንኳን በውሐና በእሳት ብቃጠልም

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

እኔ እወዳችኋለሁ አንቱም ውደዱኝ

አገሮ መዲና መካ ውሰዱኝ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

እንደምን ያለነው አንቱን የሚጠላ

ከሐራም ተወልዶ ካልሆነ ወንዳላ

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

እኔን የሚገርመኝ የመሐመድ ነገር

አርሺ ተደግፎ ከአላህ መነጋገር

ያ ሰዩዲ ያረሱለላህ

ሙሐመድ ሙሐመድ ሙሐመድ ደጉ ሰው

እንኳን ለኡመቱ ለአውሬም የሚዋሰው

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

ሙሐመድ ሙሐመድ ሙሐመድ አዲሉ

የወረደላቸው ወላ ፈዳዲሉ

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

የወረደላቸው ሰባህ አሊላሂ

መዲና ቤታቸው ነው ወልላሒ ቢላሒ

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

እኔን የሚገርመኝ የጃሒል ኩራቱ

ሰላትን ሳይሰግድ እስላም ነኝ ማለቱ

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

ሰላትም ስገዱ ኢማንም ልመዱ

ለወንድም ለሴትም አንድ ነው መንገዱ

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

ይከተላቸው ነበር የዳመና ዱካን

ሞት አልቀረላቸው ለሞሐመድ እንኳን

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

እባክህ ጌታዬ አርገው እንደነበር

ሁሉም እንግዳነው አንተነህ ባላገር

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

አንበሳና ነብር የሰገደላቸው

እኛ እንሒድ እንጂ አይመጡ እሳቸው

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

አፌት ሰላት ማለቴ ገና ነው

ሚዛን ተመዝኖ ስራ ሲሞላነው

ያ ሰዪዲ ያረሱለላህ

አፌት ሰላት የለፋ ምላሱ

የቂያማለታ ሞሐመድ ነው ዋሱ

አፌት ሰላት ወሰላም አላ

አፌትሰላት ኢወሰላመላ

ያሰኢዲ ያረሱለላህ

በርግጥ የሀረሪ ግጥሞችን እንኳን ሰብስቦ ዳግም ለንባብ ማቅረብ ባይቻልም፡፡ በቀላሉ ለማሰባሰብ የአብዱልሀፊዝ ኸሊፋ የአማርኛ ግጥሞችን ‹‹ምን ይሻላል››፣ ‹‹ይሉኝታ በቃኝ››፣ ‹‹ውሃና ጠጪው››፣ ‹‹ብሞት አልሞትም›› መሰል ስራዎቹን አፈላልጎ በማሰባሰብ ‹‹ሀ›› ተብሎ ቢጀመር ሀረር ላይ በሀረሪዎች ስነ-ጹሑፍ ምን ያህል እንደተሰራበት የሚጠቁም ነው፡፡

# የአርቲስቶቹ የፎቶ መግለጫ



የኪነ ጥበብ አባት ገጣሚና ደራሲ

አባ ኢድ አፈንዲ





የጌይ ኣዳ ፈቀር ንግስት ኣይ ኣኑሪያ

(ሻሚቱ ኣህመድ  ሻሚቱ)



ቦይስ ክለብ








ጊታር ተጫዋችና ዘፋኝ አብዶ ፈዘል



ገጣሚና ደራሲ ከሊፋ ኡመር



ገጣሚ ዘፋኝ እና መምህር በድሪ ሊማይ




እ.ኤ.አ 1960 በኒና ፊሸር በመጀመሪያው ሞይ ጋር(የስፌድ ት/ቤት) ውስጥ
ሻሚቱ እና ቤተሰቦቿና ጓደኞቿ ጋር ስዘፍን



የሐይዋን ባንድ መስራቾች  አንዱና የግል ሙዚየም ባለቤት አቶ አብዱላሒ አሊ ሸሪፍ



በስተቀኝ አሊ ቢራ በስተግራ  አህመድ ጊዳያ



አብዱል ባሲጥ (አብዲ ጊታር)



ከቢርአብዱልሙሔሚንአብዱናሲርኢብራሒም ገጣሚ፣
ዜማደራሲ፣ፈላስፋ፣የባህልእናታሪክተመራማሪ



ከፊል የሙጋዶች እንቅስቃሴ














አርቲስት ሰላህ በርኽሌ እና መንሱር አብዱል መጂድ(ሙንሺ)



ቡሌ አህመድ ድራር


ለሐኒ ወቂር
ሰዒድ አ/ቃድር (ዋሊ አነስ)
1. ዲልሶት
2. በንደር
3. ተላይና
4. ማኡኒሊ
5. ጢንማን
6. ዙጉሚት
7. አሽሩር
8. ሄጆሶት
9. አዴድቡራ
10. አቃተኝ
ዲልሶት
Seid A/kadir(Anus)
2014



ቡሌ አህመድ ዱራር እና  ሻሚቱ ሰርግ ላይ ሲጫወቱ


የሂላል አባላት



ዚክሪ ከረቦ



ገጣሚ ኣብዲ ቱሬ

# ጥቂት የ አዳ ፈቀር ዘውግና ስያሜዎች

| ተ.ቁ | የዘፈኑ መጠሪያ | ምድብ | ልዩ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጌ’ይቀሀትሌ | ኮአታን ኮአት | |
| 2 | ዋሊዬይ | ኮአታን ኮአት | |
| 3 | ወይሌሌ | ኮአታን ኮአት | |
| 4 | አሎይአሎይ | ኮአታን ኮአት | |
| 5 | ሀረሬይ | ኮአታን ኮአት | |
| 6 | አሚሬይ | ኮአታን ኮአት | |
| 7 | አልለፈንኖው | ኮአታን ኮአት | |
| 8 | አልለአሚሬይ | ኮአታን ኮአት | |
| 9 | አዋይኤሌላዎ | ደርሲ | |
| 10 | ጃሊዪይሀለስ | ኮአታን ኮአት | |
| 11 | ጀሊዬይኣዋች | ኮአታን ኮአት | |
| 12 | ጃሊዬይኣያች | ኮአታን ኮአት | |
| 13 | ጃሊዬይጌላች | ኮአታን ኮአት | |
| 14 | ጉፍተሞገድ | ደርሲ | መስኖይ |
| 15 | አኑ’ዜይ | ደርሲ | መስኖይ |
| 16 | ሀይበለቅ | ደርሲ | |
| 17 | አውቀሀቴይ | ደርሲ | |
| 18 | ሊዋዬዋዬ | ደርሲ | |
| 19 | ጪንጬሀ | ነሺዳ | |
| 20 | ባዴሀረር | ደርሲ | |
| 21 | ዚቄሀ ዘሊቃለቆ | ደርሲ | |
| 22 | ጌይወልዶውጌይጊበዋ | ደርሲ | |
| 23 | ዲጃ በሎ | ደርሲ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 24 | ዚሰፍታ ዚከመልታ ማን | ደርሲ | |
| 25 | አሹራ | ነሺዳ | |
| 26 | ነለሺ | ሳሌይ | |
| 27 | ሳይ ለሌ | ሳሌይ | |
| 28 | አሺት አሩዜይ | ደርሲ | |
| 29 | ሐና ሞገድ | ደርሲ | |
| 30 | ደድሌ ደድሌ | ደርሲ | |
| 31 | ኩዴ ከፈር ያሌይ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 32 | ሐፎት | ኮኦታን ኮኦት | |
| 33 | ሰፍፎይ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 34 | አሚሬይ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 35 | አብባ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 36 | ተስ የለሽ ሀረሬይ | ደርሲ | |
| 37 | ራሐ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 38 | ዋሊዮይ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 39 | አሰላቱ ወሰላሙ አላ | ደርሲ | |
| 40 | ኢናችሌም አልላሁ ዩሽለና | ደርሲ | |
| 41 | ጌሌሌም አሽሌ | ደርሲ | |
| 42 | ሀረሩ ሼለሜማ ሼመቄ | ደርሲ | |
| 43 | አሰላቱ ወሰላሙ አላእ ረሱሉላህ /መቆፋይ/ | ደርሲ | |
| 44 | ነቢኾ ሲናኑ /ሜገልዞ/ | ደርሲ | |
| 45 | ያሽዛል አልላ | ደርሲ | |
| 46 | ኑሮ ነቢ | ደርሲ | |
| 47 | ቢስሚላእ ራህማን ረሂም አማ ኢሳል የቶር አሩዜይ | ደርሲ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 48 | ሐደስ ጫያ አዮባን ሚገር ዛሌ | ደርሲ | |
| 49 | ያሲን ሑጡርቤ | ደርሲ | ኮኦታን ኮኦት |
| 50 | ሺፍቱ ጋሉ | ደርሲ | |
| 51 | አይነናር ዛላ አውኻሽ ጌዮይ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 52 | አው ቀሐቴይ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 53 | አዋይ መካ ሐሮው | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 54 | ዋትቲ አሩዝዋ ቤልቲ አሩዝዋ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 55 | ቢቀይማ ሼሽኚ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 56 | ቢስሚላ ዶኝ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 57 | ጌይሌ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 58 | አው አባዲር ወልዳች | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 59 | አውወል ፈለኬይ | ደርሲ | |
| 60 | ባዴ ሀረር ዱፍዜ ደዌይ | ደርሲ | ደባል ፈቀር |
| 61 | ሉሙ ሌይሙኔይ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 62 | አኪዮ ሚላኪይ | ደርሲ | |
| 63 | ሀረር አማተሺዋ | ኮኦታን ኮኦት | |
| 64 | ነይ መዲዋሎው | ኮኦታን ኮኦት | |
| 65 | ያወዱድ ኢማን አልቢሰና | ኮኦታን ኮኦት | |
| 66 | የጦርሌ | ኮኦታን ኮኦት | |

# የቃላት ፍቺ

1- ዊቂር - ግጥም

2- ላሕኒ - ዜማ

3- መዚቃ - ሙዚቃ

4- ዋሊ - ዘፋኝ

5- ፈናን - አርቲስት

6- መሸረብ - አዝማች

7- ሚጊር - ስንኝ

8- ዱመሲዛል - መሪ ድምጻዊ

9- ዱላሕዲዛል - አጃቢ

10- ሙጋድ - ባንድ አልያም ማህበር

11- ጌይ - ከተማ

12- ጩቅቲ - ቃል

13- ሐርፊ - ፊደል

14- ዊቂር ጋር - ግጥም ቤት

15- ሐንካ - ግጥም ቤት

16- ሐዋጅ - ግጥም ቤት

17- ኮረኪ -አዝማች

18- ቻላ - ምት (Beat)

19- ቻላ - ቤት(የዜማ፣የግጥም፣የምት ቤት/Bar/)

20- ፊቀር - ዘፈን

21- ነሺዳ - መዝሙር

22- ዚክሪ - መዘከር(ሐይማኖታዊ መዝሙር)

23- መርኩዝ - አንጓ

24- ረካ - የግጥም ቤት ብዛት

25- ከረቡ - ከበሮ

26- ከበል - ከእንጨት የተሰራ ማጨብጨቢያ

27-ደፍ - ከክብ እንጨት ከቆዳና ከክብ ብረት የተሰረረ የአንድ እጅ ከበሮ

28- ከበርጂ/ደርቡካ/ - ባለ አንድ ፊት አነስተኛ የእጅ ከበሮ

29- ዋይ ዊቂር - የግነት ግጥም

30- ደባል - ዳንኪራ

31- ደባል - ጭፈራ

32- መስላሕ- ባህላዊ የዳንስ አይነት

33- ቦቢሽ - ባህላዊ ዳንስ

34- ሺኒኒሕ - ባህላዊ ዳንስ አይነት

35- ጌይ ፈቀር - የከተማ ዘፈን(ዘመናዊ ዘፈን)

36- ጌይ አዳ ፈቀር - ባህላዊ ዘፈን

37- መትቃፈጥ - መጋፈጥ/ግጥም ከመሪ ድምጻዊ አጃቢ የሚወስድበት ነጥብ/

38- ወሬግ በሪ - መሰረታዊ የፈግጥሙ ውበት ያለበት አንጓ

39- ኡፍ ከፈት ዱፍ - ከአፍንጫ የሚወጣ ድምጽ(Falesyto vocal)

40- ጎረራ ጠባ - ወፍራ ድምጽ፣የሻከረ

41- ሲጠር ጠባ - ቀጭን ድምፅ

42- ሊህዲ ጠባ - የተፈጥሮ ድምጽ

43- መረኖ ጠባ - ያማረ ድምጽ

44- ሐቁር ጠባ - የደፈረሰ ድምጽ

45- ሲጠር ዋብ - እጅጉን የቀጠነ ድምጽ

46- አጉዝ ፈቀር - የሚስጨፍር ዘፈን

47- ዳገር - የድምጽ እርግብግቢት

48- ሰርቃ - ቅላፄ

49-ጃሊዩይ - ወዳጄ

50-ዊረይላ/ዊረጅላ/ - ውረጂለት

## ዋቢ

**Abdulmuhaymin Abdunassir**, *Harari Gey Fäqär*,

Addis Ababa, Artistic Printers, 1995

**The Mugads Of Harar Author Duri Mohammed** Source University College of Addis Abeba Ethnological Bulletin #4 December 1955

**THE RELEVANCY OF HARARI VALUES IN SELF REGULATION AND AS A MECHANISM OF BEHAVIORAL CONTROL:** HISTORICAL ASPECTSABDULMALIK ABUBAKER

**Yusuf, A**. (1960)'An Inquiry into some Aspects of the Economy of Harar and the Records of the Household Economy of the Amirs of Harar (1825-1875)': Bulletin of the Ethnological Society of the University College of Addis Ababa, 10 (July-Dec).

አቤጅ መፅሔት ቁጥር 1/1998

**Waldron S. R.** (1980). A farewell to Bab Haji:

City symbolism and Harari identity, 1887-1977. In D. Donham, and W. James (Eds.), Working papers on society and history in imperial

Ethiopia: The southern periphery from the 1880's to 1974 Cambridge: African Studies Center

**Aleqa Taye Gabra Mariam** (1861- 1924)

Rassegna di studi Ethiopici . vol 25 1971 – 1972

Cultural identity, Islamic revivalismand women's new-found role in preserving and transmitting musical traditions.Suggestions from Harar, Ethiopiaby Ilaria Sartori (Roma, Italy)